# የማርያም
## ታላቅ አእምሮ



## THE GREAT MIND OF MARY

ዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ

ሐምሌ 2005 ዓ/ም

@ 2013 Dr Wodajeneh Meharene.

የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው !

አድራሻ

ስልክ፡ 0911-212149, 0114653677

e-mail: drwodaje@yahoo.com

ፖስታ፡ የመ.ሳ.ቁ 915

አዲስአበባ፡፡

የሽፋን ዲዛይን

ዳዊት ቶሎሳ፡ 0911901178

አከፋፋይ

ግርማ ባዩ፡ 0911417441

ከዚህ በፊት በደራሲው የተፃፈ መፅሀፍ

ክሎዥር (Closure) 2003 ዓ/ም

# ለአለቃዬ አበረክታለሁ !

እጅግ በጣም የምወደው አለቃ አለኝ፡፡ ላለፉት አስራ ስድስት አመታት በእርሱ ስር..... በእርሱ ፀጋ...... ለእርሱ ነው የሰራሁት፡፡ የሚገርመኝ ነገር አንድም ቀን ሲሳሳት አይቼው አላውቅም፡፡ ይልቁን እኔ ስሳሳት ሳይቆጣኝ በፍቅር ያርመኛል፡፡ አንድ ጊዜ እንኳን አመናጭቆኝ አያውቅም፡፡ ሁል ጊዜ የተሻለ ሰው እንድሆን ያስተምረኛል፡፡ እኔ ተደስቼ ሲያየኝ በጣም ነው ደስ የሚለው!፤ መከፋቴን አይወድም!፡፡ ሲደክመኝ ያሳርፈኛል፡፡ የሰራሁትን ሪፖርት ሳደርግለት ከሰራሁት በላይ ያበረታታኛል፡፡ እንደርሱ ያለ አለቃ የትም የሚገኝ አይመስለኝም፡፡

ታዲያ ይህን መፅሀፍ ፅፌ ስጨርስ ለእርሱ ላበረክትለት ወደድኩ፡፡ ስለዚህም እነሆ!........ በሰማይና በምድር የመጨረሻው ስልጣን የእርሱ ለሆነው፣ ........የሁሉ ፈጣሪና ባለቤት፣ ........ የጌቶች ጌታ፣......... የነገስታትም ንጉስ ለሆነው ለተወደደው አለቃዬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን መፅሀፍ አበረከትኩ፡፡ የተወደድክ ንጉስ ሆይ ስጦታዬን ተቀበለኝ!፡፡ ለመፃፍ ፀጋ፣ አቅምና ጊዜ የተሰጠኝ ባንተው እንደሆነ አልረሳም፡፡ ይህንንም መፅሀፍ ለምትወዳቸው ሁሉ በረከት አድርገው፡፡ አመሰግናለሁ...... ከልቤ!፡፡

## ማውጫ

❖ ይህን ሳያነቡ አያንብቡ ! .................................... 5

1. ራስን በልዩነት መቀበል ! .................................... 10

2. ለህይወት ጥሪ መኖር ! .................................... 14

3. ለመማር ፈቃደኛ መሆን ! .................................... 17

4. ሞገስን ፈልጎ ማግኘት ! .................................... 19

5. ከቅንአትና ከውድድር መራቅ ! .................................... 21

6. ራስን ዝቅ ማድረግ ! .................................... 23

7. ሌላውን ሰው አለመናቅ ! .................................... 25

8. በቀላሉ አለመቀየም ! (Taking no offence!) .................... 27

9. ቀናውን ማሰብ ! (Positive Thinking!) .................... 30

10. የጥበብ አክሊልን ማድረግ ! .................................... 33

11. ሳይታክቱ ተግቶ መፀለይ ! .................................... 36

12. "እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ" ማለት ! .................................... 38

13. የማይችሉትን ማወቅ ! .................................... 40

14. መለወጥ የማይቻለውን መቀበል ! .......... 43

15. የሚዋጉትን ጦርነት መምረጥ ! .......... 45

16. በትዕግስት መጠበቅ ! .......... 47

17. ትክክለኛ ጊዜን ማወቅ ! .......... 49

18. በመከራና በስቃይ መፅናት ! .......... 51

19. ሌሊቱ እንደሚነጋ ማመን ! .......... 55

20. ሁሉን ይቅር ማለት ! .......... 57

21. በቀልን ለእግዚአብሔር መተው ! .......... 59

22. ሰላምና እረፍትን መለማመድ ! .......... 61

23. የደስታን ምንጭ ንፁህ ማድረግ! .......... 63

24. ድንግልናን መጠበቅ! .......... 67

25. ለውስጥ ውበት ዋጋ መስጠት ! .......... 69

26. በእምነትና በመተማመን መኳደድ! .......... 71

27. ቃሉን አውቆ ማድረግ! .......... 74

28. የሀገርን ህግ መጠበቅ! .......... 77

29. ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት! .......... 79

30. ልብን በማዳመጥ መመራት! .................................... 82

31. መስጠትንም መቀበልንም ማወቅ! ........................... 85

32. የርህራሔ ስራን መስራት! ........................................ 88

33. በመታዘዝ መባረክ! ................................................ 91

34. አነጋጋሪ መሆንን አለመፍራት ! .................................. 93

35. ለተቃዋሚዎች መልስ አለመስጠት ! ........................... 95

36. መልካም ስብዕናን መጠበቅ! ...................................... 97

37. ወደ ብስለት (Maturity) መድረስ! ........................ 100

38. ለዘላለም ህይወት ማሰብ! ....................................... 103

39. ታሪክ ሰሪ መሆን! ................................................. 106

40. ሌጋሲ ትቶ ማለፍ! ................................................ 108

- ሜርዮሎጂ (Mariology) ........................................ 111
- ኤኪዉሚኒዝም (Ecumenism) .............................. 118
- የሀይማኖቶች ውይይት (Interfaith Dialoge)................. 120
- ምስጋና.......................................................121
- ፀሎት ......................................................122

# ይህን ሳያነቡ አያንብቡ !

መንገድ ላይ ነበርኩ:: ቀዩ የትራፊክ መብራት ስለበራ ህግን አክብሬ መኪናዬን አቁሜያለሁ:: ከፊት ለፊቴ አንዲት ታክሲ ቆማለች:: በጣም አሮጌ ታክሲ ነች........የድሮ ታክሲ!:: አዲሱን የተሽከርካሪ ምርመራ እንዴት እንዳለፈች አላውቅም:: ለነገሩ የኔዋም መኪና በተአምር ነው ያለፈችው:: ከፊት ከፊቴ በብዙ ችግር ስትሔድ አይቻታለሁ.......ትንቀጠቀጥ ነበር ታክሲዋ!:: በዚህ ላይ አራት ሰው ጭናለች:: መንገዱ ከብዷት የሞት ሞቷን ነው ትሔድ የነበረው:: በሩ በደንብ ስለማይዘጋ ሹፌሩ ሁለት ጊዜ ከፍተው በሀይል ሲዘጉት አይቻቸዋለሁ:: አሁንም ግን በሩ የተዘጋ አይመስልም::

ታክሲዋ አዲስ ቀለም ስለተቀባች እርጅናዋን ለመሸፈን ሞክራለች..... ሙሉ ለሙሉ ባይሳካላትም:: ታዲያ ከፊቴ ስትቆም የኋላ መስታወቷ ላይ የተለጠፈውን የፅሁፍ ስቲከር ለማንበብ እድል አገኘሁና አነበብኩት!:: ፅሁፉ የሚለው እንደዚህ ነው........ "ከመቅናት መስራት!" ይላል:: ትርጉሙም "እኔን እያየህ በቅናት አትብከንከን! እኔ ጋ መድረስ ከፈለክ ስራ!" ማለቷ ነው..... ታክሲዋ!:: እኔም ምክሬን ተቀብዬ አረንጓዴው መብራት ሲበራልኝ መንገዴን ቀጠልኩኝ::

በየ ሀገሩ በመኪናዎች ላይ የሚለጠፉ ፅሁፎች አሉ:: ፅሁፎቹ የሚያስተላልፉት የሹፌሩን ወይም የመኪናውን ባለቤት መልዕክት ነው:: አሜሪካ "Leave me alone!!" የሚል ፅሁፍ አንብቤያለሁ፤ "ተወኝ ባካህ!!" ማለቱ ነው፤ ከማ ጋ እንደተጣላ አላውቅም:: ሌላ ጊዜ ደግሞ " It is none of your bussiness!" የሚል አነበብኩ:: "ምንም አያገባህም!!" ማለቷ ነው:: "አወይ አሜሪካ!" ብዬ አለፍኩኝ::

በከተማችን አዲስ አበባም በብዙ መኪናዎች ላይ እንዲሁ የተለጠፉ የፅሁፍ ስቲከሮች አሉ፡፡ የእኛን ለየት የሚያደርገው ግን ብዙዎቹ ፅሁፎች ሀይማኖታዊ መሆናቸው ነው፡፡ የሚያስቁን ሳይሆኑ አንብበናቸው በአክብሮት ዝም ብለን እንድናልፍ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከመልክታቸውም የሾፌሩን ወይም የመኪናውን ባለቤት እምነት ያሳያሉ፡፡ "ኢየሱስ ያድናል!"........ "እኔ የኢየሱስ ነኝ! (I belong to Jesus!)"....... "ያለ ቅድስት ማርያም አማላጅነት አለም አይድንም!"......... "የናቁሽ ሁሉ ከእግርሽ በታች ይሰግዳሉ!"......... "የፍቅር እናት የሰላም!"....... "አላህ በቂዬ ነው!"....... የሚሉት የተወሰኑት ናቸው፡፡

በመልዕክታቸው ሁሉም ያላቸውን እምነትና ፍቅር ያንፀባርቃሉ፡፡ አሁን አሁን ታዲያ ቅድስት ማርያምን የሚመለከቱ ፅሁፎች እየተበራከቱ መጥተዋል፡፡ የሀበሻው ህዝብ በአብዛኛው ማርያምን በጣም ይወዳታል፡፡ ብዙ ሰዎች በማርያም ስራ፣....... በማርያም ፍቅር፣...... በማርያም እናትነት፣...... ላይ ተመስርተው ለልጆቻቸው ስም ያወጣሉ፡፡ "ገብረማርያም"፣...... "ፍቅረማርያም"፣ ....... "ወልደማርያም" እያሉ፡፡ ደግሞም ሴት ልጆቻቸውን "ማርያማዊት"፣....... "ቅድስት"፣........ እያሉ ስም ይሰጧቸዋል፡፡ የሚያስገርመኝ ግን የላቲን አሜሪካ ህዝቦች ልጆቻቸውን "ሜሪ" ወይም "ሚሪያም" የሚለውን የማርያምን ስም በቀጥታ ወስደው ሲጠቀሙበት ሀበሾቹ ግን "ማርያም" ብለው ለልጆቻቸው ስም አይሰጡም፡፡ ልክ ወንድ ልጆቻቸውን "ኢየሱስ" ብለው እንደማይጠሩ፡፡ ይህም ከአክብሮት የተነሳ ነው፡፡

ህዝባችን ለማርያም ያለው ፍቅርና አክብሮት ልዩ ነው፡፡ እኔም እንደ እግዚአብሔር ሰው ለማርያም ትልቅ ፍቅርና አክብሮት አለኝ፡፡ ብዙ ስለ እርሷ አጥንቻለሁ!..... አምብቤማለሁ!፡፡ የቅድስት ማርያምን ህይወት አስደናቂ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ታላቅ የጭምትነት..... የማስተዋል...... የንፅህናን ኑሮ ኖራለች፡፡ ነገር ግን "ከቅድስት ማርያም የህይወት ምሳሌነት ምን ያህል ተምረናል?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስቸጋሪ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም ነው መንፈስ ቅዱስ ባነሳሳኝ መሰረት ይህንን መፀሀፍ ለመፃፍ የተነሳሁት፡፡

አስቀድሜ ለአንባቢው ለእርሶ ቃል ልግባሎት!፡፡ በዚህ መፀሀፍ ውስጥ የእርሶን እምነት የሚያጣጥል ወይም የሚቃወም አንድም ነገር

አያገኙበትም፡፡ አርቶዶክስ ቢሆኑ ካቶሊክ ወይም ፕሮቴስታንት ለህይወቶ የሚጠቅም ትምህርት እንጂ አንድም የእርሶን እምነት የሚተናኮል ነገር በመፀሀፉ ውስጥ አያዩም፡፡ ምክንያቱም በመፀሀፉ ውስጥ የተነሱት ሀሳቦች ህይወታችንን ለማሳመር የሚጠቅሙ ቁምነገሮች እንጂ የዶክትሪን ጉዳዮች አይደሉም፡፡ የቅድስት ማርያምን ህይወት እያየን ለእኛ ህይወት የሚጠቅሙንን 40 የጥበብ እንቁዎች እንለቅማለን፤ ገንዘባችንም እናደርጋቸዋለን፡፡ ዘና ብለው በፍቅር ያንብቡ!፡፡

በመፀሀፍ ቅዱሳችን ውስጥ መደነቅ ያለባቸው ሴቶች ሲደነቁ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ለነብዩ ኤልሳ ማረፍያ ያዘጋጀችለት ሴት "ታላቅ ሴት" ተብላ ተደንቃለች (2ኛ ነገ 4፡8)፡፡ እንደዚሁም አቢጊያ ስለተባለችው አስቀድሞ የናባል ሚስት ቆይቶም የዳዊት ስለሆነችው ሴት "የሴቲቱም አእምሮ ታላቅ መልክዋም የተዋበ ነበረ" ተብሎ ተፅፎላታል (1ኛ ሳሙ 25፡3)፡፡ ስለ ታላቅ አእምሮዋም ከጥፋት ያዳነችው ዳዊት ሲናገር "ወደ ደም እንዳልሔድ፣ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን!" ብሏት ነበር (1ኛ ሳሙ 25፡33)፡፡

እንግዲህ የአቢጊያ አእምሮ "ታላቅ" ከተባለ ከአቢጊያ በብዙ የምትበልጠው የቅድስት ማርያም አእምሮ "ታላቅ" ቢባል ማን "ይበዛባታል" ይላል?፡፡ ለዚህም ነው የቅድስት ማርያምን ድንቅ ህይወት የምናይበትን ይህንን መፀሀፍ "የማርያም ታላቅ አእምሮ" ወይም "The Great Mind of Mary" ያልኩት፡፡ በማርያም ህይወት የታየው መልካም ነገር ሁሉ የተባረከ አእምሮዋ ውጤት ነውና!፡፡

አእምሮ (Mind) እውቀታችን..... ስሜታችን...... ሀሳባችን...... የሚገኙበት ስፍራ ነው (It is the department of our Intellect, Emotions and Thoughts)፡፡ አእምሮ አንጎል (Brain) አይደለም፡፡ አንጎል የጭንቅላታችን አጥንት ቢነሳ የሚታየው ሴሬብረም.... ሰሬቤለም.... ፖንስ..... ሜዱላ.... እያልን የምንከፋፍለው የሰውነታችን ክፍል ነው፡፡ አእምሮ ግን ያለው እዛው አንጎል ውስጥ ቢሆንም የማይዳሰስ፣ የማይነካ የነፍሳችን (Soul) ክፍል ነው፡፡ በተጨማሪም ብዙ ጊዜ "ልቤ ንፁህ ነው"..... "ልቤ ፈራ" እያልን የምናነሳው "ልብ" ደግሞ በደረታችን በግራ በኩል ያለው ደም

የሚረጭ ጡንቸኛ የሰውነት ክፍል ሳይሆን በአውቅናችን ስር ያልሆነውን....... ከህፃንነታችን ጀምሮ ብዙ ታሪክ ያጠራቀመውን ስውር አእምሮአችንን (Subconscious Mind) ነው፡፡

እንግዲህ የማርያም የተባረከ አእምሮዋ ውጤት የሆነውን ድንቅ ህይወቷን እያየን አርባ ትምህርቶችን እናያለን፡፡ እዚህ ጋ ልብ እንድንል የምፈልገው ነገር የህይወታችን ዋነኛ መመዘኛችን (Standard) የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት ነው፡፡ የመጨረሻው የህይወት ደረጃ በእርሱ ታይቷል፡፡ ለእርሱ አገልጋዮች የሆኑት እነ ሐዋርያው ጳውሎስ "እኔ እርሱን (ኢየሱስን) እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ነበር የሚሉት (1ኛ ቆሮ 11፡1)፡፡ በኢየሱስ አምላክነት የማያምኑ ምሁራን እንኳን "የመጨረሻው የላቀ የህልውና መደምደሚያ (The highest level of consciousness)" ብለውታል...... ኢየሱስን!፡፡ ለሁላችን ምሳሌ እርሱ የህይወት ጌታ ኢየሱስ ነው፡፡ ለዚህም ነው "ቅድስት ማርያም እግዚአብሔርን በመምሰል ያሳየቻቸው 40 የጥበብ እንቁዎች" ያልኩት!፡፡

ብዙ ጊዜ በመድረኮቻችን ላይ ስለ ሳራ እንሰብካለን!...... ስለ ርብቃ እናስተምራለን!........ ራሔልን እናነሳሳታለን!........ ሀናን ምሳሌ እናደርጋለን!...... በአስቴር እንደነቃለን!....... በሩት እንገረማለን!....... በአቢጊያ ራሳችንን እንነቀንቃለን!፡፡ ደግሞም እነ ሊዲያ...... ዮሐና...... ሶስና...... መግደላዊት ማርያም የምናስተምረውን ቁም ነገር ማሳያ ተደርገው ይነሳሉ፡፡ ልክ እንደዚሁ በማንነቷም በስራዋም ከነዚህ ሁሉ የምትልቀውን ቅድስት ማርያምን አንስተን ከህይወቷ ምሳሌነት መማር ተገቢና አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህም ዛሬ እኔ በዚህ መፀሀፍ የማርያምን ህይወት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ስገልጥ... "ነገሩ እንዴት ነው? ወዴት እየሔድክ ነው?" የሚለኝ አንድም ሰው እንደማይኖር ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

መቼም የሀበሻው ህዝብ ለእኔ መልካም ህዝብ ነው፡፡ ከጥፋቱ ይልቅ የሚታየኝ መልካምነቱ........ ደግነቱ ነው፡፡ ቤቱ እንግዳ ሲገባ "ካልበላህ!....... ካልጠጣህ!....... በሞቴ!" እያለ የሚሽቆጠቆጥ ህዝብ ነው፡፡ ሀዘን ሲመጣ ቤቱን ጥሎ፣ ተሰብስቦ የሚያፅናና ሩህሩህ ህዝብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስርግም ሲሆን ያለውን አዋጥቶ እንደ ራሱ ልጅ የሚድር ደግ ህዝብ ነው፡፡ ደግሞም

ጨዋ ነው ሀበሻ!:: የደርግ መንግስት ወድቆ ለጥቂት ቀናት በአገሪቱ መንግስት ባልነበረበት ጊዜ ህዝቡ እየዘለለ ወደ ሌላ ሰው ግቢ እየገባ አልዘረፈም:: ያ ጊዜ በሰላም ማለፉ የህዝቡን ጨዋነት የሚያሳይ ነው::

የሀበሻው ህዝብ ታላቁን ያከብራል:: በየቋንቋው "አባዬ!.... እማዬ!.... ጋሽዬ!...... እትዬ!" እያለ ታላላቆቹን ያቆላምጣል:: የራሱ የሆነ ወግና ስርአትም አለው......... ሀበሻው! :: እግዚአብሔርን ይፈራል!...... ያከብርማል!:: "ገዝቼሀለሁ!" ከተባለ መቼ ንቅንቅ ይላል!:: ደግሞም ጀግና ህዝብ ነው ሀበሻው....... ለማን ቅኝ ተገዛና ?!:: የብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ህብር..... የብዙ ቋንቋዎች ባለቤት የሆነ ታላቅ ህዝብ ነው:: ተከባብሮ፣ ተቻችሎ መኖርን ያውቃል::

እኔም በዚህ መፀሀፍ ለማድረግ የሞከርኩት በቅድስት ማርያም ምሳሌነት የህዝባችንን መልካምነት የሚጨምር..... አስተሳሰቡን የሚያሳድግ..... አመለካከቱን የበለጠ የሚያቃና ጥበብን መጨመር ነው:: ምን ያህል ተሳክቶልኝ እንደሆን አላውቅም:: በጣም ጥሩ ከሆነ እግዚአብሔር ስለረዳኝ ነው:: ከጠበቁት በታች ከሆነ ደግሞ ድካሙ ከእኔ ነው:: ይህንን መፀሀፍ ሲያነቡ የእግዚአብሔር በረከት በእርሶ ላይ እንዲሆን ፀሎቴ ነው::

# የጥበብ እንቁ 1

## ራስን በልዩነት መቀበል !

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ለቅድስት ማርያም ካመጣላት መልዕክት መሀል..... "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" የሚል ይገኝበታል (ሉቃስ 1:28)፡፡ ይህን ከልቧ ያደመጠችው ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ዘንድ በሔደች ጊዜ ደግሞ ኤልሳቤጥም ከመልአኩ ገብርኤል ጋ የተመካከረች ይመስል ይህንኑ ደግማላታለች...... "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ!" ብላ (ሉቃስ 1:42)፡፡ መንፈስ ቅዱስ በሁለቱም መልከተኛነት የነገራት የተባረከች መሆንዋን ብቻ ሳይሆን "ልዩ" መሆንዋንም ነው...... ለማርያም፡፡ እርሷም ይህን "ልዩ" የመሆን ፀጋን በደስታ ተቀብላዋለች፡፡ ሌላ ማንንም ለመሆን አልጣረችም፡፡ ማርያም.... ማርያምነቷን ተቀብላ..... ማርያም ሆና ኖረች!፡፡

ምንም እንኳን የቅድስት ማርያም "ልዩ" መሆን የላቀ ትርጉም ቢኖረውም እያንዳንዱ ሰው ደግሞ በራሱ መንገድ ልዩ ነው፡፡ ሁላችንም የአዳም ዘር እንሁን እንጂ በፋብሪካ እንደተመረተ ሳሙና አንድ አይነት አይደለንም፡፡ ከእርሶ የጣት አሻራ (Finger Print) ጋር አንድ አይነት የሆነ የጣት አሻራ ያለው ሰው በምድር ላይ የለም፡፡ ከእርሶ ራስ ላይ አንድ ፀጉር ተወስዶ መለያዎ የሆነው DNA ቢጠና ከየትኛውም ሰው ጋ አንድ አይነት ሆኖ አይገኝም፡፡ ስለዚህ እርሶ አንድ እርሶ ነዎት..... በዚህ ዩኒቨርስ የተገኙ ልዩ ሰው!፡፡

እግዚአብሔር አምላክ ለእያንዳንዳችን የተለያየ ቁመና ፣ መልክ፣ ችሎታ...... ሰጥቷል፡፡ ታዲያ ሰው ከአምላኩ በተሰጠው ልዩ ስጦታ ደስ ሊለው ይገባል፡፡ ራስን መቀበል (Self acceptance) ከዚህ ይጀምራል፡፡ አንድ ጊዜ በአሜሪካ..... በአንዱ ከተማ..... አንዲት ወጣት እያነባች ችግሯን አዋየችኝ፡፡ ችግሯ ...... "መወፈር አቃተኝ!".... የሚል ነበር፡፡ እያለቀሰች "ሱሪ ስለብስ አያምርብኝም፡፡ ለመወፈር ብዙ ፀለይኩ!፣ እግዚአብሔር ግን አልሰማ አለኝ፡፡ ለመሆኑ እርሱ እኔን ይወደኛል?" ነው ያለችኝ፡፡ ታዲያ እኔ የእርሷን እንባ እያየሁ..... እንደርሷ ቀጭን ለመሆን መከራቸውን የሚያዩ ብዙ ሴቶችን

አያስብኩ.... በህሳብ ነጎድኩ፡፡ እርሷ ስለ ቅጥነቷ ስታለቅስ ቢያዩአት ምን ይሉ ይሆን ብዬ አሰብኩ!፡፡

አንዳንድ ጊዜ በዙሪያችን ስናስተውል አጭሩ ሰው ቁመቱ በማጠሩ ሲያማርር እናገኘዋለን፡፡ ረዥሙ ደግሞ...... "ኧረ የኔስ በዛ! እንደው አንቀዋሎ ነው የፈጠረኝ!" ይላል፡፡ ወፈር ያለችው እንዴት እንደምትከሳ ቀን ከሌሊት ታስባለች፤ ዳይት እየቀያየረች ትሞክራለች!፡፡ ቀጭኗ ደግሞ እንዴት 'ወፈር' እንደምትል ነው የምታሰላስለው፤ "አንድ ቀን አይቀርም..... ጂንሴን አሞላዋለሁ!" እያለች ትዝታለች፡፡

እንደኛ ጠየም.... ጠቆር ያሉ አንዳንድ ሰዎች ነጣ ለማለት በተለያዩ ሳሙናዎች ይታጠባሉ፤ ያነጣሉ ብለው የሚያስቧቸውን ቅባቶችንም ይቀባሉ፡፡አንዳንዶቹ ነጮች ደግሞ ንጣታቸው እያነጫነጫቸው ፀሀይ ብቅ ባለች ቁጥር አሸዋ ላይ ይሰጣሉ፡፡ ራሰ በራነት የሚያሰጋቸው ወንዶች ፀጉራቸውን ወደ ፊት ይጎትታሉ፤ ጎፈሬዎቹ ደግሞ ሙልጭ አድርገው ይላጩታል! ፡፡ የወንዶች ቁጥር አንድ የጭንቀት ምክንያት ራሰ በራነት ነው ይባላል፡፡ እርስዎ ግን ይህ ስጋት ካለዎት አይጨነቁ!፤ ፀጉር መሔድ ካለበት ይሒድ እንግዲህ!፤ ደግሞስ ምንም ያልተማረውን ሁሉ ምሁር የሚያስመስል ራሰ በራነት አይደለምን?!፡፡

በጥሩ ጤንነት፣ የአካል ብቃት፣ ትክክለኛ ክብደት.... ሰውነትን መጠበቅ ተገቢ ነው፡፡ ያፈሳል...... ያንጠባጥባል...... ብለን እንደ መኖርያ ቤት የምንቀይረው መኖርያ ሰውነት የለንም፡፡ ከዚህ አለም የምንለይበት ጊዜ ደርሶ እስኪፈርስ ድረስ ይህ አካል አብሮን ይኖራል፡፡ ስለዚህም ሰውነታችንን በጥሩ ሁኔታ መንከባከቡ ትክክል ነው፡፡ ከዚያ ያለፈ ጭንቀት ግን አስፈላጊ አይደለም፡፡

ስለ ሰውነትሽ መወፈርና መክሳት ከመጠን ያለፈ አትጨነቂ፡፡ የመፅሔት ሽፋን ላይ ወይም በፊልም ያየሻቸውን ሴቶች መምሰል የለብሽም፡፡ እነርሱም እኮ ለፊልሙ ወይም ለፎቶው ብለው ለሶስት ወራት በእራታቸው ላይ ጨክነው ነው ያንን የመሰሉት፡፡ ከአመት በኋላ ብታገኚያቸው ፎቷቸውን አይመስሉም፡፡ በዚህ ጉዳይ ከልክ ያለፈ መጨነቅ የአመጋገብ መቃወስን

(Eating Disorders) ሊያመጣ ይችላል:: ከነዚህ አንደኛው አኖሬክስያ ነርቮሳ (Anorexia Nervosa) ይባላል፡፡ ይህ ችግር ያለባቸው ሰዎች ከመወፈር ፍርሀት የተነሳ.... የሰውነታቸው ቅርፅም እንዳይበላሽ ከመስጋት የተነሳ.... የምግብ ፍላጎታቸውን ያጣሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በጣም ዝቅተኛ ክብደት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ችግር ከከፋ ለሞትም ሊዳርግ ይችላል፡፡

ሌላው የአመጋገብ መቃወስ ደግሞ ቡሊሚያ ነርቮሳ (Bulimia Nervosa) ይሰኛል፡፡ ይህ ችግር ያለባቸው ሰዎች ምግባቸውን..... ሳንድዊቻቸውን..... ክትፎአቸውን..... ፍርፍራቸውን በርከት አድርገው በሚገባ ይበላሉ፡፡ ጥቂት ይቆዩና ግን የመወፈር ፍርሀት ሲመጣባቸው ጣታቸውን ወደ ጉሮሯቸው እየከተቱ ያስወጡታል፡፡ ወይም የሚያስቀምጥ መድሀኒት ካላቸው ይወስዱታል፡፡ ይህም ብዙ ችግሮችን ሊያመጣ ይችላል፡፡

እርስዎ ግን ራስዎን ይቀበሉት፡፡ ውብ እኮ ነዎት!፤ እንዴት አወቅህ?፤ አዎ እርሶን አላውቆት ይሆናል፡፡ በጥበቡ የሰራዎትን እግዚአብሔርን ግን አውቀዋለሁ!፡፡ እርሱ አንድም ደረጃውን ያልጠበቀ ስራ ሰርቶ አያውቅም!፡፡ ስራው ሁሉ ውብ ነው!፤ እርሶ ደግሞ የእርሱ ስራ ነዎት፡፡ አንዳንድ ሰዎች "ከዝንጀሮ መሰል እንስሳ ነው የተገኘነው" ብለው ያምናሉ፡፡ የእነርሱን ህገ መንግስታዊ መብታቸውን አከብርላቸዋለሁ፡፡ እርስዎና እኔ ግን የእግዚአብሔር የእጅ ስራዎች ነን!፡፡

ራስን መቀበል (Self acceptance) በራስ መተማመንን (Self confidence) ይጨምራል፡፡ በራስ መተማመን ሲጨምር ደግሞ ለራስ ትክክለኛ ስፍራ መስጠትን (Self steem) ይጨምራል፡፡ በአለማችን ቶክ ሾው ከሚያዘጋጁ ሰዎች ኦፕራ ዊንፍሪን የሚስተካከላት ያለ አይመስለኝም፡፡ ታዲያ የእርሷ ፕሮግራም ኢጋጥሞኝ ከተከታተልኩኝ የሚያስገርመኝ ነገር ኦፕራ ያላት በራስ መተማመን ነው፡፡ የትኛውንም ምሁር፣...... ባለፀጋ፣....... ባለስልጣን፣........ ፕሮግራሟ ላይ ትጋብዝ በማንም ፊት አትሸማቀቅም..... ኦፕራ፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው? ራስዋን ሙሉ ለሙሉ የተቀበለች ሰው ስለሆነች!፡፡ እርስዎም ራስዎን መቶ ፐርሰንት ይቀበሉ፡፡ መስተዋት ፊት ቆመው ከራሳቸው ጋ እንደሚጣሉ ሰዎች አይሁኑ፡፡ የሰው አስተሳሰቡ እንጂ

የቁመቱ ማጠር ወይም መርዘም....... የቆዳው መንጣት ወይም መጥቆር.... ልዩነት አያመጣም::

ራስን መቀበል ታዲያ የተገኘንበትን ቤተሰብ፣ የዘር ሀረግ፣ ጎሳ፣ ብሔር እንዲሁም ህዝብ በደስታ መቀበልን ይጨምራል:: አንድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሜዲካል ፋኩልቲ የሚያስተምሩ ምሁር ነበሩ:: የእኚህ ታዋቂ ምሁር አባት ደግሞ የሚኖሩት ድሬዳዋ ነበር:: አባትየው ጠጅ ይወዳሉ:: እስኪሰክሩ ይጠጡና ድሬዳዋ አሸዋው ላይ ይተኛሉ:: ታዲያ አንድ ጊዜ ከአሜሪካ ጉብኝት የሚያደርጉ አስተማሪዎች (ነጮች) ይመጡና ከምሁሩ ጋ ወደ ድሬዳዋ ይሔዳሉ:: በመኪና ዞር ዞር ሲሉ ምሁሩ ወላጅ አባታቸውን ያዩአቸዋል:: እንደ ተለመደው ሰክረው ጋደም ብለዋል...... አባትየው..... አሸዋው ላይ::

ምሁሩ እንዳላየ ሆነው አላለፉም..... ሹፌሩ መኪናውን እንዲያቆም አዘዙ:: ፈረንጆቹንም "ውረዱ! የማስተዋውቃችሁ ሰው አለ" አሉአቸው:: ከዚያም በቀጥታ ጠጥተው ወደ ተኙት አባታቸው በመሔድ "ይህንን ሰው አያችሁት?" አሉ:: ፈረንጆቹ ግራ በመጋባት ራሳቸውን በአዎንታ ነቀነቁ:: "ይህ ሰው የምወደው አባቴ ነው! እርሱ ነው ያሳደገኝ!" አሉአቸው:: እንግዶቹ ለምሁሩ የነበራቸው አክብሮት በጣም ጨመረ፤ አደነቋቸው!:: ይህ ራስን የመቀበል ውጤት ነው::

በውጪው አለም ለሚኖሩ ወገኖቻችን የቆዳ ቀለምና ማንነት አስቸጋሪ ሁኔታዎችን የሚፈጥርበት ጊዜ አለ:: ጥቁር.... ነጭ.... ቢጫ እየተባለ!:: ታዲያ እርስዎ የትም አገር ቢሔዱ..... ቀና ይበሉ:: የራስዎን ማንነት ይቀበሉ:: የሌሎችንም ማንነት ያክብሩ:: ይህም በራስ መተማመኖን ይጨምርሎታል:: ማርያም ማርያምነቷን ተቀብላ ማርያም ሆና እንደኖረች አንቺም አንቺነትሽን ተቀብለሽ አንቺን ሆነሽ ኑሪ!፤ አንተም እንደዚያው!::

# የጥበብ እንቁ 2

## ለህይወት ጥሪ መኖር!

ቅድስት ማርያም ወደዚህ አለም የመጣችው የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ፀንሳ ለመውለድ፣ ወልዳም ለማሳደግ፣ አሳድጋም ለአገልግሎት እድሜው ለማብቃት ነበር፡፡ እርሷም ይህን የተፈጠረችበትን አላማ ጠንቅቃ ተረድታለች፡፡ እግዚአብሔር መልአኩ ገብርኤልን ልኮ አስረግጦላታልና!፡፡ ጥሪዋን ካወቀች በኋላ ታዲያ ማርያም ሌላ ነገር ለመሆን አልሞከረችም፡፡ እስቲ ተነስቼ የተዋጣላት ነጋዴ ልሁን አላለችም፤ የባህል ሀኪም ለመሆንም አልሞከረችም፤ ወይም የልምድ አዋላጅ ለመሆን አልጣረችም፡፡ ጥሪዋ ሙሉ ጊዜዋን የሚጠይቅ ነበርና በዚያ የህይወት ጥሪዋ ላይ በሙሉ ልብዋ፣ በመሉ ሀሳብዋ፣ በሙሉ ሀይልዋ አተኮረች፡፡ ህይወቷን ሰጠች!፡፡

እያንዳንዱ ሰው ወደዚህ አለም የመጣበት አንድ ዋነኛ አላማ አለው፡፡ ያ ሰው ከትዳር ውጪ ተፀንሶ የተወለደ ቢሆን እንኳን..... ቤተሰብ የማይፈልገው ልጅ ቢሆን እንኳን...... ወይም በአስተዳደጉ "ይድፋህ!" "አይለፍልህ!" እየተባለ ያደገ ቢሆን እንኳን በፈጣሪው ዘንድ ግን የታወቀ፣ የተፈለገ፣ የተወደደ ነው፡፡ በእግዚአብሔር በአምላኩ አንድ የህይወት አላማ ተሰንቆለት ነው ወደዚች ምድር ያቀናው፡፡ ያ አላማ ግን ሊፈፀም ወይም ላይፈፀም ይችላል፡፡

የተሰጠው አላማ እንዲፈፀም ከፈለገ ያ ሰው ራሱን መፈለግ አለበት፡፡ "ውስጤ ያለው ስጦታ ምንድን ነው? የተሰጠኝ ታለንት ምንድን ነው?" ብሎ መጠየቀ...... መፈለግ አለበት!፡፡ ብዙዎቻችን ህፃን ሳለን "ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ" ተብለን ስንጠየቅ ዶክተር፣ ፓይለት ወይም ኢንጂነር እንል ነበር፡፡ ይህንን የምንልበትም ምክንያት የዚያ አይነት ሙያ ያላቸው ሰዎች በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው ከበሬታና የኑሮ ደረጃ በጨቅላ

አእምሮአችን ተቀርፆ ስለነበር ነው፡፡ ካደግንም በኋላ በቤተሰብ ግፊት መሆን ያልነበረብንን የሆንን ብዙዎች ነን፡፡ ምርጥ ተዋናይ የሚወጣው ሰው ወታደር ሆኗል፡፡ ልዩ የፖለቲካ ሰው መሆን የነበረበት ሰው ሐኪም ሆኖ ክሊኒክ ተቀምጧል፡፡ ልዩ ኢንቬስተር..... የስራ ፈጠራ ባለሙያ መሆን የነበረበት ሰው ደግሞ ቄስ ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ በሰዎቹ ዘንድ እርካታ ማጣትን፣ በሙያቸውም የብቃት ማነስን ያስከትላል፡፡

ምንም ዘመኑ ቢያልፍ ታዲያ በየትኛውም ዕድሜ ራስን መፈለግ ይቻላል፡፡ "ስጦታዬ ምንድን ነው? በጣም የሚያነሳሳኝ (Passionate የሚያደርገኝ) ምንድን ነው?" ብሎ መጠየቅ!፤ በዚያም አቅጣጫ መሔድ!፡፡ "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ስራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" ይላል ቃሉ (ኤፌ 2፡10)፡፡ አስቀድሞ የተዘጋጀ ነገር አለ ማለት ነው፡፡ በህይወት አጋጣሚ ያንድ ሙያ ባለቤት ብንሆን እንኳን ያንን ሙያ ሳንተው ዋናኛውን ነገር ማድረግ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ሰአሊ መሆን የነበረበትና በህይወት አጋጣሚ አስተማሪ የሆነ ሰው ማስተማሩን ሳይተው በስዕሉ መጠበብ ይችላል፡፡

እኔ አስራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ከትምህርት ቤቱ ልዩ ውጤት ሳመጣ ያዩ አስተማሪዎቼ ሽልማት ሸለሙኝና "አንተ የህክምና ዶክተር መሆን ነው ያለብህ አሉኝ"፤ በቃ! ዶክተር ለመሆን ወሰንኩ፡፡ በዚሁም መሰረት 12ኛ ክፍል ስጨርስ በዘመኑ ይሞላ የነበረው ፎርም ላይ ህክምናን ሞላሁ፡፡ ለ ስድስት አመታት ህክምና ተምሬ የህክምና ዶክተር ሆንኩ!፡፡ አጋጣሚ ሆኖ የኔ ፕሮፌሽን ከጥሪዬ ብዙ አልራቀም፡፡ እኔ የሰዎችን ስነ-ልቦና ወደ ማጥናት አደላለሁ፤ መንፈሳዊው አለም ደግሞ ከቁሳዊው አለም ይልቅ ይማርከኛል፡፡ ስለዚህ ጥሪዬን ካወቅሁ በኋላ ለጥሪዬ የበለጠ የሚረዱኝን ትምህርቶች ጨማመርኩ፡፡ አሁን የእግዚአብሔር ሚኒስተር ነኝ፤ የተፈጠርኩበትን አላማ አግኝቼዋለሁ!፤ ፍላጎቴ ፣ትምህርቶቼ ሁሉ ከጥሪዬ ጋ ተስማምተውልኛል፡፡

አብሮኝ የተማረ ዶ/ር በእውቀቱ ስዩም የሚባል ወዳጅ አለኝ፡፡ ገና ከዩኒቨርሲቲ ሳንወጣ ዶ/ር በእውቀቱ የሚያስበው ስለ ንግድ ነበር፡፡ ታዲያ በተመረቅን በ 6 ወሩ እርሱ ከአጎቱ ጋ ክሊኒክ ከፍቶ አንዳንዶቻችንን ቀጠረን፡፡ በፍጥነትም በቢዝነሱ አለም እያደገ መጣና የመድሀኒትና የህክምና

ኢቃዎች አስመጪ ሆነ፡፡ ዛሬ የእርሱ የሆነው ድርጅት 'ላቦራ ኢንተርናሽናል' ተብሎ ይጠራል፡፡ ከታላላቅ ካምፓኒዎች አንዱ ነው፡፡ ዶ/ር በእውቀቱ በእርግጥም ራሱን ፈልጎ አግኝቶታል፡፡

የእርሶ የህይወት ጥሪ ምንድን ነው? ለምንድነው በዚህ ምድር የተገኙት? ውስጥዎ ምን ስጦታ አለ? የሚያነሳሳዎ ምንድን ነው? ልብዎ ምን ይመኛል፡፡ "በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ የልብህን መሻት ይሰጥሀል" ይላል ቃሉ (መዝ (37):4) ፡፡ ወደ ህይወት ጥሪዎ አቅጣጫዎን ያስተካክሉ፡፡ ይህ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል፤ ለጊዜው ብዙ ገንዘብ ላያገኙ ይችላሉ፤ በእርግጠኛነት ግን እርካታን ያገኛሉ!፤ በዘመንዎ ፍፃሜም አይፀፀቱም!፤ ለትውልድ ጠቃሚ ሆነው ያልፋሉና!፡፡

አንዳንድ ሰዎችን ሳስብ ጥሪያቸውን ስተው ቢሆን እንዴት እንሆን ነበር ብዬ እቸገራለሁ፡፡ ለምሳሌ አይዛክ ኒውተን በስህተት ልብስ ሰፊ ቢሆን ኖሮስ?..... ግራቪቲን ማን ያስረዳን ነበር?፤ ዊልያም ሼክስፒር የባዮሎጂ አስተማሪ ቢሆን ኖሮስ?....... ስነ-ፅሁፍ የቁጋ ይገኝ ነበር?፤ አሌክሳንደር ፍሌሚንግ ገበሬ ቢሆን ኖሮስ...... ኢንፌክሽኑ እንዴት ያደርገን ነበር?፤ ቤትሆቨን ሐኪም ሆኖስ ቢሆን........ ያንን ሙዚቃ ማን ኮምፖዝ ያደርገው ነበር?፤ ግራሃምቤል ስፖርተኛ ቢሆንስ........... የስልኩ ጉዳይ እንዴት ይሆን ነበር?፤ ቢሊ ግራሃም ነጋዴ ሆነው ቢሆንስ?...... ወንጌል በዚያ ስፋት እንዴት ይሰበክ ነበር?፡፡

ደግሞስ ሀዲስ አለማየሁ ሙዚቀኛ ቢሆኑ....... ያንን ተወዳዳሪ የሌለው ልብ ወለድ ማን ይፅፈው ነበር?፤....... ውብሸት ወርቅአለማሁ ፓይለት ሆነው ቢሆን....... የማስታወቅያውን ኢንዱስትሪ ፊር ቀዳጅ ሆኖ ማን ይመራው ነበር?፤......... ሀይሌ ገብረስላሴ ሰአሊ ቢሆን ኖሮ....... ስንት ወርቅ እናጣ ነበር?፤ .......... ሼህ አላሙዲ የዩኒቨርሲቲ መምህር ቢሆኑ....... ኢንቬስትመንቱ ምን ይውጠው ነበር?፤....... ጌትነት እንየው ሀኪም ሆኖ ቢሆን...... ቲያትሩና ግጥሙ እንዴት በጎደለ ነበር?፤...... አሰልጣኝ ሰውነት ቢሻው ሜካኒክ ቢሆኑ........ የኳሱ ብርሀን እንዴት ይፈነጥቅ ነበር?፤....... ቄስ በሊና ኢኮኖሚስት ቢሆኑስ........ አገራዊ ትንቢትን ማን ይነግረን ነበር?፡፡ እርሶም የህይወት ጥሪዎን ፈልገው ያግኙ......ትኩረቶን በዚያ ላይ ያድርጉ!

# የጥበብ እንቁ 3

## ለመማር ፈቃደኛ መሆን !

ቅድስት ማርያም ጥሪዋን እንደተረዳች ወዲያው የወሰደችው እርምጃ ወደ ኤልሳቤጥ መሔድ ነበር (ሉቃስ 1:39-41)። ኤልሳቤጥ ለብዙ ዘመን ልጅ ሳትወልድ ቆይታ በዚያ ጊዜ ከፀነሰች ስድስት ወር ሆኗታል። በዚህም ላይ ለማርያም ዘመዷ ነች!። የፀነሰችው ደግሞ ታላቅ ነብይ የሚሆነውን መጥምቁ ዮሐንስን ነው። ስለዚህ ኤልሳቤጥ ማርያምን ብዙ ነገር ልታስተምራት ትችላለች። የፀነሰች ሴት ስለ እርግዝና ጥሩ ትምህርት የምታገኘው ከእርሷ በፊት ከፀነሰች ሴት ነው። ብዙ ልምዷን ታካፍላታለች...... የቀደመችዋ..... ለአዲሷ። በመጀመርያዎቹ ወራት ስለሚያስቸግረው የጠዋት ማቅለሽለሽና ማስመለስ ትነግራታለች። "አይዞሽ! ትንሽ ጊዜ ነው ቢያስቸግርሽ ትላታለች"፤ ማድረግ ያለባትንም ትመክራታለች። ምንም እንኳን ቅድስት ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ የሔደችበት ምክንያት ከዚህም ያለፈ ቢሆንም ያቺ ወጣት ድንግል ብዙ ትምህርት ከኤልሳቤጥ እንደምታገኝ ጥያቄ የለውም።

የህይወት ጥሪያችንን በትክክል ካወቅን በኋላ በዚያው አቅጣጫ መማር ያለብንን መማር፣ ማንበብ ያለብንን ማንበብ አለብን። የሚያስፈልገንን እውቀት በትምህርት ቤት (Formal Education) ወይም ደግሞ ጥሩ አንባቢ በመሆን ልናገኘው እንችላለን። በተጠራንበት አቅጣጫ የሚገኝን እንድ ከእኛ የተሻለ እውቀትና ልምድ ያለውን ሰው አስተማሪያችን ፣ መካሪያችን (Mentor) ፣ አራሚያችን አድርገን መሾም ያስፈልገናል። የማናውቀውን ጠይቀን የምንረዳ ጥሩ አዳማጮችም መሆን አለብን።

በምድራችን ታሪክ ሰርተው ያለፉ እንደ ጳውሎስ ዓይነት ሰዎች በትምህርቱ አለም ብዙ ለመግፋት አልታደሉም ነበር። ሳይፈልጉ ቀርተው ሳይሆን አልተመቻቸላቸውም ነበርና ነው። ነገር ግን ያንን ለማካካስ

እነበቡ!፤ ተግተው እነበቡ!፤ ከማንበብ ብዛት አዋቂዎች ሆኑና በህብረተሰብ ተከበሩ፡፡ ልጅ ሆኜ በእሁድ ጠዋት የመዝናኛ ፕሮግራም ለጳውሎስ ኞኞ ቃለ መጠይቅ ሲደረግለት አስታውሳለሁ፡፡ ከተናገረው ውስጥ የማልረሳው "መፀሀፍ ማንበብ እወዳለሁ! እንደውም መፀሀፍ ካልያዝኩ እንቅልፍ አይወስደኝም" ያለውንና "የማላውቀውን ነገር እጠይቃለሁ፤ 'እንዴት ይህን አያውቅም' ብለው ይስቁብኛል ብዬ አልፈራም!፤ አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ የሰጡኝን ምግብ እንዴት እንደምበላው ካላወቅሁ ሆስተሷን ጠርቼ እጠይቃታለሁ" ብሎ ነበር፡፡

እኔ እንደታዘብኩት አንዳንድ ሰዎች ለመማር ፈፅሞ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ ማዳመጥ አይወዱም!፤ ሁሌ መናገር ብቻ ይፈልጋሉ፡፡ ከአንድ የሙያ ባለቤት ከሆነ ባለሙያ ጋ ሲገናኙ ጥያቄ እየጠየቁ አጋጣሚውን ተጠቅመው ብዙ እውቀት ማግኘት ሲችሉ እነርሱ ጭራሹኑ ለሙያው ባለቤት ስለ ሙያው ሊያስተምሩት ይወዳሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ማንበብ የሚባል ነገር አይወዱም፡፡ "ከነ እከሌ ገንዘብ መደበቅ ከፈለክ መፅሀፍ ውስጥ ሸሽገው" የተባለባቸው አይነት ናቸው፡፡ ሁሉም ነገር በፊልም ተሰርቶ እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ....... ባዮሎጂውም....... ፊዚክሱም ፊልም ሆኖ እስኪወጣ ይጠብቃሉ!፡፡ ለእነዚህ ሰዎች በእውቀት ማደግ አስቸጋሪ ነው፡፡

ማንበብ ግን መልካም ነው! ሁል ጊዜ ማንበብ መልካም ነው፤ የሚጠቅመውን እየመረጡ ማንበብ!፤ ደግሞ ጥያቄ መጠየቅ!....... ከዚያም ማዳመጥ!፡፡ እኔ ከአንድ የህግ ባለሙያ ጋ ከተገናኘሁ ጥያቄ ጣል እያደረኩ የህግ እውቀትን እቀስማለሁ፡፡ ኢኮኖሚስቱን ካገኘሁት እኔ ስለ ኢኮኖሚክስ የማውቃትን በእርሱ ፊት በማውራት ፋንታ እርሱን አዳምጣለሁ፡፡ እርሶም እንዲሁ ቢያደርጉ ጥሩ ነው፡፡ ምግብ ቤት ገብተው የተዘረዘረውን ሜኑ ካላወቁት አስተናጋጁን ጠርተው "ይሄ ምንድን ነው?" ብለው ይጠይቁ፡፡ ነውር የለውም!፡፡ ሁኔታዎች ከተመቻቹሎት ደግሞ ት/ቤት ጎራ ይበሉ.... ለትምህርት መቼም አይመሽም (It is never too late)!፡፡ ትምህርት ቤት መግባቱ ካልሆነ ግን ያንብቡ!፤ እንደውም ከትምህርት የጎደለውን ለማካካስ በትጋት...... በየቀኑ....... ያንብቡ!፡፡

# የጥበብ እንቁ 4

## ሞገስን ፊልን ማግኘት !

ለቅድስት ማርያም በመልአኩ ገብርኤል ከመጣላት መልካም የምስራች ውስጥ "ደስ ይበልሽ ፀጋ የሞላብሽ ሆይ...." የሚል ይገኝበታል (ሉቃ1:28):: ይህም በእንግሊዘኛው "Rejoyce, highly favored one…!" ነው የሚለው:: ይህም "ሞገስን ያገኘሽ" እንደ ማለት ነው:: ማርያም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሞገስ አግኝታ ነበር:: ይህም ተወዳጅነትን፣ ተቀባይነትን፣ ተደማጭነትን ያሳያል:: ሞገስ እጅግ ልዩ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው!፤ እግዚአብሔርም ለወደደው ይሰጠዋል::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ያጋጥሙናል:: ያለ ምክንያት እንወዳቸዋለን:: "ምን ላድርግለት?"፤ "ምን ላድርግላት?" ብለን እናስባለን:: እነርሱ ውለታ እንድናደርግላቸው ከጠየቁን በታላቅ ደስታ ነው የምናደርግላቸው:: እነርሱ መናገር ከጀመሩ በጥሞናና በአክብሮት በፍቅርም እንሰማቸዋለን:: አስተያየት ከሰጡ የሰጡት አስተያየት ብዙ የተለየ ባይሆንም እንኳን በአስተያየታቸው እንደነቃለን፤ እናጨበጭባለን!:: አብረውን ቢቆዩ ደስ ይለናል:: ስለ እነርሱ ለሰዎች መልካምን እናወራለን:: አንዳንዴ ራሳችን ተገርመን "ምንድነው ሚስጥሩ?" ብለን ልንጠይቅ እንችላለን:: ሚስጥሩ እነዚያ ሰዎች ሞገስ (Favor) አላቸው!፤ ሞገስ ተሰጥቷቸዋል!::

ሞገስ እጅግ አስደናቂ ነገር ነው:: በታሪክ ምናልባት ትልቁ የቁንጅና ውድድር የተካሔደው በንጉሱ በአርጤክስስ ቤተ-መንግስት ውስጥ ነበር:: በዚህ ውድድር ለንጉሱ ሚስት፣ ለግዛቱ ንግስት የምትሆን ሴት ትፈለግ ነበር:: ከመቶ ሀያ ሰባት ሀገሮች የመጡ ቆነጃጅት ተሳትፈዋል...... ውድድሩ ላይ:: ብዙዎቹ በድሎት ያደጉ፣ በሳውናና በስቲም ቆዳቸውን ያጠሩ፣ ጿሱ ቆመጠጠኝ፣ የእንጀራው ጠርዝ እጇን

ወጋኝ የሚሉ ናቸው። በእነርሱ መሐል ግን ለመወዳደር የገባች በድህነት ያደገች 'አስቴር' ወይም በአይሁድ ስሟ 'ሀደሳ' የምትባል ሴት ነበረች (መፅ አስቴር 2፡7)። እርሷ ቀን የለበሰችውን ቀሚስ ማታ አጥባ አድርቃ በማግስቱ የምትለብስ ሴት ናት። ውድድሩ ሲጀመር ግን ንጉሱ ብዙ ሴቶችን ካየ በኋላ አስቴር ላይ ፈዞ ቀረ!፤ ሌላ ሴት አታሳዩኝ አለ!፤ አስቴርን የምትወዳደር ሴት አልተፈጠረችም ብሎም አመነ። ስለዚህም በ 127 ሀገሮች ላይ ንግስት አደረጋት!፤ ሚስትም ሆነችው!። የአስቴር ሚስጥሯ ምን ነበር? ሞገስ ነበር!......... ፌቨር!።

ይህንን አስደናቂ ሞገስ የሚሰጥ ታዲያ እግዚአብሔር ነው። ደስ ላሰኘው ሰው ይሰጠዋል። ከአመፅ የሚርቅ፤....... ለድሀ አደጉ አባት ለመበለቲቱም ጧሪ የሚሆን፤........ በቅንነት የሚፈርድ ፤........ ማየት ለተሳነው 'አይን' መራመድ ላቃተውም 'እግር' የሚሆን፤....... ለተራበው እንጀራውን ለተጠማው ውሀውን የሚያካፍል....... እርሱ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኛል። እግዚአብሔር በሰው ደስ ሲለው ሞገስን ይሸልመዋል!።

ማርያም ይህንን ሞገስ ያገኘችው እንደ ሔኖክ አካሔዷን ከእግዚአብሔር ጋ ስላደረገች ነበር። ከብዙ ጥረት ይልቅ መልካሙ ሞገስ ስኬትን ያመጣል። ይህን ሞገስ ለማግኘት ታዲያ አካሔድን እርሱ እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ከባድ አይደለም። እግዚአብሔርን መፈለግ፤....... እርሱን ማክበር፤...... እርሱን መፍራት፤........ ከማይወዳቸው ነገሮች መራቅ ብቻ ነው።ወደ እርሱ መቅረቢያ መንገድ ደግሞ አለው። እርሱም ከዘላለም የነበረው፣ በስጋ ከድንግል ማርያም የተወለደው፣ ለእርሶና ለእኔ ሐጢያት ስርየት በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በእርሱ መጋረጃው ተቀዷል!።

ወገኔ ያገሬ ልጅ ሆይ! ወደ ፈጣሪዎ ወደ እግዚአብሔር ይጠጉ። አካሔድዎን ከእርሱ ጋ ያድርጉ። እርሱም ሞገስን ይሰጦታል!፤ ሞገስ ደግሞ መልካም ምኞትዎን ሁሉ ያስወርሶታል!።

## የጥበብ እንቁ 5

# ከቅንአትና ከውድድር መራቅ !

የቅድስት ማርያም ባህሪዋ ድንቅ ነበር:: ልዩ ካራክተር ነበራት!:: ከሚያስደንቀው ካራክተሯ አንዱ ደግሞ ከውድድርና ከቅናት ነፃ መሆኗ ነበር:: እራሷን ከማንም ጋ አላወዳደረችም:: ልጇ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲያገለግል እየተከተሉት በገንዘባቸው የሚያግዙት ሴቶች እንደነበሩ ይታወቃል:: መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ ሶስና የሚባሉ! (ሉቃ 8:2):: እርሱም እንደ እህቶቹ ያቀርባቸው ነበር:: በተለይ ከትልቅ የሰይጣን እስራር የታደጋት መግደላዊት ማርያም በጣም ቅርቡ ነበረች:: እርሱም በመለኮታዊ ፍቅሩ ይወዳት...... ይራራላትም ነበር:: ጌታ ከሙታን ሲነሳ እንኳን በመጀመርያ የታየው ለመግደላዊት ማርያም ነው (ማር 16:9)::ታዲያ ቅድስት ማርያም በዚህ ቅር አላላትም፤ "እንዴት እኔ እያለሁ?" አትልም ነበር:: እርሷ ራሷን ከማንም ጋ አታወዳድርም ነበርና ቅናትን አታውቅም!:: ማድረግ ያለባትን አድርጋ ዞር ትላለች::

በምድር ላይ ስንኖር በጣም መጠንቀቅ ያለብን ከውድድርና ከቅንአት ነው:: ራሳችንን ማወዳደር ያለብን ከራሳችን ጋ ብቻ ነው:: "ምን ያህል መስራት እችል ነበር?..... ምን ያህልስ ሰራሁ?"......ብለን! :: ከሰው ጋ ከተወዳደርን ግን ህይወታችን አሳዛኝ (Miserable) ነው የሚሆነው:: የእኔ የሆነ የሌላ አይሆንም፤ የሌላው ደግሞ ለእኔ አይሆንም:: ወጣቱ ሳኦል በወጣትነቱ ወደ ሳሙኤል ግብዣ ሲመጣ በ 30 ሰዎች ተቀድሞ ነበር:: ነገር ግን ለእርሱ የተቀመጠለትን ድርሻ ማንም አልበላበትም:: የተሰጠውም መቀመጫ ወንበር.... የመርፈቂያው ራስ (The head of the table) ላይ ነበር (1ኛ ሳሙ 9:17-25):: ልክ እንደዚሁ ለእርሶ የተዘጋጀውን በረከት ማንም ሊወስድቦት አይችልም!፤ ለእርሶ የተዘጋጀው ወንበር ላይም ማንም መቀመጥ አይችልም፤ ቢቀመጥ እንኳን አጅግ ስለሚቆረቁረው ብዙ ሳይቆይ ይነሳል::

መቼም የኑሮ ውድድር ነገር ሲነሳ ትዝ የሚሉኝ ዋሺንግተን ዲሲ አካባቢ የሚኖሩ አንዳንዶቹ ሀበሻ ዘመዶቼ ናቸው:: "አንዳንዶቹ" ነው ያልኩት! :: ከጓደኛማቾቹ መሀል አንዱ ውድ መኪና ከገዛ ሌሎቹም በተከታታይ ይገዛሉ....... ያለ ፕሮግራማቸው!:: ከመሀላቸው አንዱ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም ከገዛ እንዲሁ ሌሎቹም ይከተላሉ:: እርስ በርስ ይወዳደራሉ:: እዛ አካባቢ በጣም የሚዘንጡት ሀበሾቹ ናቸው:: የአገሬው ሰዎች እንደሁ የሚመቻቸውን ጂንስና ስኒከር ካገኙ ስለ ልብስ ብዙም አያስቡም:: የኛዎቹ ግን ዝንጥ ይላሉ!:: በተለይ ሰርግ ላይ የዲዛይነር ልብስ ሾው የሚያሳዩ ነው የሚመስሉት:: መቼም ፕሬዚደንት ኦባማ በሊሞዚናቸው ሲያልፉ ሀበሻውን እያዩ ሳያደንቁ አይቀሩም::

ወገኖቼ ይልበሱ!፤ እሰይ ይመርባቸው!:: ችግሩ ያለው እርስ በርስ መወዳደራቸው ላይ ነው:: እርሶስ ራሶን ከሌሎች ጋ ያወዳድራሉ? ጓደኞችዎ ፎቅ ሰርተዋል? አንድ ሐያት አንድ ለቡ? እርሶ አልሰሩም? ታዲያ በዚህ ቅር ይሎታል? አይበሎት!:: እነርሱ ይሳካላቸው:: ለእርሶ ደግሞ እግዚአብሔር በጊዜው ይሰጦታል:: እርስዎ ራስዎን ከማንም ጋ አያወዳድሩ::

ሌላው የሰውን ልጅ የሚያስቸግር ከባድ ነገር ቅናት ነው:: "አጥንትን ያነቅዛል" ይለዋል መፀሀፍ ቅዱስ (ምሳ 14:30):: የቅናት መነሻው ደግሞ ጤናማ ያልሆነ ውድድር...... ራስን ከሌላው ጋ ማስተያየት...... ማነፃፀር ነው:: በነገራችን ላይ ቅናት የነጮቹም ችግር ነው:: ፊታቸው በርበሬ እስኪመስል ድረስ ነው የሚቀኑት:: መበለጥ ፈፅሞ አይወዱም...... አንዳንዶቹ ነው ያልኩት!::

ቅናት በተለይ ደግሞ በሀይማኖት ሰዎች አካባቢ ለምን እንደሚጠነከር አላውቅም:: ግን እዛ አካባቢ በጣም ጠንካራ ነው!:: ሰዎች ቅናትን ካልገሰፁት በስተቀር ወደ ትልቅ ከፋት ሊወስዳቸው ይችላል:: ንጉስ ሳኦል በዳዊት ላይ ስለቀና የዳዊትን ኑሮ የስቃይ አደረገው:: የእርሱም የራሱ ህይወት ተበላሸ!:: ቅናትና ውድድርን እግዚአብሔር ከእኛ ያርቃቸው!...... እኛም እናስተናግዳቸው!::

## የጥበብ እንቁ 6

# ራስን ዝቅ ማድረግ !

ቅድስት ማርያም በመልአኩ ገብርኤል ለመጣላት መልዕክት መስማማቷን ስትገልፅ "እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደቃልህ ይሁንልኝ" ነው ያለችው (ሉቃ 1፡38)፡፡ "የጌታ ባርያ" ያለችው መልአኩን ሳይሆን ራስዋን ነው፡፡ የእንግሊዘኛው "Behold the handmaid of the Lord, be it unto me according to thy word" ነው የሚለው፡፡ ለራስዋ የሰጠችው መጠርያ የሴት አገልጋይ መጠርያ የሆነውን "handmaid" የሚለውን ነው፡፡ ይህም ማርያም ራስዋን እንዴት ዝቅ ታደርግ እንደነበረ ያሳያል፡፡ እርሷ ልማዷ ራስዋን ዝቅ ማድረግ ነበር!፡፡ ብትፈልግ እኮ በደንብ መኩራት ትችል ነበር፡፡ ከእርሷ የተወለደው.... በቤቷ ያደገው ኢየሱስ.... ፍጥረት ሁሉ በእጁ ላይ ያለ..... አምላክ ነው፡፡ "ድንግል ፈጣሪዋን ወለደች" እንዲሉ ማርያምን ራሷን ሳይቀር የሰራት ፈጣሪዋ ነው፡፡ እርሷ ግን መኩራቱን አልመረጠችም፡፡

ታላላቅ ስብእና፣ አስተሳሰብና እውቀት ያላቸው ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ፡፡ ብዙ ፍሬ እንዳለው ዛፍ ወደ መሬት ይጎነበሳሉ፡፡ ሌሎችን ከራሳቸው አስበልጠው ያያሉ፡፡ ጥራዝ ነጠቆቹ ደግሞ ያለ እነርሱ አዋቂ፣ ያለ እነርሱ ትልቅ ሰው ያለ አይመስላቸውም፡፡ ትንሽ በርከት ያለ ገንዘብ ካላቸው መንገዱን ሁሉ ልቀቁልኝ ይላሉ፡፡ የመኪና ቁልፍ በእጃቸው እያሽከረከሩ ካፌ ገብተው የሚታዩበት ቦታ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ "ማነሽ አንቺ!..... እስቲ ነይ እዚህ ታዘዢ!" ብለው በንቀት ይጣራሉ፡፡ ሲቀርብላቸው ማኪያቶው ጠቆረ ወይም ነጣ ብለው ይደነፋሉ!፡፡ የምታስተናግዳቸው ሴት ምናልባት በአእምሮዋ ከእነርሱ ልትበልጥ እንደምትችል አያስተውሉም፡፡

የእከሌ ዘር ነኝ ብሎ መኩራትም እኔ ብዙ አይገባኝም፡፡ እከሌ ምናልባት ትልቅ ስራ ሰርተው አልፈው ይሆናል፡፡ የእርሳቸው ዘር ነኝ ብሎ መኩራት ግን አስፈላጊ አይደለም፡፡ ከተቻለ እንደርሳቸው ሰርቶ ማሳየት ነው

እንጂ!:: ሌሎቹ ደግሞ "ተምረናል.... አውቀን ጨርሰናል....." የሚሉት ናቸው:: በቃ! የአለም ኢንሳይክሎፒዲያ ሆነዋል:: ቁጭ አድርገው በደንብ ቢያናግሩአቸው ግን ከኮሌጅ ከተመረቁ ሁለት ገፅ ቁም ነገር አንብበው እንደማያውቁ ይረዳሉ::

ደግሞ ሌሎችም አሉ:: የቤተ-ክርስትያን አገልጋዮች ናቸው:: ልክ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ...... ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሮ ለመግባት..... እነርሱ ብቻ እንደተፈቀደላቸው ነው የሚያስቡት:: የእግዚአብሔር ዋነኛና ብቸኛ ቃል አቀባይ ናቸው...... በእነርሱ አመለካከት:: ስለዚህም ይኮራሉ..... እንደኛው ሰው መሆናቸውን ይረሳሉ::

እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙት ሰዎች ትሁታኖቹ ናቸው:: ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉቱ!:: እያላቸው እንደሌላቸው፣ እያወቁ እንደማያውቁ፣ ትልቅ ባለስልጣን ሆነው ሳለ እንዳልሆኑ ይሆናሉ:: ሁሉን ሰው ያከብራሉ!:: በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ያ ሀሳብ በእነርሱ ዘንድ አለ:: "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋ መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፤ ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፤ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ"(ፊሊ. 3፡6-7) እንደሚል ቃሉ ምሳሌነቱን እየተከተሉ ራሳቸውን ዝቅ ያደርጋሉ:: ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ..... የእግዚአብሔር ልጅ፣ አልፋና ኦሜጋ ሆኖ ሳለ ራሱን ካዋረደ...... የእኔ መኮፈስ ምን ያመጣልኛል?

ንጉስ ዳዊትም በእግዚአብሔር የተሾመ ታላቅ ንጉስ ሆኖ ሳለ "አቤቱ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድን ነው?" ብሎ ካለ (1ኛ ዜና 17፡16) ፣እኔም ከእርሱ ልማርና ልበል እንጂ...... "በውኑ እኔ ማን ነኝ?..... ቤቴስ ምንድነው?" :: ነገሩ እንደሁ እንደ ፑሊ ነው:: ሰው ራሱን ዝቅ ሲያደርግ ከፍ ይላል፤ ራሱን ከፍ ሲያደርግ ደግሞ ዝቅ ይላል፤ ጌታ ለትሁታን ፀጋን ይሰጣልና!:: ከሀይለኛው ከእርሱ በታች ራሳቸውን የሚያዋርዱትን በጊዜው ከፍ ያደርጋቸዋል::

# የጥበብ እንቁ 7

## ሌላውን ሰው አለመናቅ !

ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ተነስቶ...... ወደ አባቱ...... ወደ ሰማይ ዙፋኑ....... ካረገ በኋላ የእርሱ ደቀ መዛሙርት የሆኑ አንድ መቶ ሀያ ሰዎች በአንድ ልብ ተሰብስበው ይፀልዩ ነበር፡፡ ከነዚህ አንዷ ቅድስት ማርያም ነበረች (ሐዋ 1፣13-15)፡፡ የሚያስገርመው ነገር ማርያም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳ ያሳደገች ሆና ሳለ በዚያ ከተሰበሰቡት ሰዎች ራሷን ሳታስበልጥ...... ሳትንቃቸው....... አብራ እየበላች...... አብራ እየጠጣች..... በአንድ ቤት መፀለይዋ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ማርያም ሰው አትንቅምና ነው!፡፡

ብዙ ሰዎች የሰውን ፊት አይተው ያደላሉ፡፡ ሀብት ያለውን ሰውና የሌለውን ሰው እኩል አያዩም፡፡ ለባለፀጋው ሰው ቁጭ ብድግ ይላሉ፤ ድሀውን ደግሞ ፊት ይነሳሉ፡፡ አገልጋዮችም ከሆኑ የድሀውን ችግር ለመስማት "ቢዚ ነኝ" እያሉ ባለፀጋውን ግን ቀኑን ሙሉ ለማጫወትና ለማሳቅ ጊዜ አላቸው፡፡

ሰው ሌላውን ሰው በሀብት ብቻ ሳይሆን በትምህርት ደረጃ፣..... በመልክ፣..... በስልጣን፣..... በዘር ከፍ ዝቅ ያደርጋል፡፡ ያልተማረ ሰውን የሚንቁ አሉ፡፡ እነርሱ የተገኙበትን ብሔር ትልቅ የሌሎችን ደግሞ ትንሽ አድርገው የሚያዩም አሉ፡፡ ለባለስልጣን ጠብ እርግፍ ብለው ስልጣን የሌለው የመሰላቸውን ደግሞ ችላ የሚሉም አሉ፡፡ ይህ የሰውን ፊት አይቶ የማድላት ነገር እጅግ ከወረደ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው፡፡

ጉድ ሼፐርድ የሚባል ክሊኒክ በሰራሁበት ዘመን ሊታከሙ የሚመጡት ሴቶች የተለያየ የኑሮ ደረጃ ያላቸው ነበሩ፡፡ አንዳንዶቹ ሲገቡ ሽቶ የተቀቡ ሳይሆን ሽቶ ውስጥ ተነክረው የመጡ ነበር የሚመስሉት፡፡ እጆቻቸው...... አንገታቸው...... በወርቅና በአልማዝ የተሸቆጠቆጠ ነው፡፡ እነርሱን ከመቀመጫዬ ተነስቼ በአክብሮት አስተናግዳለሁ፡፡ መልካም

አደረግሁ!:: እነርሱ ከወጡ በኋላ ግን ሌላ ታካሚ ትገባለች:: በኑሮ የተንሳቆለች....... ኮንጎ ጫማ ያደረገች....... ሻማ ቀሚስ የለበሰች..... ቢያሽለኝ ብላ ፀጉሯ ላይ ቅቤ አድርጋ ስምንት ቀን ያከረመች...... ትሆናች:: እንግዲህ ያቺኛዋን ሴት አክብሬ ይቺኛዋን ችላ ብላትና..... "ተንፍሺ!"....... "ተነሺ!" እያልኩ መንጩቅ መንጩቅ ባደርጋት በእግዚአብሔር ፊት እጅግ የተናቀ ሰው እሆናለሁ:: በራሴም ህሊና ፊት....... ትንሽ ሰው!::

ሰው በሰውነቱ የከበረ ነው:: እውነት ነው ግብራቸውና አስተሳሰባቸው የማያስከብራቸው ሰዎች ይኖራሉ:: ቢሆንም በእኛ በኩል ሰዎችን ሁሉ ለማክበር መወሰን አለብን:: እነርሱን ስናከብር ራሳችንን ማክበራችን ነው:: አንዳንድ በጣም የምደነቅባቸው የዩኒቨርሲቲ መምህራን ነበሩ:: እነዚህ መምህራን ተማሪዎቻቸውን አይንቁም:: ከግቢው ዘበኞች ጋ እኩል ሲያወጉ አገኛቸዋለሁ፤ የፅዳት ሰራተኞቹን ጊዜ ሰጥተው ሲያዳምጧቸው አያቸዋለሁ፤ ካፌ ሲገቡ ከማዘዛቸው በፊት አስተናጋጇን ሰላም ብለው ነው:: እንደዛ አይነት ሰዎች ደስ ይሉኛል....... አከብራቸዋለሁ!::

ሰውን የሚንቁ ሰዎች ራሳቸው በራስ መተማመን የሌላቸውና ከፍተኛ የበታችነት ስሜት የሚሰማቸው ናቸው:: ያንን የሚሰማቸውን የበታችነት ስሜት ለማካካስ ነው ቀድመው የሚንቁት:: በእርሶ ዘንድ ግን ሰው መናቅ አይኑር:: ጌታ ኢየሱስ የቅርብ ወዳጆቹንና ደቀመዛሙርቶቹን ሲመርጥ የመረጠው አሳ አጥማጆችን...... ያልተማሩ የተባሉትን...... በሌሎች የተናቁትን....... እንደ ማቲዎስ ያሉ ቀራጭና ሀጢያተኛ የተባሉትን ጨምሮ ነበር:: ይህ ታላቅ አስተሳሰብ ነው!::

# የጥበብ እንቁ 8

## በቀላሉ አለመቀየም ! (Taking no offence !)

የእስራኤልን ህዝብ ከግብፅ መርቶ ያወጣው የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ሞቶ ወደ አባቶቹ ከተሰበሰበ በኋላ እግዚአብሔር ሆን ብሎ እስራኤላውያኑ የሙሴን መቃብር እንዳያገኙት ሰወረባቸው (ዘዳ 34፡6)፡፡ ሙሴን እጅግ በጣም ይወዱት ስለነበር የተቀበረበትን ቦታ ቢያገኙት ትልቅ ሀውልት ሊሰሩለት ይችሉ ነበርና ነው፡፡ ሀውልት መስራት ብቻም ሳይሆን ወደ ሀውልቱ በመሔድም ሊያመልኩት ይችሉ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን ይህ እንዳይሆን ልዩ ጥንቃቄ አደረገ፡፡

ጌታ ኢየሱስም በስጋ የወለደችው እናቱ በጣም ተወዳጅ እንደሆነች ያውቃል፡፡ እርሱ ደግሞ የመጣው የሰማይ አባቱንና አምላኩን ልዑል እግዚአብሔርን ለመግለጥ ነበር፡፡ ስለዚህም ሰዎች ማርያምን ከመውደድ የተነሳ ለእግዚአብሔር የሚገባውን አምልኮ ለእርሷ እንዳይሰጡ ተጠንቅቋል፡፡ በዚህም ምክንያት እርሱ ባስተማረባቸው አመታት በህዝብ ፊት ብዙ ስለ እርሷ አልተናገረም፡፡ እንደውም አንዳንድ ቦታ ላይ "ማርያም በዚህ ተቀይማ ይሆን?" የሚያሰኙ ነገሮችን ተናግሯል፡፡

ለምሳሌ በአንዱ ቀን ከህዝብ መሀል አንዲት ሴት ከፍ ባለ ድምፅ "የተሸከመችህ ማህፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁአን ናቸው" አለችው፡፡ እርሱ ግን "አዎን፤ ብፁአንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው" ብሎ መለሰላት (ሉቃ 11፤27-28)፡፡ በሌላ ቀን ደግሞ "እናትህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው በውጪ ቆመዋል" ተብሎ ሲነገረው "እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት እነዚህ ናቸው" ብሏል (ሉቃ 8፤19-21) ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህን ያደርግ የነበረው እናቱን ስለማያከብር አልነበረም፡፡ በሙሴ ህግ እናትና አባትን ማክበርን ለህዝብ ያስተማረ ማን ሆነና?!፤ ነገር ግን ሙሉ ትኩረት ወደ እግዚአብሔር...... ወደ ሰማይ አባቱ እንዲሆን ይጠነቀቅ ስለ ነበር ነው፡፡

ታዲያ ቅድስት ማርያም እንዲህ አይነት የጌታን ንግግሮች ስትሰማ አትቀየምም ነበር፡፡ ነገሩን ትረዳዋለች፡፡ እርሷም ያ ፍቅር የሆነ ልጇ...... ደግሞም ፈጣሪዋ...... ይከበርላት እንጂ ክብሩን አትሻማም ነበር፡፡ እርሱ ሰውም አምላክም እንደሆነ፣ እርሷ ግን ሰው ብቻ እንደሆነች ረስታ አታውቅም፡፡ አመለካከቷ የላቀ መንግስታዊ አመለካከት ስለነበር ደስታዋ በእግዚአብሔር ስራ መሰራት ላይ፣ ወንጌል ለድሆች በመሰበኩ ላይ ነበር፡፡

ድሮ...... ድሮ..... በብዙ ነገር ሳላልፍ በፊት በጣም ቶሎ የሚከፋው (Sensitive የሆነ) ፣ በቀላሉ የሚቀየም ሰው ነበርኩ፡፡ በዘመናት ያለፍኩባቸው መንገዶች ግን ያንን ተቀያሚነቴን አቅልጠው አውጥተውልኛል፡፡ ምስጋናዬ ለዚህ ላበቁኝ ይሁንልኝና አሁን ቶሎ አይሰማኝም...... ቶሎ አይከፋኝም!፡፡ በምድር ላይ ብዙ አይነት አስቸጋሪ ሰዎች አሉ...... ይኖራሉማል፡፡ ቶሎ የሚከፋንና የምናኮርፍ ከሆነ ዘመናችን በሀዘን ያልቃል፡፡ እንዳኮረፍን አመታቶቻችን ያነጉዳሉ!፡፡

የትዳር ጓደኛዎን ፈጥነው አይቀየሙ፡፡ ጓደኞችዎን..... ዘመዶችዎንም ቶሎ አይዘኑባቸው፡፡ መጠነኛ ግጭቶች (Conflicts) ሁል ጊዜ ይኖራሉ፡፡ በሰዎች መካከል ቀርቶ በእኛ በራሳችን..... በውስጣችን እንኳን የተለያዩ ግጭቶች አሉ፡፡ በሰዎች መካከል ያለው ግጭት "Interpersonal Conflict" ሲባል በእኛ በውስጣችን ያለው ግጭት ደግሞ "Intrapersonal Conflict" ተብሎ ይጠራል፡፡ ፈፅሞ ምንም ግጭት የሌለበት ኑሮ መኖር አይቻልም ማለት ነው፡፡ አንዳችንን ከሌላችን የሚለየን ያንን ግጭት የምንይዝበት...... ግጭቱንም የምንፈታበትም መንገድ ነው፡፡

የልብ ሰፋት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ አንዳንዴ ብዙ ለውጥ የማያመጡ ሁኔታዎችን በትዕግስት ማለፍ ያስፈልጋል፡፡ የሰዎችን እያንዳንዷን ስህተት መመርመር አስፈላጊ አይደለ፡፡ አይቶ ማለፍ..... ሰምቶም ማለፍ ....... የሚያስፈልግባቸው ጊዜያት አሉ፡፡ የትዳር አጋራችንም፣ ጓደኞችንም፣ ዘመዳችንም..... ሁሉም ፍፁም አይደሉም፡፡

አንድ ጊዜ አንዲት እህት ለትዳር ስትፀልይ ስለምትፈልገው የባል አይነት ብዙ መስፈርቶችን ደረደረች ይባላል፤ "መልኩ.... ቁመናው ያማረ!.....

በጣም የተማረ!...... ልዩ አፍቃሪ (Romantic)...... የማይቆጣ!...... የማይናደድ!..... በጣም ደግ!...... ሩህሩህ!...... ወደ ሌላ ሴት ፊፅም የማያይ!.... በጊዜ ቤቱ የሚገባ!..... በጠዋት ቁርስ ሰርቶ መኝታዬ ድረስ የሚያመጣልኝ!" እያለች ደረደረችው፡፡ እግዚአብሔርም ሁሉን ካዳመጠ በኋላ "ልጄ ሆይ! እንዲህ አይነት ሰው እኔ ራሴ ባገኝ ኖሮ ለትልቅ ስራ እሾመው ነበር፡፡ ካገኘሽው ጠቁሚኝ!" አላት ይባላል፡፡ ፍፁም የለም ማለት ነው ምሳሌው!፡፡

የምንኖርበት አለም ፍፁም ያልሆነ (Imperfect) ሆኖ ሳለ ማንንም ሰው ፈፅሞ ስህተት የማይሰራ ፍፁም ሰው አድርገን ከወሰድነው አንዳንዴ ያ ሰው ከጠበቅነው በታች ሆኖ ስናገኘው..... ሲያጠፋ..... ሲበድለን ቶሎ መቀየም......... ማኩረፍ የለብንም፡፡ ሰዎችም ስለ እኛ የተለያየ አስተያየት ሲሰጡ መከፋት የለብንም፡፡

በስራም ሆነ በተለያየ መንገድ በህብረተሰብ ውስጥ ወደ ከፍታ ሲወጡ በእርሶ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች መሰንዘራቸው አይቀርም፡፡ ከአስተያየቶቹ ደግሞ እንዳንዶቹ...... ወይም ብዙዎቹ...... ደስ የማያሰኙት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ችግረኞችን ሲረዱ...... "በድህ ስም ሀብት እያካበቱ ነው!" ...... ከተማ ሲያፀዱ...... "ቆሻሻውን እየሸጡት ነው!"...... ሮጠው ሲያሸንፉ........ "እስደግመው ነው!" ....... ሲባሉ ይችላሉ፡፡ እርሶ በንፅህና ይስሩ እንጂ ለምን እንዲህ ተባልኩ እያሉ አይማረሩ፡፡ ያደረጉት መልካም ነገር ሁሉ የሚነገርበት....... የሚወራበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ስለዚህ አይቀየሙ! አይከፋዎት!፡፡

# የጥበብ እንቁ ፱

## ቀናውን ማሰብ ! (Positive thinking!)

ቅድስት ማርያም ቀና ቀናውን የምታስብና የምትናገር "ፖዘቲቭ ቲንከር (Positive thinker)" ነበረች። ይህን የምናስተውለው ከኤልሳቤጥ ጋ በተገናኘች ጊዜ የተናገረችውን ስናስብ ነው። በወቅቱ ማርያምን የሚጠብቃት ፈተና ቀላል አልነበረም። ከመንፈስ ቅዱስ መፀነሷን ዮሴፍ ባይረዳትስ ኖሮ? ከትዳር ውጪ አርግዛ መጣች ብሎ አሳልፎ ቢሰጣትስ ኖሮ? በእርግጠኛነት የሚጠብቃት እድል በድንጋይ መወገር እንደሆነ ታውቃለች። እርሷ ግን ይህንን አስፈሪ መንገድ ቁጭ ብላ እያሰላሰለች "ምን ይውጠኝ ይሆን?" ብላ በመጨነቅ ፋንታ ቀናውን......... ፖዘቲቩን ብቻ በማሰብ "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል!" ብላ ቀናውን........ ፖዘቲቩን ተናገረች.......። በራስዋም ላይ አወጀች!። ይህም ቅድስት ማርያም ቀናውን በማሰብና በመናገር የምታምን ፖዘቲቭ ቲንከር መሆንዋን በግልፅ ያሳያል (ሉቃ 1:48-49) ።

በዘመናችን ያሉ የተለያዩ የመንፈሳዊ ህይወት፣ የስነ-ልቦናና፣ የፍልስፍና አስተማሪዎች በአእምሮአችን የምናስተናግዳቸው ሀሳቦች የኑሮአችንን መከናወንና ወደ ፊት የሚገጥመንን እጣ ፈንታ እንደሚወስኑ ያስተምራሉ። የነዚህ አስተማሪዎች ችግር ግን ታላላቅ ፅንሰ ሀሳቦችን ከመፀሀፍ ቅዱስ በመውሰድ የራሳቸው አእምሮ ያመነጨው ረቂቅ ሀሳብ አድርገው ማቅረባቸው ነው። በእግዚአብሔርም ፈንታ 'ዩኒቨርስ' (Universe) የሚለውን ይተካሉ። ሁሉም ነገር በሰው ችሎታ እንደሚሰራ....... በሰው ውሳኔ እንደሚሆን...... መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት የሚባል ነገርም እንደሌለ ይሰብካሉ። ስለዚህ እውነቱን በሀሰት ይቀይጡታል።

በእርግጥ በአእምሮአችን የምናስባቸው ሀሳቦችና በአንደበታችን የምንናገራቸው ነገሮች በእኛ ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳላቸው መፀሀፍ ቅዱስ ያስተምራል። ሰው በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነው! (ምሳ 23:7)።

በአእምሮአችን ሁል ጊዜ የምናስበው የተሸናፊነትን ሀሳብ ከሆነ ተሸናፊ እንሆናለን!፤ የምናሰላስለው ሀሳብ ግን የድልና ያሸናፊነት ከሆነ ደግሞ በፊታችን የሚመጣው አሸናፊነት ነው፡፡ ስለዚህ የምናስበው ነገር ሁሉ ቀና ቀናውን መሆን አለበት፡፡

ከአንደበታችን የሚወጣ ቃል ከፍተኛ ሀይል አለው፡፡ ታላቁ መምህር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር ይህን ተራራ፡-ተነቅለህ ወደ ባህር ተወርወር ቢል ይሆንለታል" ብሎናል (ማር 11:23) ፡፡ እንግዲህ አለመጠራጠሩ........ የእምነትን ቀና (ፖዘቲቭ) ሀሳብ ማሰቡ ነው፡፡ የዚህ ተቃራኒና ቀና ያልሆነው አሉታዊ (ኔጌቲቭ) ሀሳብ ደግሞ የመጠራጠር፣........ የመወላወል፣........ የማፈግፈግ ሀሳብ ነው፡፡ "ተነቅለህ ወደ ባህር ተወርወር" የሚለው ደግሞ በአንደበት የሚነገር፣ ከአንደበት የሚወጣ ነው፡፡ ይህ የእምነት ቃል በመንፈሳዊው አለም ታላቅ ስራን ይሰራል፡፡

ፖዘቲቭ ቲንኪንግ ሆን ብለን የምንለማመደው ነገር ነው፡፡ ወደ አእምሮአችን የሚመጡ ሀሳቦችን ሙሉ ለሙሉ ማቆም ባንችልም ገደብ ማስያዝ ግን እንችላለን፡፡ "በዚህች ደቂቃ ምን እያሰብኩ ነው?" ብሎ መጠየቅ፡፡ ከዚያም እያሰብን ያለነው ነገር አፍራሽ ከሆነ እርሱን አስወግደን የእርሱን ተቃራኒ መልካሙን ሀሳብ ማሰብ ነው፡፡ ስንናገርም "ነገ መልካም ይሆናል!"........ "እግዚአብሔር ታላቅን ነገር ያደርግልኛል!"...... "አሁን ካለሁበት ጉድጓድ እወጣለሁ!" ብሎ በቃል ማወጅ ያስፈልጋል፡፡

በተቻለን መጠን ስለ ሰዎች የምናስበው ነገር መልካም ይሁን፡፡ ሰዎቹ መልካም ባይሆኑ እንኳን እኛ ኢቃንተን ነው ማሰብ ያለብን፡፡ ለምሳሌ የምናውቀው ሰው ባጠገባችን ሰላም ሳይለን ቢያልፍ........ "ስላላየኝ ይሆናል...." ወይም "እንግዲህ ስራ በዝቶበት ሀሳብ ይዞት አላየኝ ይሆናል......." ብሎ ማሰብ፡፡ ለአንድ ሰው ስልክ ደውለን ስልኩ እየጠራ የተደወለለት ሰው ካላነሳ....... "እየው ይሄ ሰውዬ! ስልኬን እያየ አያነሳም!" ከማለት ይልቅ "ስልኩን አስቀምጦት ወጥቶ ይሆናል......" ወይም "ድምፁን አጥፍቶት ረስቶት ይሆናል" ብሎ ማሰብ ነው፡፡

በተቻለን መጠን ስለ ሰዎች ጥሩ ያልሆነ ነገር አለማውራት መልካም ነው። በተቻለ መጠን ያልኩት ለብዙዎች አስቸጋሪ ጉዳይ እንደሆነ ስለማውቅ ነው። ግን በደንብ ከታሰበበትና ከተለማመድነው ይቻላል። በሰዎች መሀል ተቀምጠን ስለ አንድ ሰው ከተነሳ ያ ሰው ያለውን አንድ በጎ ነገር አንስቶ በመናገር ማለፍ ይቻላል። ለምሳሌ አንድ ረዥም ሰው ብዙ የባህሪ ችግሮች ቢኖሩበትና ሰዎች በተሰበሰቡበት ስለ እርሱ ቢነሳ..... እርስዎም አስተያየት እንዲሰጡ ቢጠበቅቦት...... "ይገርማችኋል! ቁመቱ ረዥም ነው!" ብለው ያምልጡ። በተደጋጋሚ ደግሞ ብዙ ሀሜት ያለበት ህብረት ውስጥ ከሆኑ ጓደኞችን ይምከሯቸው። የማይለወጡ ከሆኑ ግን መለየትም ሊያስፈልግ ይችላል። ምክንያቱም ከምንናገረው ብቻ ሳይሆን ከምንሰማውም መጠበቅ አለብንና ነው።

ፖዘቲቭ ቲንኪንግ ለጤናችንም መልካም ነው። እርካታ ያለበትን የሰላም ኑሮ እንድንኖር፣ የጣፈጠ እንቅልፍም እንድንተኛ ያደርገናል። በህይወታችን ደስተኛ እንሆናለን። በተቃራኒው አእምሮአችንን በየለቱ የምንሞላው ከፉ በሆኑ....... የጥላቻ...... የምሬት....... የጭንቀት ሀሳቦች ከሆነና ኔጌቲቭ ቲንከር (Negative thinker) ከሆንን የተለያዩ ህመሞችን ወደ ሰውነታችን እንጎትታለን!፤ ውበታችን እየረገፈ ይመጣል!፤ ቶሎ እናረጃለን!፤ እድሜያችንም ያጥራል!።

የፖዘቲቭ ቲንኪንግ ትምህርትን በማስተማር የሚታወቁት ኖርማን ቪንሴንት የመፅሀፍ ቅዱስ አስተማሪ ናቸው።በዚህም ምክንያት የትምህርቱን መሰረታዊ ሀሳቦች የወሰዱት ከመፅሀፍ ቅዱስ ነው። እርሳቸውም ይህንን አበክረው ይናገራሉ።ፖዘቲቭ ቲንኪንግ የሰው ፈጠራ ሳይሆን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት ነው። እርሱ ስለሚሰቅሉት እንኳን "የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብሏል። ሰቃዮቹን እንኳን በቀና ሀሳብ ሊያስባቸው ቀናም ሊናገርላቸው ችሏል።

## የጥበብ እንቁ 10

# የጥበብ አክሊልን ማድረግ !

ቅድስት ማርያም ልጇ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ታውቃለች፡፡ ይህንን ደግሞ ለረዥም ጊዜ ለማንም ሳትነግር በሚስጥር መያዝ ነበረባት፡፡ ይህም ከባድ ነው!፡፡ ጌታ 30 አመት ሞልቶት፣ መንፈስ ቅዱስ ወርዶበት፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ እስኪገለጥ ድረስ ማርያም ለአንድም ሰው ስለ እርሱ ማንነት አላወራችም!፡፡ ዝም ብላ በልብዋ ትጠብቀው ነበር፡፡ እንዴት ያስችላል? ሌላ ሴት ብትሆን እኮ ከሰው በተጣላች ቁጥር "በቤቴ ያለው ማን እንደሆነ ብታውቂ አትደፍሪኝም ነበር! ቆይ!" ነበር የምትለው፡፡ ማርያም ግን ዝም አለች..... በልቧ እየጠበቀችው! (ሉቃ 2፡51)፤ ይህ ደግሞ የጥበበኛ ሴት ምልክቷ ነው፡፡

ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ትከብራለች....... የተከበረም ነገር ሁሉ አይስተካከላትም....... በብርና በወርቅ ከመነገድ ይልቅ በእርሷ መነገድ ይሻላል...... በቀኝዋ ረዥም መንገድ፣ በግራዋ ባለጠግነትና ክብር ነው ተብሎላታል (ምሳሌ 3፡13-20)፡፡ ደግሞም ከፍ ከፍ አድርጋት፣ ከፍ ከፍ ታደርግሀለች....... ብታቅፋትም ታከብርሀለች...... የሞገስ አክሊልን ታበረክትልሀለች! ተብሎ ተፅፎላታል (ምሳሌ 4፡5-9)፡፡

እውቀት (Knowledge) ስለ አንድ ጉዳይ ወይም ነገር ያለን መረጃና ብርሀን ነው፡፡ ማስተዋል ደግሞ መረዳት ወይም ግንዛቤ (Understanding) ነው፡፡ ያስተዋልነውን ነገር እውቀት እናደርገዋለን፡፡ እውቀታችንን ግን የምንጠቀመው በጥበብ ነው፡፡ ሰው እውቀት ኖሮት ጥበብ ከሌለው ብዙ ጥፋት ሊያጠፋ ይችላል፡፡ በ HIV/AIDS ህክምና ላይ ብዙ ምርምር ሰርቶ PHD የሰራ ሰው ከማያውቃት ሴት ጋ ሊተኛ ይችላል፡፡ ለዛውም ያለ ኮንዶም!፤ እውቀቱ አለው...... ጥበብ ግን ጎድሎታል!

ጥበብ አኗኗርን ታስተምራለች...... በሰዎች መሀል ሳንናቆር እንዴት እንደምንኖር ታሳየናለች!፤ አሰራርን ውጤታማ ታደርጋለች!፤ የራሳችን ሀብት ይዞን እንዳይጠፋ ትጠብቀናለች!፤ በሚጠሉን ሰዎች መሀል እንዴት መኖር እንደምንችል ታሳየናለች፡፡ አንድ ጊዜ የአሜሪካ 37ኛው ፕሬዚደንት የነበሩት ሪቻርድ ኒክሰን ሲናገሩ "ሰዎች ቢጠሉህ አያሸንፉህም! መልሰህ የጠላሀቸው ቀን ግን ተሸንፈሀል!" ብለው ነበር፡፡ በአስቸጋሪ አለም ስንኖር 'እንዴት' መኖር እንዳለብን ጥበብ ታሳየናለች፡፡

ጥበበኛ ሰው በሰው ጉዳይ ዘሎ አይገባም፡፡ በጥበቡ የሚታወቀው ንጉስ ሰለሞን እንዳስተማረን "አልፎ በሌላው ጥል የሚደባለቅ ውሻን በጆሮው እንደሚይዝ ነው!" (ምሳሌ 26:17)፡፡ ጠቢብ ሰው ፈጥኖ አይናገርም....... ከመናገሩ በፊት የሚናገረውን በጥንቃቄ ይመዝናል፡፡ ከአንደበቱ ከወጣ በኋላ በተናገረው ላይ ስልጣን እንደሌለው ያውቃል፡፡ ከሀሜት ይርቃል!....... እዚህኛው ቤት እርሱ ሲያማ እዚያኛው ቤት እየታማ መሆኑን ያውቃል፡፡ ደግሞ ስሜቱን ይገታል!፤ ቱግ ቱግ አይልም!፤ የሰላምን ዋጋ ያውቃልና ሰላምን ይጠብቃል፡፡ መዘዙን ይረዳልና የሌላይቱን ሴት ብብት አያቅፍም....... ከሰው ሚስትም ይሸሻል፡፡ ጉድጓድ ለሰው አይቆፍርም........ ከቆፈረ ራሱ እንደሚወድቅበት ያውቃል፡፡

ቤትዎንም ስራዎንም በጥበብ ያስተዳድሩ...... ይምሩ!፡፡ በስራዎ ልፋት ስኬታማ መሆን ይችሉ ይሆናል፡፡ ስኬታማ ሆኖ ለመቆየት ግን ጥበብ ያስፈልጋል፡፡ በችሎታዎ...... በልፋትዎ....... ከፍታ ላይ ቢወጡ....... እዚያ ከፍታ ላይ የምታቆይዎ ጥበብ ናትና ጥበብን አጥብቀው ይያዙ!፡፡ የዚያን ጊዜ ወጥተው ወጥተው እንደሚንከባለሉት አይሆኑም፡፡ ከፍ ካሉበት ከፍታ በላይ ከፍ ያለ ሌላ ከፍታ አለና ጥበብ ወደዚያም ታወጣዎታለች!፡፡

ቤት በጥበብ ይሰራል፡፡ ጥበበኛ ሴት ተብላ በምሳሌ መፅሀፍ የተተረከችልን ሴት አስገራሚ ናት (ምሳሌ 31:10-31)፡፡ እድሜዋን ሙሉ መልካም ታደርጋለች....... ክፉ አታደርግም....... ሌሊት ሳለ ትነሳለች........ መብራትዋ በሌሊት አይጠፋም.......... እጅዋን ወደ አመልማሎ ትዘረጋለች....... እንዝርትም ትይዛለች........ ለቤትዋ ሰዎች ሁሉ ምግባቸውን ትሰጣለች....... ለሰራተኞችዋም ስራቸውን ታከፋፍላለች........ ደግሞ ድሆችን ትረዳለች.......

የበረዶ ብርድን አትፈራም........ ቤተሰብዎችዋ እጥፍ ለብሰዋልና......... ብርታትና ከበሬታ ልብስዋ ነው.......... በኋላ ዘመን ላይ ትስቃለች...... በጥበብ አፍዋን ትከፍታለች........ ባልዋም ያመሰግናታል........ ስራዎችዋም በአደባባይ ያመስግኗታል....... ይህች ጥበበኛ ሴት ናት!፡፡

ልጆቻችንን ስናሳድግም ጥበብ በእጅጉ ያስፈልገናል፡፡ አንድ ጊዜ ወንድም እና እህት የሆኑ ወጣቶችን እንዳነጋግር ወላጆቻቸው ጠየቁኝ፡፡ ወጣቶቹንም አግኝቼ አወራኋቸው፡፡ ወንዱ "እኔ ስለ እግዚአብሔር መስማት እንኳን አልፈልግም" አለኝ፡፡ ሴቷ ደግሞ "ቄስ ወይም ፓስተር የሚባል ሰው ለአይኔ እንኳን ማየት አልፈልግም...... (I hate them!) እጠላቸዋለሁ!" አለችኝ፡፡ ወጣቶቹ እኔንም ለማግኘት ፈቃደኛ የሆኑት ዶክተርነቴ ተነግሯቸው፣ የእግዚአብሔር ሰውነቴ ደግሞ ተደብቋቸው ነበር፡፡

በፍቅርና በትዕግስት ለምን እንደዚህ እንደሆኑ ለማወቅ ሞከርኩ፡፡ ነገሩ እንደዚህ ነው፤ ልጆች ሆነው ቤታቸው ውስጥ ማታ ማታ ሁል ጊዜ የቤተ-ክርስትያን ፕሮግራም ይደረጋል፡፡ ይህ ሲደረግ ልጆቹ ከወላጆቻቸው ጋ መጫወት፣ ቴሌቪዥን ማየት፣ በቤታቸው መቦረቅ አይችሉም ነበር፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ጊዜ ከክፍለ ሀገር እንግዳ ስለሚመጣ ለእንግዳው መኝታቸውን እንዲለቁ ይጠየቃሉ፡፡ የሚወዱትን የመኝታ ክፍላቸውንና መኝታቸውን ለቀው በማይወዱት ስፍራ ይተኛሉ፡፡ ወላጆቻቸው ይህንን ሲያደርጉ እግዚአብሔርን ማገልገላቸው........ እርሱን ደስ ማሰኘታቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ልጆቻቸውን ያለ አግባብ መበደላቸውን አላወቁም፡፡ ስለዚህም ሲያድጉ ልጆቹ.......... ቤተ-ክርስትያንንና አገልጋዮችን........ ልጅነታቸውን የሰረቁባቸው ጠላቶቻቸው አድርገው ቆጠሯቸው፡፡ ይህ የወላጆቹ ጥበብ ማጣት ውጤት ነው፡፡ በጥበብ ሁሉን በልክ ቢያደርጉት ኖሮ የሆነው አይሆንም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ጥበብን ይጨምርልን፡፡

# የጥበብ እንቁ 11

# ፀሎትን መፀለይ !

ኤልሳቤጥ እየሰማቻት...... በእግዚአብሔር ፊት ቆማ...... ቅድስት ማርያም "ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች..... መንፈሴም በአምላኬ በመድሀኒቴ ሀሴት ታደርጋለች...." እያለች ምስጋናዋን አሳረገችው (ሉቃ 1፡47)፡፡ የማርያም ትልቁ መታወቅያዋ ፀሎት........ ዘመንዋን ሁሉ የሰጠችውም ለፀሎት ነበር፡፡ በህይወት ዘመንዋ የገጠሟትን ተግዳሮቶች ሁሉ በፀሎት አለፈቻቸው፡፡ እስትንፋስዋ ነበር ማለት ይቻላል......... ፀሎት!፡፡

የፀሎት ነገር ሲነሳ ሰዎች ቀድመው የሚያስቡት ፀሎት ለአዛውንቶች የተተወ ነገር እንደሆነ ነው፡፡ ሰዎች በህይወታቸው መጨረሻ ሀጢያታቸውን ለማወራረድ የሚጠቀሙበት የሒሳብ መዝገያ አድርገው ያዩታል፡፡ ወይም ደግሞ ፀሎት ያልተማሩ ሰዎች፣ ተስፋ የሌላቸው ፣ ግራ የተጋቡ ሚስኪኖች የሚለማመዱት ለሰለጠነው ሰው ግን የማያስፈልግ ኋላ ቀርነት አድርገው ይወስዱታል፡፡ ሌሎችም ፀሎትን ለቄሶች የተሰጠ፣ አድካሚ፣ ፍሬ የሌለው ማነብነብ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡

እኔ ግን እንዳየሁት ፀሎት አእምሮአቸው እጅግ ብሩህ የሆነ (Brilliant የሆኑ) ሰዎች የህይወት ልምምድ ነው፡፡ ብሪሊየንስ እራሱ የሚያመለክተው በብርሀን መሞላትን ነው፡፡ ታዲያ የሚፀልይ ሰው የሚንበረከከው ወይም የሚቆመው ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሀን ውስጥ በተቀመጠው በእግዚአብሔር ፊት ነው፡፡ ያ ራሱ ብርሀን የሆነ እግዚአብሔር በፊቱ ባለው ሰው ላይ ብርሀኑን ያበራል፡፡ ብሪሊየንት ያደርገዋል፡፡

ፀሎት አእምሮን ይከፍታል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጨማሪ ትምህርቶችን በምማርበት ጊዜ..... ፈተና ቢቀርብም....... የሚፃፍ

ወረቀት ቢኖርም...... ለፀሎት ጊዜ መስጠትን አልተውም ነበር፡፡ ታዲያ የሚያስገርመኝ ከፀሎት ስነሳ አስቸግሮኝ የነበረው፣ የከበደኝም ሁሉ በጣም ይቀለኛል፡፡ አእምሮዬ ይከፈታል!፤ ብዙ ሰአት ሊፈጅብኝ ይችል የነበረውን ስራ በአጭር ጊዜ እጨርሰው ነበር፡፡

አምላካችን እግዚአብሔር ፀሎትን ይሰማል፡፡ ሰምቶም ይመልሳል፡፡ ፀሎት የመንፈስ እርካታን...... የህይወት ደስታን...... የኑሮ ስኬትን ያመጣል፡፡ ካልሞከሩት እስቲ ዛሬ ይጀምሩት፡፡ ምንም አያስቸግርም..... አይከብዶትም፡፡ ማታ ቤትዎ ሲገቡ ለብቻዎ ቆም ብለው ወይም የበለጠ እግዚአብሔርን ለማክበር ከወደዱ በርከክ ብለው "ዛሬ ስላደረክልኝ ሁሉ በልጅህ በኢየሱስ ስም አመሰግንሀለሁ" ይበሉት፡፡ ደግሞ የከበዶትን፣ ያስጨነቆትን ሁሉ ይንገሩት ለእግዚአብሔር!፤ ይሰማዎታል!፤ደግሞም ይመልስሎታል!፡፡

እኔ እፀልያለሁ!...... ሞኝ ስለሆንኩ ግን አይደለም፡፡ ብዙ የወጣትነት ዘመኔን ያሳለፍኩት ኒያላ እያጨስኩ፣ ቪኖ እየጠጣሁ ነው!፡፡እውነተኛው አራድነት ሲገባኝ ግን ጉልበቴን ለእግዚአብሔር አንበረከኩ፡፡ በእግዚአብሔር ፊት በራሴ ለመቅረብ ብቃት ስለሌለኝ ደግሞ ብቃቱ ባለው በመድህኔአለም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በፊቱ ቀረብኩ፡፡ በአዲሱ አራድነቴ ደስ ይለኛል!፡፡

እርሶ ከፀለዩ እግዚአብሔር የኑሮዎ አጋር የህይወትዎ አለኝታ ይሆናል፡፡ በቅዱሳን መላዕክቶቹ ይጠብቆታል!፤ ልጆችዎ በሰላም ውለው ይገባሉ፡፡ በከበረው በልጁ ደም ስለሚሸፈኑ መቅሰፍት ወደ ቤትዎ አይገባም!፤ ሰዎች በእርስዎ ላይ የሚያስቡት ክፋት፣ የሚያስደግሙት ድግምት፣ የሚያስጠነቁሉት ጥንቆላ አይሰራም፡፡ ሰላምና ደስታ የእርስዎ ይሆናሉ፡፡ ብቻዎን ስለምን ይንከራተታሉ?፤ ኢየሱስ እውነተኛ ወዳጅ ነው፡፡ ባለዎት ጊዜ ቀርቦ በሌሎት ጊዜ የሚለይ አይደለም፡፡ በተራራም በሸለቆም ያው ነው!፤ የቅርብ ወዳጅዎ ያድርጉት!፡፡

## የጥበብ እንቁ 12

# እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ ማለት !

በመልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ያ ታላቅ መልዕክት በመጣላት ጊዜ ቅድስት ማርያም "ኧረ እኔ ይቅርብኝ!" ማለት ትችል ነበር፡፡ "እግዚአብሔር ሆይ! እኔ አልችልም! ሌላ ሰው እንድትልክ እለምንሀለሁ!" ብትል አያስገርምም....... ታላቁ መሪ ሙሴ በመጀመርያ መልዕክት በመጣለት ጊዜ እንደዚያ ብሏልና (ዘፀ 4፡13)፡፡ "እኔ ብላቴና ነኝ! እናገር ዘንድ አላውቅም!" ብትልም አያስገርምም...... ነብዩ ኤርምያስ ደግሞ መልዕክት በመጣለት ጊዜ እንደዚያ ብሎ ነበርና (ኤር 1፡6)፡፡ ቅድስት ማርያም ግን "ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?" ብላ ብቻ ጠየቀች፡፡ በቅዱስ ገብርኤል መልሱ ከተሰጣት በኋላ ማርያም መስማማቷን በድንቅ ቃላት "እነሆኝ የጌታ ባርያ...... እንደ ቃልህ ይሁንልኝ!" ብላ አረጋገጠች! (ሉቃ 1፡38)፤ ፈቃድህ ይሁን አለች!፡፡

ባለፈው ዘመኔ እንዳስተዋልኩት አንዳንዱ እኔ ተመኝቼው የነበረው ነገር እኔኑ የሚጎዳኝ ነበር፡፡ ፈቃዶ...... ከፈቃዱ፤ ሀሳቤ...... ከሀሳቡ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ እየራቀ ተቸገርኩ፡፡ እኔ የማስበው ሌላ! እግዚአብሔር የሚያስብልኝ ሌላ!፡፡ ስለዚህ በአንዱ የህይወት ምዕራፌ ላይ ስደርስ እንዲህ ማለትን ተማርሁ...... "አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ! እንደ ፈቃድህ ይሁንልኝ!"...... ሙሉ ለሙሉ ለፈቃዱ እጄን ሰጠሁ! (Surrender አደረኩ)፡፡

አንዳንድ ሰው ይህ ነገር ካልሆነልኝ ብሎ ድርቅ ይላል፡፡ የተሟላ ኑሮ፣ ስራ፣ ቤተሰብ ያላቸው....... በማህበረሰባችን ውስጥ አንቱ የተባሉ ሰዎች .........ተነስተው አሜሪካ ሔጄ ካልኖርኩ ብለው መንገድ ያፈላልጋሉ፡፡ የእግዚአብሔር ሀሳብ ግን በምድራቸው የተከበሩ ሰው ሊያደርጋቸው ነበር፡፡ እምቢ ብለው በፈቃዳቸው ሲያደርጉት ግን መንገዱን ይለቅላቸዋል!፤ ይሔዳሉ!፡፡ እዚህ "ጋሼ መጡ" እየተባለላቸው ትውልድ ከመቀመጫው የሚነሳላቸው ሰው እዚያ ሔደው እጅግ ደስ የማያሰኛቸውን ስራ ይሰራሉ፡፡

አሜሪካ እንደሁ "አንቱ" ማለት አታውቅም፡፡ ታዲያ እኚህ ሰው ለምን የማይወዱት ነገር ሆነባቸው? "ፈቃድህ ይሁንልኝ" ማለትን ስላልተማሩ!፡፡ የትም ሀገር በእግዚአብሔር ፈቃድ መሔድ መልካም ነው፡፡ ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር ናትና በፈቃዱ ከኖሩ የእግዚአብሔር ልጆች የትም ባይተዋር አይሆኑም፡፡ ያለ ፈቃዱ ሲሆን ግን ትልቅ ዋጋ ያስከፍላል፡፡

አንዳንድ እህቶች ደግሞ 'እከሌን' ካላገባሁ ይላሉ፡፡ ምናልባት መልከና ቁመና አይተው....... ወይም በኑሮው ተደንቀው ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ "ይቅርብሽ" ብሎ ይመክራል!...... ይከለክላል!..... ምልክቶችን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ፈቃዱን አልፈው ሔደው ያደርጉታል፡፡ ከሀኒሙን በኋላ ያገቡት ሰው ሒትለር እንደሆነ ይደርሱበታል!፤ ቢቃ ኑሮው የመጥበሻ ኑሮ ይሆናል!፡፡ ለምን እንደዚህ ሆነ? ፈቃድህ ይሁንልኝ ማለትን ስላልተማሩ፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሲጀምሩት ደስ ላያሰኝ ይችላል፡፡ መቼም ቢሆን ከብቶች በሚያድሩበት በግርግም ውስጥ ልጅ መውለድ ደስ አያሰኝም፡፡ ማርያም ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ እዚያ ወልዳለች፡፡ በፈቃዱ ስንሔድ መጀመርያ ላይ የተሳሳትን ነው የሚመስለው፡፡ የፈቃዱ መልካምነት የሚታወቀው ቆይቶ ነው...... ቆይቶ!፡፡

አንድ ጊዜ ከአረብ ሀገራት አንዱ በሆነ ሀገር እንዳገለግል ተጋበዝኩኝ፡፡ ኤምባሲያቸው ስሔድ እያንዳንዱ መንገደኛ ቪዛ ለማግኘት ሙሉ የጤና ምርመራ ማድረግ እንዳለበት ነገሩኝ፡፡ "እናንተ ከማን በልጣችሁ ነው አውሮፓና ካናዳ ስንሔድ የማንጠየቀውን የምትጠይቁት?" አልኳቸው፡፡ በዚሁ ተለያየን!፡፡ ለካ ግን እግዚአብሔር እዚያ ሀገር ብሔድ ከሚገጥመኝ ከበድ ካለ ነገር እየጠበቀኝ ነበር፡፡ እኛ "ፈቃድህ ይሁን!" ካልነው በየዋህነት ልንሳሳት ከነበረው ሁሉ ይጠብቀናል፡፡ እግዚአብሔር አንዳንድ በሮችን ሲዘጋ ለእኛ ብሎ ነው..... ሊጠብቀን..... እንዳንጎዳበት!፡፡ እነሆኝ የጌታ ባርያ...... እንደ ቃልህ ይሁንልኝ!፡፡

# የጥበብ እንቁ 13

## የማይችሉትን ማወቅ !

ቅድስት ማርያም ለተጠራችበት ጥሪ በጥንቃቄ መኖርዋ እውነት ነው፡፡ ያንንም የህይወት ጥሪዋን በጥራት ተወጥታዋለች፡፡ ከእግዚአብሔር ያልተሰጣትን.... የማትችለውን ነገር ግን ለማድረግ አልሞከረችም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያቱን ሾሞ ሲልካቸው..... በሐዱበትም ወንጌልን ሲሰብኩ..... አጋንንቶችን ሲያስወጡ...... ህመምተኞችን ሲፈውሱ እንደከረሙ ማርያም ታውቃለች፡፡ በሌላ ጊዜም ሰባ ደቀመዛሙርቱን ልኳቸው እንዲሁ እንዳደረጉ ሰምታለች (ሉቃ 10፡1)፡፡ ታዲያ ማርያም ይህንን ስትሰማ "እኔስ ከማን አንሼ! እኔም ሔጄ እሰብካለሁ..... አጋንንትን አስወጣለሁ...... ህመምተኞችን አፈውሳለሁ!" አላለችም፡፡ በተሰጣት ነገር ብቻ አገለገለች!፡፡ የማትችለውንና ያልተላከችበትን ታውቅ ነበር፡፡

ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል አምላካችን እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እኔ የማልችላቸው ነገሮች ብዙ ናቸው!፤ እንደ ቀነኒሳ ልሩጥ ብዬ ብሞክር ሩጫ ያልለመደ ልቤን አደጋ ላይ እጥለዋለሁ!፤ እንደ ሙላቱ አስታጥቄ ሙዚቃ ልጫወት ብዬ ብሞክር ጫማ ሊወረወርብኝ ይችላል!፤ እንደ ኮሜድያን ደረጄ ህዝብ ላስቅ ብል የተሰበሰበውን ሰው ሁሉ በጣም አበሳጫለሁ!፤ እንደ ሽመልስ አበራ መድረክ ላይ ልተውን ብል በዚያ የተገኘው ሁሉም ሰው በስምምነት አዳራሹን ለቆ ይወጣል!፤ ለምን? አልተሰጠኝም! አልችለውም!፡፡

ግን ደግሞ የምችላቸው ነገሮች አሉ፡፡ የታመመ ሰው አከም ቢሉኝ ጥሩ ነኝ!፤ በጭንቀት ያለ ሰውን ካውንስል አድርግ ብባል ይሆንልኛል!፤ በአንድ ሀሳብ ላይ ተዘጋጅተህ ሌክቸር ስጥ ተብዬ ብጋበዝ ይዋጣልኛል!፤ የእግዚአብሔርን ቃል ስበክ.... አስተምር ከተባልኩ ደግሞ

ተስጥቶኛል!፤ የመንፈስ ቅዱስ ቅባት በህይወቴም በአገልግሎቴም አለ፡፡ ሌሎችም የምችላቸው አንዳንድ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ታዲያ ለእኔ ብልህነት የምችለውን ነገር ከማልችለው ለይቼ ማወቄ ነው!፡፡

አንዳንዶች "እንዴ! ኧረ እኔ ሁሉንም ማድረግ እችላለሁ!" ይሉ ይሆናል፡፡ ይህ ግን ከእውነታው በጣም ይርቃል፡፡ ሳይንሳዊም አይደለም፡፡ በውስጣችን ያለው እምቅ ብቃት (Potential) ያንዳችን ከሌላችን ይለያል፡፡ በውስጣችን ታዲያ እምቅ ብቃት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ውሱንነቶች (Limitations) ደግሞ አሉ፡፡ ይህንን ማወቅ ከአላስፈላጊ ትግል ይጠብቀናል፡፡ ለምሳሌ ድምፅና ቅባት ያልተሰጠው ዘማሪ ካሴት ላውጣ ቢል ካሴቱን የሚያደምጥለት እግዚአብሔር ብቻ ነው......... ከምህረቱ ብዛት የተነሳ!፡፡

ቋንቋን በቀላሉ የመማርና የማወቅ ችሎታ Linguistic Intelligency ይባላል፡፡ ታላላቅ የሒሳብ ጥያቄዎችን የመረዳትና የመፍታት ችሎታ ደግሞ Mathematical Intelligency ተብሎ ይጠራል፡፡ እንዲሁም ሙዚቃን የማጣጣም፣ ኮምፖዝ የማድረግና የመጫወት ችሎታ Musical Intelligency ይሰኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስዕልን የመሳልና አቅጣጫን የመለየት ችሎታ Spacial Intelligency ይባላል፡፡ የአትሌቲክስ፣ የዳንስ፣ የመድረክ ትወና ችሎታ ደግሞ Bodily-Kinesthetic Intelligency ተብሎ ይጠራል፡፡ ቀድሞ "ጥሩ ጭንቅላት ካለህ በሁሉም ነገር ጎበዝ መሆን አለብህ" የሚለውን አስተሳሰብ የለወጠልን...... ከላይ የተዘረዘሩትንም የኢንተሊጀንሲ አይነቶች አጥንቶ የከፋፈለልን ሐዋርድ ጋርድነር የተባለ ሳይኮሎጂስት ነው፡፡

ልጆቻችን ያላቸውን ልዩ ችሎታ በመለየት ብናግዛቸው ጥሩ ነው፡፡ ሁሉም ተማሪዎች እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ድረስ በተመሳሳይ ትምህርት አለም ቢያልፉም ችሎታቸው ግን ያንዱ ካንዱ ይለያል፡፡ እንዲያጠኑ....... እንዲያነቡ..... መምከርና መቆጣጠር ሁኔታዎችንም ማመቻቸት ተገቢ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ነገር ግን "ለምን

እንደ እከሊ ልጅ ማትስ መቶ ከመቶ አላመጣህም?" ብለን ልንቆጣቸው "ከክፍልህ ለምን ከአንድ እስከ ሶስት አልወጣህም?" ብለን ልንጮህባቸው አይገባም:: በእርግጠኝነት በውስጣቸው አንድ የተለየ ችሎታ አላቸው......... ከሌሎች የሚለያቸው!::

ጎልማሳም ሆነህ የሙዚቃ ችሎታህ እጅግ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ ሒሳብ (Mathes) ከተገዳደረህ ምንም ህሳብ አይግባህ:: አንድ ትልቅ ሰው "የሒሳብ መምህሬን እስከ ዛሬ ድረስ ሳስታውሰው እደነግጣለሁ!" ያሉት ትዝ ይለኛል...... የሒሳብ ትምህርት ወይም ማቲማቲክስ ታሪካዊ ጠላታቸው ነበርና ነው!:: እንግዲህ ሁሉ ነገር ስላልተሰጠን በተሰጡን ስጦታዎች ላይ በማተኮር ትልቅ ስራ መስራት እንችላለን:: በማንችለው ላይ ዘመናችንን ካሳለፍን ግን እንከስራለን!::

## የጥበብ እንቁ 14

# መለወጥ የማይቻለውን መቀበል !

ቅድስት ማርያም የዘጠኝ ወር እርጉዝ ሆና ከዮሴፍ ጋ ወደ ቤተልሔም ይሁዳ በሔደች ጊዜ የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ነበር፡፡በዚያም ስፍራ ብዙ ህዝብ ለመቆጠር ስለመጣ የእንግዳ ማረፍያ አልነበረም..... ሞልቶ ነበር ፡፡ የተገኘላቸውም ቦታ የከብቶች ግርግም ብቻ ሆነ (ሉቃ 2፡7)፡፡ ሌላ አማራጭ ስላልነበራቸው ዮሴፍና ማርያም በዚያ ግርግም አረፉ!፡፡ ለጊዜው መለወጥ የማይችሉትን ተቀበሉት፡፡

በህይወታችን የሆኑብን አንዳንዶቹ ነገሮች ልንለውጣቸው የማንችላቸው ናቸው፡፡ የህክምና ተማሪ እያለሁ በጣም እጓጓ የነበረው ትምህርቴን ጨርሼ እናቴን ለመርዳት ነበር፡፡ የሚያሳዝነው ግን የሶስተኛ አመት ተማሪ ሆኜ እናቴ በሞት መሸጋገርያነት ወደ እዚያኛው ቤት ሔደች፡፡ በጊዜው በጣም አዘንኩ!፡፡ ነገር ግን ልለውጠው የማልችለው ነገር ነበር ፡፡ እርሶስ በሞት ያጡት የቅርብ ዘመድ..... የቤተሰብ አባል አለ? ማጣቶን ይቀበሉት!...... ሊለውጡት አይችሉምና!፡፡

አንድ ጊዜ ንጉስ ዳዊት ያደረገው ነገር ያስገርመኛል፡፡ ከቤርሳቤህ የተወለደው ትንሹ ልጁ በጠና ታመመበት፡፡ ዳዊትም ምግብ አልበላም ብሎ መሬት ላይ ተኝቶ ነበር፤ ቆይቶ ልጁ ሞተ!፡፡ በዚህ ጊዜ አሽከሮቹ "ታመመ ሲባል እንደዚያ ከሆነ ሞተ ካልነውማ እንዴት ይሆናል" ብለው በጣም ፈሩ፡፡ ዳዊት ግን ሲንሾካሾኩ ሲሰማ ልጁ መሞቱ ገባው፡፡ ተነስቶ ታጠበ!፤ ተቀባ!፤ ምግብ አቅርቡልኝ ብሎም በላ!፡፡ በዚህ የተገረሙ አሽከሮቹ ቢጠይቁት "በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደ እርሱ እሔዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም" አላቸው (2ኛ ሳሙ 12፡15-23)፡፡ መቀበል ማለት እንዲህ ነው!፡፡

ልክ እንደዚሁ ደግሞ ከእኛ ቁጥጥር ውጪ የሆኑ ሌሎች ያለፉ ነገሮች አሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ያለፉ ነገሮቻችን ላይ ስልጣን የለንም፤

አልፈዋልና!፡፡ "ትላንትና ሔዷል..... ነገም ገና አልመጣም....... እንግዲያውስ ዛሬ እንደ አዲስ እንጀምር!" ያሉት ማዘር ቴሬዛ ናቸው፡፡ ካለፈው ተምረን..... ነገን የተሻለ ለማድረግ ወስነን ማለፍ ነው እንጂ በመፀፀት ጊዜያችንን ማባከን የለብንም፡፡ "በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ!" እንዳለ ሐዋርያው ጳውሎስ (ፊሊ. 3፥13)፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በአደጋ ምክንያት አካላቸውን ያጡ ይኖራሉ፡፡ የሆነባቸው ያሳዝናል!፤ ነገር ግን የሆነውን መለወጥ አይቻል ይሆናል፡፡ ስለዚህ ይቀበሉታል...... እንደ ማንኛውም ሰው በደስታ ይኖራሉ........ በሙያቸው በብቃት ይሰራሉ!፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በህይወቴ ካጋጠሙኝ ታላላቅ ሰዎች መሀል ሁለቱ በዊልቼር ተቀምጠው ያሉ ናቸው፡፡ የአካል ጉዳት ምንም እንደማያጎድል ያሳዩኝ ጀግኖች ሆነው አገኘኋቸው!፡፡ ደግሞ የነገንስ ማን ያውቃል.... ጌታ እንደሁ ከዊልቼር ማስነሳትም ያውቃል!፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ልባችንን የሚያሳዝኑ ትናንሽ ነገሮች ይፈጠራሉ፡፡ ለምሳሌ እቃ....... ሞባይል ይጠፋብናል፡፡ እንፈልጋለን ....... እናመለከታለን....... አልተገኘም!፤ በቃ ጠፋ!፡፡ ልንለውጠው አንችልም፤ እግዚአብሔር ሌላ ይተካልናል፡፡አንድ ቦታ ለስራ አመልክተህ ይሆናል፤ አልተቀበሉህም!፤ ስራው ለሌላ ሰው ተሰጠ!፡፡ ምንም አይደለም!፤ ወይ ሌላ ቦታ ይቀበሉሀል ወይም የራስህን ድርጅት ትጀምራለህ፡፡

የማይለውጡትን መቀበል ከከፋ ሀዘን ይጠብቃል፡፡አንድ በጣም የምወደው የቅርብ ወዳጄን ባለቤቱ ጥላው ወደ አንድ አገር ሔደች፡፡ መደወልም ቀነሰች!፤ ጭራሹኑ አንድ ቀን "በቃ አልፈልግህም! አልመጣም!" አለችው፡፡ አብዝታም ሰደበችው!፡፡ ያ ወዳጄ በጣም ሲበሳጭ አየው ነበር፡፡ "እንግዲህ ጌታ ልቧን ቀይሮ ከመጣች መጣች ያለበለዚያ ግን የማትለውጠውን ነገር ተቀበለው" እያልኩ ልመክረው ሞከርኩ፡፡ እርሱ ግን አልቻለም፤ በብስጭት በጣም ተጎዳ፡፡ ያለመቀበል መዘዝ ደረሰበት!፡፡

# የጥበብ እንቁ 15

## የሚዋጉትን ጦርነት መምረጥ !

ሔሮድስ ህፃኑን ኢየሱስን ለመግደል ፍለጋ ጀመረ:: ዮሴፍና ማርያምም ዮሴፍ ባየው ህልም መሰረት ህፃኑን ይዘው ወደ ግብፅ ሸሹ (ማቴ 2፡13):: ግን ለምን ሸሹ? ሔሮድስን ለምን አልተጋፈጡትም? ምነው ዮሴፍ ወንድ አይደል እንዴ!፤ እንዴት ይሸሻል?፤ ዞር ማለትን ለምን መረጡ?

አንዳንድ መጋፈጥ ያለብን ሁኔታዎች አሉ፤ አንዳንዱን ግን እንሸሸዋለን!:: በመንገድ ላይ ተሳዳቢ ሰዎች ቢሰድቡኝ ቆሜ አልሰዳደብም..... ወይም አልደባደብም:: ያን ባደርግ ችግር ውስጥ የምገባው እኔው መሆኔን አውቃለሁ:: ጉልበት በዝቶልኝ ብደበድብ...... እስር ቤት እገባለሁ!....... ብደበደብ ደግሞ እዋረዳለሁ!፤ ደግሞ እኔ ልሞክረው ብልም መደባደብ አልችልበትም:: ስለዚህ በሰላም ከዚያ ስፍራ ዞር ማለት ነው ያለብኝ!፤ አያድርገውና አልፈው ከመጡ..... ፖሊስ መጥራት ጥሩ መፍትሔ ነው!::

አንዳንድ ሰዎች መኪና እየነዱ በእጃቸውም በአፋቸውም ሊሳደቡ ይችላሉ:: እኔ መልሼ እንደነርሱ ማድረግ አልችልም:: ምንም አይነት ብሽቅ ይግጠመኝ ዋጥ አድርጌያት አልፋለሁ:: አንድ ጊዜ እሮብ ምሽት የእግዚአብሔርን ቃል ለማካፈል ወደ አንድ ቤተ-ክርስትያን እየነዳሁ እያለ ከጎኔ የመጣ መኪና በጣም በሚያበሳጭ ሁኔታ ከፊቴ ጥልቅ ብሎ ገባ:: እግዚአብሔር ሲረዳኝ "አይዞህ ምንም ችግር የለም! It is Ok!" አልኩት..... የሚሾፍረውን ሰው:: ሶስት ሰዎች ጭኗል!፤ መንገዱን ቀጠለ..... እኔም ቀጠልኩ:: ከፊት ለፊቴ ሲሔዱ ቆዩና እኔ እየሄድኩበት ወደነበረው የቤተ-ክርስትያን ግቢ አዞረው ገቡ:: ለካ እነርሱ የእኔን ስብከት ለመስማት ወደ ቤተ-ክርስትያን እየሔዱ ነበር:: ስሜታዊ ሆኜ ተናግሬያቸው ቢሆንስ? ለማስተማር እመድረኩ ላይ ስቆም እንዴት በተቸገሩ ነበር!::

አንዳንድ ችግሮች ሲመጡ ዞር ማለትን መልመድ አለብን፡፡ መሸሽ ያለብንንና መሸሽ የሌለብንን መለየት ይገባናል፡፡ ለምሳሌ ሰይጣንን በመንፈሳዊ ውጊያ እንዋጋዋለን እንጂ አንሸሸውም....... ጎረቤታችን ጠንቋይ ገብቷል ብለን ቤት አንለቅም፡፡ ዝሙትን ግን እንሸሸዋለን እንጂ አንዋጋውም!፡፡ ጎልማሳው ወገኔ በጣም የሚፈትን ሁኔታ ውስጥ ተቀምጦ....... አጭር ቀሚስ...... የተገለጠ ሰውነት...... አማላይ ፈገግታ..... እያየ "በኢየሱስ ስም!" እያለ ቢገስፅ ተቀባይነት የለውም!፤ አቅሙን አውቆ ውልቅ ብሎ መውጣት ነው ያለበት፡፡

አንዳንድ ቤተሰብ ውስጥ ወንድም ከወንድሙ፣ እህት ከእህቷ የሚዋጉበት ጊዜ አለ፡፡ የገዛ እህቱን ያስጨንቃታል....... የገዛ ወንድሟን አበሳውን ታሳየዋለች፡፡ ባልና ሚስትም በቤት ውስጥ የማያባራ........ አሸናፊ የሌለበት ጦርነትን ያደርጋሉ........ በምሽት ይናቆራሉ........ ሁለቱም እንቅልፍ አጥተው ሲገላበጡ ያድራሉ!፡፡ እግዚአብሔር በትዳር ያስተሳሰራቸው አንድ ሆነው የምድርን ኑሮ እንዲያሸንፉ...... በበረከትም እንዲኖሩ ነበር፡፡እነርሱ ግን ትዳሩን የጦር ሜዳ ያደርጉታል!፡፡

በቤተ-ክርስትያንም ያለ ጦርነት ደግሞ አያድርስ ነው፡፡ አለመግባባትን በመነጋገር በመፍታት ፋንታ የነገር ጥይትን ይታኮሳሉ፡፡ በአሽሙር ጦር ይወጋጋሉ፡፡ ይህ ጦርነትን ያለመምረጥ ችግር ነው፡፡ ለዳዊት ግን አቢጊያ እንዲህ አለችው "አንተ የእግዚአብሔርን ጦርነት ስለምትዋጋ እግዚአብሔር የታመነ ቤትን ይሰራልሀል!" (1ኛ ሳሙ 25፡28)፡፡ ለካ ዳዊት የሚዋጋው የእግዚአብሔርን የፅድቅ ጦርነት እንጂ የራሱን ጦርነት አልነበረም፡፡ ለዚህም ደግሞ "የታመነ ቤት" ሽልማት ሆኖ ተዘጋጅሎታል፡፡

# የጥበብ እንቁ 16

## በትዕግስት መጠበቅ !

ቅድስት ማርያም ታላቅ ትዕግስት የታየበት ኑሮ ነው የኖረችው፡፡ ብዙ መጠበቅ...... መታገስ ነበረባት!፡፡ ከዮሴፍ ጋ ህፃኑን ኢየሱስን ይዛ ወደ ግብፅ ከሸሸች በኋላ "የህፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋል" ብሎ ጌታ "ተመለሱ" እስኪላቸው ድረስ ታግሳ መጠበቅ ነበረባት፡፡ "ከሀጢያታቸው ያድናቸዋል" የተባለለት ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገልጦ እስኪያገለግል ድረስ ደግሞ 30 አመት መጠበቅ ነበረባት፤ በግፍ የተገደለው ልጇ ከሙታን እስኪነሳ ድረስም ሶስት ቀን ታግሳ ጠብቃለች፡፡ ብቻ ህይወቷ ብዙ ትዕግስትን....... ብዙ ጥበቃን የሚጠይቅ ነበር፡፡

በምድር ላይ ከእግዚአብሔር ጋ ስንኖር አንድ መልመድ ያለብን፣ ትዕግስታችንን የሚፈታተን ነገር 'መጠበቅ' የሚባለው ነው፡፡ ጌታ ደግሞ እስኪደርስልን..... እስኪመጣልን...... እስኪፈርድልን ያስጠብቀናል፡፡ "በለሱን የሚጠብቅ ፍሬዋን ይበላል፤ ጌታውን የሚጠብቅ ይከብራል!" እንደሚል ቃሉ የልብዎን መሻት እስኪሰጦት መጠበቅ የግድ ነው (ምሳሌ 27፡18)፡፡

አንድ ጊዜ ለአንዲት የ 3 አመት ህፃን ልጅ ብርቱካን እየላጥኩላት ነበር፡፡ «ስጠኝ!» አለችኝ......... «እየላጥኩልሽ ነው አልኳት»....... ትንሽ ቆየችና «ስጠኝ እንጂ!» አለችኝ........ «እሺ ሚሚዬ! ልጣጩ ልስጥሽ ብዬ ነው አልኳት»፡፡ በዚህ ጊዜ «አልሰጥም አልከኝ!» አለችና እሪ ብላ አለቀሰች፡፡ «እንዴ! እኔኮ ላንቺ ብዮ ነው!..... ልጣጩ ይመርሻ!...... አንቺ ብትልጪው ደግሞ አይንሽን ያቃጥልሻል» አልኳት፡፡ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ነገር አስተማረኝ፡፡ ከአምላካችን አንድ ነገር ስንፈልግና ስንጠይቀው ፀሎታችንን ወዲያው ይሰማል፡፡ ነገር ግን የጠየቅነውን ነገር የሚሰጠን ልጦ...... የሚመረውንና አይናችንን የሚያቃጥለውን ልጣጭ አስወግዶ ነው፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ ያስጠብቃል..... ጊዜ ይወስዳል!፤ ታዲያ እርሱ ለእኛ

እየላጠልን እያለ እንደ ህፃናት ልጅ ማልቀስ እንጀምራለን፡፡ "እግዚአብሔር አይወደኝም!" እያልን እናጉረመርማለን........ እናማርራለን፡፡

ከሳይንስ ክፍሎች ውስጥ ኢምብርዮሎጂ (Embryology) የሚባለው ዘርፍ ያስደንቀኛል፡፡ ልጅ በሴት ማህፀን ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ የሚያስረዳ ትምህርት ነው፡፡ አንዲት የሴት እንቁላል (Ova) በሚሊዮን በሚቆጠሩ የወንድ የዘር ሴሎች (Spermatozoa) ትከበባለች፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የወንድ ሴል አቅም አግኝቶ ወደ ሴቷ እንቁላል ይገባል፡፡ ከዚያም የረቀቀ ውህደት ይሆንና አንድ አዲስ ሴል (Zygot) ይሰራል፡፡ ያ አንዱ ለሁለት ይከፈላል...... ሁለቱ ደግሞ አራት ይሆናሉ........ አራቱ ስምንት ይሆናሉ፡፡ ስምንት ሴል ደረጃ ላይ ሲደርስ ሞሩላ (Morula) የሚባል ነገር ይሰራል፡፡ ያም ሞሩላ በማህፀን ላይ ይጣበቅና እድገት ይቀጥላል፡፡ እንግዲህ ከዚያች የስምንት ሴል ጅማሬ ነው የህፃኑ አንጎል....... ነርቮቹ.... ልቡ .....ሳንባው..... ኩላሊቶቹ..... ጉበቱ..... አጥንቶቹ........ መላው አካላቱ የሚሰራው፡፡ በዘጠኝ ወር ጊዜ ውስጥ አንድ የሚያምር ህፃን ተሰርቶ ይወጣል፡፡

እኔ ለአንባቢ እንዲቀል አስቤ አሳጥሬው ነው እንጂ ሒደቱ እጅግ አስገራሚና ውስብስብ ነው ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ታዲያ እናት ምን ብትጓጓ መጠበቅ ግዴታዋ ይሆናል፤ በትዕግስት ትጠብቃለች!፤ ልጁ በማህፀኗ ውስጥ እየተሰራላት ነው!፤ እያደገላት ነው!፤ ህፃኑም በዚያ በጠባብ ስፍራ የግድ መጠበቅ አለበት!..... ያም ደግሞ ለጥቅሙ ነው፡፡ ሙሉ አካል እንዲሆንለት!፡፡

እርሶም እግዚአብሔርን በትዕግስት ይጠብቁት፡፡ እርሱ አይዘገይም!፤ በትክክለኛው ሰአት (On time) ይመጣል!፡፡ በእግዚአብሔር መንግስት አሰራር መጠበቅ የግድ እንደሆነ ይገንዘቡ፡፡ በየትኛውም ጉዳይ እግዚአብሔርን መቅደም ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ንጉሱ ሳኦል ለጥቂት ደቂቃዎች መታገስ አቅቶት ነው ትልቅ ችግር ውስጥ የገባው፡፡ ይታገሱ!፤ በትዕግስት ይጠብቁ! ...... እግዚአብሔርን ጠብቀውት አያፍሩምና!፡፡

## የጥበብ እንቁ 17

# ትክክለኛ ጊዜን ማወቅ !

ቅድስት ማርያም ነገር ሁሉ በጊዜው ውብ እንደሚሆን ታውቅ ነበር፡፡ ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው መጠበቅን፣ መታገስን ተምራለች፡፡ ትጠብቅና ግን ልክ ጊዜው መሆኑን ስታውቅ ትንቀሳቀሳለች፡፡ ለምሳሌ በግብፅ የቆየችበት ጊዜ ሲያበቃ ወዲያው ወደ አገርዋ ለመመለስ ተነሳች፡፡ "ቆይ አስቲ..... ትንሽ ልክረም" አላለችም፡፡ በትክክለኛው ጊዜ ትክክለኛውን ነገር ታደርግ ነበር፡፡

'ኢምብርዮሎጂ' ልጅ በማህፀን ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ያጠናል ብለን እንስተነው ነበር ባለፈው ምዕራፍ፡፡ ከህክምና ሳይንስ ደግሞ በነፍሰ ጡር ሴቶችና በወሊድ ላይ የሚያተኩረው ክፍል ኦብስቴትሪክስ (Obstetrics) ይባላል፡፡ ታዲያ ይህ ዘርፍ እንደሚያስተምረን ልጅ የሚወለድበት ትክክለኛው ጊዜ ከ 37ኛው እስከ 42ኛው የእርግዝና ሳምንታት ውስጥ ነው፡፡ ከ 37ኛው ሳምንት በፊት ከተወለደ "Preterm" ይባላል፡፡ ልጁ ያለጊዜው ስለተወለደ ብዙ ችግር ያያል፡፡ ሳምባው በሚገባ ስላልተዘጋጀ መተንፈስ ያስቸግረዋል....... የተለያዩ ኢንፌክሽኖች (Infections) ያስቸግሩታል....... ጃንዲስ (Jaundice) ይኖረዋል.... ሌሎችም ብዙ ችግሮች ይገጥሙታል፡፡ የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ምንድን ነው? ያለ ጊዜው መወለዱ ነው!፡፡ ከዚህም በጣም ቀድሞ በ 26ኛው ሳምንት ቢወለድ ደግሞ ውርጃ ነው!፡፡

እኛም ያለ ጊዜው የምናደርጋቸው ነገሮች እንዲሁ አይነት ችግሮች ይገጥሟቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ የሆነን ነገር ትክክለኛ ባልሆነ ጊዜ እናደርግና ብዙ ዋጋ እንከፍላለን፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ሆቴል ለመክፈት ራዕይ ይኖረዋል፡፡ ግን ጊዜውን ሳያውቅ በጣም ቀድሞ ካደረገው ሊበላሽበት

ወይም ሊደናቀፍበት ይችላል፡፡ ራዕይው ትክክል ነው..... ጊዜውን ግን አላወቀውም!፡፡

በተቃራኒው ደግሞ ልጅ ከ42ኛው ሳምንት በላይ ሳይወለድ ከቆየ "Post Term" ይባላል፡፡ በጊዜው ስላልተወለደ ብዙ ችግሮች ይገጥሙታል፡፡ በወሊድ ጊዜ ጭንቅላቱ ለማለፍ ያስቸግረዋል....... ትከሻውም ሊሰበር ይችላል፡፡ ከዚህም ሲከፋ ሳይወለድ ብዙ ከቆየ በማህፀን ውስጥ የመሞት አደጋው ይጨምራል፡፡ የዚህ ሁሉ ችግር ምክንያቱ ምንድነው? በትክክለኛ ጊዜው አለመወለዱ...... ጊዜውን ማሳለፉ ነው!፡፡

ልክ እንደዚሁ ራዕይ ያላቸው ሰዎች ትክክለኛ ጊዜውን አልፈው በጣም ሊዘገዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ አሜሪካ የሚኖር ሰው ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ አንድ ስራ ለመስራት ያስባል፡፡ ግን ልክ መሆኑን ልቡ እያወቀ..... ያመነታል...... ይወላውላል፡፡ "ኢትዮጵያ ገብቼ ቺከን ባይኖርስ?" ይላል..... "መብራት ደግሞ ይጠፋልኮ!" ይላል..... "ሙቅ ሻወር ባይኖርስ?" ብሎ ደግሞ ይሰጋል፡፡ በዚህ መሀል አመታቶቹ ያልፋሉ፡፡ በጣም ቆይቶ ወስኖ ሲመጣ እርሱ ሊሰራ ያሰበውን ስራ ሌሎች ቀድመው መጥተው ሰርተውታል፡፡ ጥቁር መነፅራቸውን አድርገው V8 ላንድ ክሩዘር እየነዱ በአጠገቡ እያፏጩ ያልፋሉ፡፡ የእርሱ ችግር ጊዜውን አለማወቁ ነው!፡፡

ሰው ጊዜን ማወቅ አለበት፡፡ ለመማር ጊዜ አለው...... ለመስራት ጊዜ አለው......... ለማግባት ጊዜ አለው....... ለመውለድ ጊዜ አለው፡፡ "ለሁሉም ጊዜ አለው" ይላል መፀሀፍ ቅዱስ (መክ13፡1-2) ፡፡ ታዲያ እርሶ መማር ባለቦት ጊዜ ይማሩ ፡፡ ማግባት ባለቦት ጊዜ ደግሞ ዙረትን አያብዙ...... ያግቡ እንጂ!፤ ባስቸኳይ ጉዳዮትን መፈፀም ባለቦት ጊዜ ጃኩዚ ገብተው ቁጭ አይበሉ፡፡ ጊዜውን ይወቁ! Timing ወሳኝ ነው፡፡ እግዚአብሔርም በጊዜው ውብ አድርጎ ይሰራዋል፡፡ ብዙ ነገር ሞክረው አልሆን ብሎት ከሆነ ደግሞ ጊዜው ስላልነበረ ነው፡፡ ግዴለም ይታገሱ!፤ ሌሊቱን በሙሉ አሳ ሲያጠምዱ አንድም አሳ መያዝ አቅቶት ቢሆን ትክክለኛው ጊዜ ሲመጣ መረብዎ እስኪቀደድ ድረስ አሳን ይሞላሉ!፤ ለመጎተት እስኪቸገሩ ድረስ በረከትዎ ይበዛል፡፡

# የጥበብ እንቁ 18

## በመከራና በስቃይ መፅናት !

መቼም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለውን መከራና ስቃይ ያህል ማንም አልተቀበለም፡፡ እርሱ ህመማችንን ተሸከመ........ ስለ ሀጢያታችን ደቀቀ....... የደህንነታችን ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበረ....... ተጨነቀ....... ተሰቃየ!፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ እንደሚታረድ በግ ዝም አለ፤ ዝም ብሎ...... ሀጢያት የሌለበት እርሱ አስጨናቂ መከራን ተቀበለ!፡፡ እኔ መገረፍ የነበረብኝን እርሱ ተገርፎልኛል!...... የእኔ እጅና እግር በሚስማር መቸንከር ሲኖርበት የእርሱ ተቸንክሮልኛል!...... የእኔ የሀጢያተኛው ደም መፍሰስ ሲኖርበት የእርሱ ክቡር ደም ስለ እኔ ፈሷል፡፡ ስለዚህም የእርሱን መከራ ከማንም ጋ ልናወዳድረው አንችልም፡፡

ነገር ግን ኢየሱስ ለቅድስት ማርያም ልጇ ነው!፤ የሚያልፍበት መከራ ሁሉ ይመለከታት ነበር፡፡ ተቃውሞ ሲበዛበት እየሰማች ትሳቀቃለች!፤ ሲቀኑበት....... ሲጠሉት ስታይ እንደ ማንኛዋም እናት ይሰማታል፡፡ በውሸት ሲያስወሩበት የልጇን ንፁህነት ስለምታውቅ በልቧ ታነባለች፡፡ ሊገድሉት እንደሚፈልጉት ስትሰማ....... "አምላኬ! እንዴት ታደርገኝ ይሆን? ልጄን ሊገድሉት ይፈልጋሉኮ!" ትላለች፡፡ በተለይ በተለይ አልፎ በተሰጠበት በዚያን ጊዜ እየደረሰበት የነበረውን ስቃይ እየሰማችና እያየች በስሜቷ አብራ ተሰቃይታለች፡፡ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ....... በደም ተለውሶ ሲያጣጥር ማርያም እዛ ቆማ ነበር!፡፡ የሚሰማትን ስቃይ ማንም ልጅ ያላት እናት ልትረዳው ትችላለች፡፡ የትኛዋም እናት በዚህ ውስጥ ብታልፍ አእምሮዋን ልትስት (Nervous breakdown) ትችላለች፡፡ በዚህ ሁሉ መከራና ስቃይ ግን ማርያም ፀንታ ቆማለች!፤ በእውነት አስገራሚ ነው!፡፡

መከራና ስቃይ (suffering) በምድር ላይ ልናሳልፋቸው ግድ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡ በተለይ ደግሞ በእግዚአብሔር ለታላቅ ስራ ከታጩ መከራዎ

ብዙ ነው የሚሆነው:: እግዚአብሔር የከበረ እቃ አድርጎ የሚሰራዎት በመከራ ውስጥ ነው:: መንፈስ ቅዱስ  አልማዝን ምሳሌ አድርጎ እንዲህ አስተማረኝ  :: አልማዝ (Dimond) ከከሰል (Coal) ብዙ ልዩነት እንዳለው ግልፅ ነው........ ለማወዳደርም አይቻልም:: በጣም የሚያስገርመው ግን ሁለቱም የሚሰሩት ከአንድ ነገር መሆኑ ነው........ ከካርበን (Carbon):: ታዲያ በሁለቱ መሀል ያለው ልዩነት የሚመጣው አልማዝ ከሚያሳልፈው የመከራ ብዛት የተነሳ ነው::

አልማዝ የሚሰራው ከምድር በታች ከ 300 እስከ 600 ኪሎ ሜትር ጥልቀት ውስጥ ነው:: መውረድ....... መዋረድ አለበት!:: በዚያ ጥልቀት ደግሞ አልማዝ 'አልማዝ' ሆኖ ለመስራት እስከ 1200 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ቃጠሎ ውስጥ....... በከፍተኛ ግፊት (Pressure)....... ለረዥም ዘመናት መቀመጥ አለበት:: ከሰልም እነዚህ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ካገኘ ወደ አልማዝነት መለወጥ ይችላል:: ይህ ስለታወቀ ነው በላቦራቶሪ ውስጥ HPHT (High Pressure, High Temperature) በሚባል ሂደት አልማዝን መስራት የተቻለው::

እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ ባላለፈ የ "ከሰል ስብዕና" ታላቅ ስራን አይሰራም:: ለታላቅ ስራ የተመረጠው ሰው የ "አልማዝ ስብዕና" እንዲኖረው ይፈልጋል!፤ ስለዚህም ያንን የተወደደ ሰው ከጓደኞቹ በታች ያደርገዋል...... ከ 300-600 ኪሎ ሜትር!:: ይህም ብቻውን በቂ ስለማይሆን ያን ምርጥ ሰው በከፍተኛ መከራ ውስጥ ያሳልፈዋል...... የ 1200 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ቃጠሎ!:: የኑሮ መንገላታቱም ይበዛል...... ከፍተኛ ግፊት (Pressure) !:: ያ በእግዚአብሔር የተወደደና የተመረጠ ሰው ለአመታት በዚህ ሁኔታ አልፎ "የአልማዝ ስብዕና" ን ይዞ ይወጣል::

እርስዎ በእንዲህ አይነት መከራ ውስጥ አልፈው ከሆነ.... "እግዚአብሔር ከጓደኞቼ በታች አደረገኝ!" ብለው ከሆነ..... "የእኔስ አበሳ በዛ!" ብለው አዝነው ከሆነ.... "እግዚአብሔርን ምን አደረኩት?" ብለው አማረው ከሆነ ይህ መልዕክት ይሁንሎት:: እርሱ አምላክ ስለወደዶት...... ታላቅን ስራ በእርሶ ሊሰራ ስለመረጦት ነው በዚህ መንገድ ያለፉት:: ለክብሩ መገለጫ

"አልማዝ" አድርጎ ሰራዎት!.... የ "አልማዝ ስብዕና" ተሰጦት፡፡ ያመስግኑ እንጂ አያማሩ!፡፡

በመከራ ውስጥ ያለፉ ሰዎች ውድ ናቸው....... በቀላሉ አይገኙም!፤ አልማዝ እኮ ውድ ነው፡፡ አንድ አልማዝ በ 25 ሚሊዮን ዶላር ተሸጦ ያውቃል፡፡ አልማዝ ያላቸው አገሮች........ እንደ ብራዚል፣ አውስትራሊያ፣ ካናዳ፣ ህንድ፣ ሳውዝ አፍሪካ ያሉት....... ብዙ ሀብትን ያገኙት በአልማዝ ምክንያት ነው፡፡ በአፍሪካም...... እንደ አንጎላ፣ ሴራሊዮን፣ ኮትዲቯር፣ ላይቤርያ.... የመሳሰሉት አገሮች አልማዝን ያወጣሉ፡፡ አንዳንዴም በእርሱ ምክንያት ይዋጋሉ፡፡ እርሶም በመከራ አልፈው ሲወጡ የሀገር ሀብት ሆነው ነው የሚገለጡት፡፡

የ "አልማዝ ስብዕና" ያላቸው ሰዎች የአልማዝ ባህሪያት ይታዩባቸዋል፡፡ በምድር ላይ ያለው የመጨረሻው ጠንካራ ነገር አልማዝ ነው፡፡ አልማዝ ብረትን ይቆርጠዋል እንጂ ብረት አልማዝን አይቆርጠውም፡፡ መከራ ሰውን እንዲህ መንፈሰ ጠንካራ ያደርገዋል...... በመከራ ያለፈ ሰው ቆፍጠን ይላል!፡፡

ሌላው የአልማዝ ባህሪ ደግሞ የተቀበለውን ብርሀን በልዩ ሁኔታ የማንፀባረቅ ችሎታውና (Refractive Index) ያንኑ ብርሀን ወደ ተለያዩ ቀለማት መበታተኑ (Dispertion Value) ነው፡፡ ቀስተ ዳመናን ያወጣል!፡፡ እርሶም በመከራ ካለፉ በኋላ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያንፀባርቁ የቃልኪዳን ሰው ይሆናሉ፡፡

አልማዝ በጣም ንፁህ (Pure) ነው፡፡ ቆሻሻ ተብሎ ውስጡ ቢገኝ ናይትሮጂን ብቻ ነው፡፡ በእውነተኛ መከራ ውስጥ ያለፈ የ "አልማዝ ስብዕና" ያለው ሰውም ንፁህ ነው!፤ የጥላቻ ቆሻሻ...... የቂም ቆሻሻ...... የዘረኝነት ቆሻሻ....... የጠማማነት ቆሻሻ አይገኝበትም፡፡ የመከራ ሰው ከነዚህ የፀዳ ነው የሚሆነው፡፡

ሌላው እጅግ አስገራሚ የአልማዝ ባህሪ በእሳት አለመቃጠሉ ነው፡፡ አይቀልጥም....... አይቃጠልምም!፡፡ አሲድ (Acid) ውስጥ ቢነክሩት

አይበላሽም!፤ ከዚያ አውጥተው ተቃራኒው በሆነው ቤዚክ (Basic) የሆነ ፈሳሽ ውስጥ ቢነክሩት ምንም አይሆንም፤..... እርሱ አልማዝ ነው!::

በመከራ ካለፉና የ "አልማዝ ስብዕና" ን ከያዙ በኋላ በቀላሉ እርሶን ማጥፋት አይቻልም!፤ ሰዎች የተንኮል እሳትን በዙሪያዎ ቢያቃጥሉ...... የእርሶን ስራ ሊያቃጥሉት አይችሉም!፤ በለመደ እጃቸው የነገር አሲድን ሊያፈሱቦት ቢሞክሩ...... አያበላሾትም!፤ በመከራ ውስጥ አልማዝ ሆነው ተሰርተዋልና ነው።፡

ከአመታት በፊት በሳውዝ አፍሪካ ኦሬንጅ ካውንቲ የተባለ ቦታ አንድ ህፃን ልጅ ሲጫወት አንዲት ጠጠር ያገኛል፡፡ ለየት ያለች ጠጠር!፤ ታዲያ ልጁ ያቺን ጠጠር ወስዶ ለአባቱ ይሰጠዋል፡፡ አባቱም ወስዶ ቢያስመረምራት አልማዝ ሆና ተገኘች፡፡ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው ለመጀመርያ ጊዜ በሳውዝ አፍሪካ አልማዝ የተገኘው፡፡ እርሶም የአልማዝ ስብዕና ከተሰጦት በኋላ አንድ ሰው ያገኞታል!፤ ማን መሆንዎ ሲገለጥ "ጠጠር ነው" ብለው የናቁዎት ሁሉ እርሶ አልማዝ እንደሆኑ ይደርሱበታል፡፡

በተፈጥሮ አልማዝ ከተሰራበት ጥልቀት የሚወጣው በቮልኬኖ ነው፡፡ ቮልኬኖው መሬት ላይ አውጥቶ ያፈስዋል!፤ ከዚያም ይለቀማል..... ቅርፅ ይሰጠዋል.... ይወለወላል (Collecting, Cutting, Polishing) ይባላል። ከዚያም ለገበያ ይቀርባል፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር በመከራ ውስጥ አሳልፎ አልማዝ አድርጎ የሰራው ሰውም በደንብ ተቀርፆ...... ተወልውሎ በደተዘጋጀለት ታላቅ ስራ ይገባል፡፡ ትልቅ ቁም ነገርም በእርሱ ይሰራል!::

አንዱ አልማዝ ከሌላው አልማዝ ይለያል፡፡ በንፁህነቱ፣ በቀለሙ፣ በአቆራረጡ እና በካራቱ ይለያያል። እነዚህን አራቱን 'The 4 C' ይሏቸዋል (Clarity, Color, Carat, Cutting)፡፡ እርሶም ብዙ ተሰቃይተው ከሆነ ከሌሎቹም አልማዞች በስብዕናዎ የተሻሉ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ሁሉ አሳልፎ የአልማዝ ስብዕናን የሰጦትን እግዚአብሔርን ያመስግኑ! ስለወደዶትና ስለመረጦት እንጂ ስለጨከነቦት አይደለምና!::

# የጥበብ እንቁ 19

## ሌሊቱ እንደሚነጋ ማመን !

ያን ታላቅ መከራ የተቀበለው ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ተቀበረ፡፡ መቃብሩም በትልቅ ድንጋይ ተዘጋ፡፡ ደግሞም ታተመ!፤ ይህ ታዲያ በእናቲቱ በማርያም ላይ የህይወት ጨለማ ነው ያመጣባት፡፡ ያ ደግ ልጇ ተቀብሯል! ሊቀካህናቱ ተደስተዋል........! ወታደሮቹ ተሳክረዋል......! ደቀመዛሙርቱ ተበታትነዋል......! ለእርሷ የብቸኝነት ጊዜ ነው፡፡ በህይል ጨልሞባታል! ሌሊት ሆኖባታል!፤ ቅድስት ማርያም ግን ሌሊቱ እንደሚነጋ ታምን ነበር፡፡ ጨለማው በበረታ ቁጥር ሊነጋ እንደሆነ ትረዳለች፡፡ እውነትም ታዲያ በሶስተኛው ቀን ታላቅ የምስራች ተሰማ!፤ ሽቶ ሊቀቡት ለሔዱ ሴቶች መላዕክት ተገለጡላቸውና...... "ህያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነስቷል እንጂ እርሱ በዚህ የለም!" አሉአቸው፡፡ ደስታ ሆነ!፤ ታሪክ ተሰርቷል! ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ ተነስቷል!፡፡ ይህንን ስትሰማ ..... ቆይቶም በአይኗ ስታየው...... ቅድስት ማርያም የሚሰማትን ደስታ ለመገመት እንኳን ከባድ ነው!፡፡ ሌሊቱ አልፎ ሔዷል! ጨለማውም በርቷል! ፡፡

በእኛም ህይወት ቀኑ የሚጨልምበት ጊዜ አለ፡፡ ሌሊት ይሆናል.... ሰዎች ሁሉ በእኛ ላይ ፊታቸውን ያዞራሉ....... ወዳጆቻችን ከእኛ ይርቃሉ...... ከባድ እጦት ውስጥ እንገባለን...... ወይም ህመም ይመጣል....... በሮቹ ሁሉ ይዘጋጋሉ...... መድረሻ እናጣለን....... ግራ እንጋባለን..... ብንጮህ የሚሰማ የለም........ እንዲህ አይነት ነገር ሲገጥመን ሌሊቱ እንደሚነጋ ማመን አለብን....... በእርግጥ ሌሊቱ ይነጋል!፡፡

የጌታ ደቀመዛሙርት ከባድ አውሎ ነፋስና ማዕበል የገጠማቸው በአራተኛው ሌሊት ነበር፡፡ ከሌሊቱ 9 ወይም 10 ሰአት አካባቢ ማለት ነው፡፡ በዚያ በሌሊት ታንኳቸው ስትናወጥ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በውሀው ላይ

እየተራመደ መጣ፤ ምትሀትም መሰላቸው:: እውነት ነው ለሚታመኑበት እርሱ በወሳኝ ሰአት ይመጣል:: ነፋሱንም ማዕበሉንም "ፀጥ በል! ዝም በል!" ይለዋል::

ብቻ እርሶ መታመኛዎ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ:: ታይታኒክ (Titanic) የተባለችው መርከብ ካፒቴን ስለ መርከቢቱ ሲናገሩ "እግዚአብሔር እንኳን ሊያሰጥማት አይችልም! (Not even God himself could sink her!)" ብለው ነበር:: ታይታኒክ ግን በመጀመርያው የአሜሪካ ጉዞዋ ከበረዶ ግግር ጋ ተጋጭታ ሰጠመች:: እርሶ ግን መታመኛዎን እግዚአብሔር ያድርጉ!:: ምን ሀብት ቢበዛሎት..... ብዙ እውቀት ቢኖርዎት.... ዘመድ አዝማድ፣ የወዳጅም ብዛት ዙሪያዎን ቢከቦት...... የሚታመኑት በእግዚአብሔር.... በልጁም በኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን::

ሰው በእግዚአብሔር ከታመነ..... ቀኑ ቢጨልምበት እንኳን..... ማዕበልና ወጀቡ ቢጠነክርበት እንኳን..... በወሳኝ ሰአት ታማኙ ኢየሱስ ይደርስለታል:: በ 1991 ዓ/ም (በእኛው አቆጣጠር) ዋሺንግተን ዲሲ ነበርኩኝ:: በጣም ከባድ ግራ መጋባትና ጭንቀት ገጠመኝ፤ ተስፋ ቆረጥኩ!:: በዚህ ሁኔታ እያለሁ አንድ ምሽት አርፌበት የነበረ ኮንዲሚኒየም በረንዳ ላይ ወጥቼ ዘመዴ እየሰማችኝ ከልብ የሆነ ፀሎት ፀለይኩ:: በማግስቱ ጠዋት ባልጠበኩት መንገድ ነገሩ ሁሉ ተለወጠ፤ እኔም ዘመዴም እጅግ ተደነቅን!:: አዎ! በወሳኝ ሰአት...... ኢየሱስ ይመጣል!፤...... ሌሊቱም በእርግጥ ይነጋል!::

ሌሊት የማይነጋ ቢሆን ኖሮ ኢዮብ ላይ እንደ ጨለመ ይቀር ነበር:: ያለውን ሁሉ አጥቶ...... ሰውነቱ ተልቶ በገል ፎክቷል..... ሚስቱ "እግዚአብሔርን ስድበህ ሙት" ብላው ተለይታዋለች (ኢዮብ 2:9):: የቅርብ ወዳጆቹ "የተደበቀ ሀጢያት ቢኖርብህ ነው እንጂ ፃድቅ ብትሆን ይህ መቼ ይመጣብህ ነበር እያሉ" አቁስለውታል:: ደስ የሚያሰኘው ግን የታሪኩ አጨራረስ ነው:: የኢዮብ ድቅድቅ ጨለማ በርቶ ነው ታሪኩ የሚያበቃው:: "ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንህ ሀሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ!" አስብሎታል እግዚአብሔር (ኢዮብ 42:2):: የእርሶም ጨለማ ይበራል!..... ሌሊቱ በእርግጥ ይነጋል!::

# የጥበብ እንቁ 20

## ሁሉን ይቅር ማለት!

ጌታ ኢየሱስ አልፎ የተሰጠበት ያ ጊዜ ማርያም ሁሉን የታዘበችበት ጊዜ ነው፡፡ ያንን ሁሉ መከራ ሲቀበል ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ እንኳን "ተውት እንጂ! ምን አድርጓልና ነው የምታንገላቱት፤ ተውት መምህሬን!..... ያለበለዚያ እኔን ግደሉኝ!...." ያለ አልነበረም፡፡ "እረኛውን ምታ፤ በጎቹም ይበተናሉ" የተባለው ቃል ይፈፀም ዘንድ ሁሉም ጥለውት ሔደዋል (ዘካ 13፡7)፡፡ ከአጠገቡ የማይለየው ጴጥሮስም "ሰውዮውን አላውቀውም!" እያለ ደጋግሞ ከዶታል (ማቴ 26፡70)፡፡ ለእናቲቱ ለማርያም ይህ የምታየውና የምትሰማው ሁሉ የሚያሳዝን ...... ልብን የሚሰብርም ነው!፡፡ "አይ ሰው!" የሚያስብል ነገር ነው የታዘበችው፡፡

ጨለማው አለፈና ጌታ ኢየሱስ ከሙታን በኩር ሆኖ ተነሳ፡፡ ደስታ ሆነ!....... እንደውም ወደ አባቱ አረገ!፤ እርሱ ከሔደ በኋላ እንግዲህ ማርያምን ነው ማየት!፡፡ ከጴጥሮስ ጋ ሲገናኙ ምን አለችው? ሌሎቹንስ ደቀመዛሙርት? በልጇ መከራ ጊዜ ሸሽተው የተበተኑትን ሁሉ እንዴት አናገረቻቸው? ፡፡ "አይ! የእናንተስ ነገር በቃኝ!" ብላቸዋለች? ፈፅሞ አልወጣትም!፡፡ ይልቁን ከእነርሱ ጋ ተሰብስባ ስትፀልይ እናያታለን፡፡ ሁሉን ይቅር ብላለችና ነው!፤ ጌታ ኢየሱስ ሁሉን ይቅር እንዳለ እርሷም እንደዚሁ ያለፈውን ትታዋለች..... ይቅር ብላለች!፡፡

እንደ ሐኪም ይቅር ማለትን ለሁሉ ሰው በመድሀኒት መልክ ባዝ ደስ ባለኝ!፤ ምክንያቱም ይቅርታ ለጤንነታችን ወሳኝ ነው!፡፡ የተለያዩ የካንሰር አይነቶች የአለማችንን ህዝቦች እያስጨነቁ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለካንሰር ምርምር ይውላል፡፡ ትልቁ ችግር ካንሰር ምን እንደሆነ ማወቁ ወይም ታማሚውን የጎዳው ህመም ካንሰር መሆኑን ማረጋገጡ አይደለም፡፡ በጊዜ (early) እንዲታወቅ የሚረዱ ምርመራዎች አሉ፡፡ ዘግይቶም ከተገኘ ሰውነትን እየቦረቦረ በጭካኔ ሲገሰግስ በግልፅ መታወቁ አይቀርም፡፡ ያልተመለሰው ትልቁ ጥያቄ ግን የካንሰር መንስዔው

ምንድነው? የሚለው ነው። ለዚህም የተለያዩ መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉ ምክንያቶች ይዘረዘራሉ። ምግብ ውስጥ የሚገቡ የተለያዩ ኬሚካሎች....... ቫይረሶች....... ጄኔቲክ ችግሮች...... በቤተሰብ አባላት ተመሳሳይ ችግር መኖር (Heredity) ና የመሳሰሉት በትኩረት ይጠናሉ። ከነዚህ በተለየ ግን አንዳንድ ሳይንቲስቶች ለካንሰር መነሻ ምክንየት 'ቂም ወይም 'ይቅር አለማለት' ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ። ይህንንም በተለያዩ ጥናቶች ለማረጋገጥ እየሞከሩ ነው። እኔ ደግሞ በዚህ በጣም እስማማለሁ!።

በምድር ስንኖር የሚበድሉን ሰዎች ይኖራሉ። ባልጠበቁት ሰአት የቅርቤ የሚሉት ሰው ከባድ ጉዳት አድርሶቦት ይሆናል። "አይ እርሱንስ ይቅር አልልም!" ይላሉ...... ቂም በልብዎ ያስቀምጣሉ! አውነት ነው ተበድለዋል!....... አዝነውማል። ይሁን እንጂ ይቅር ከማለት ሌላ አማራጭ የለም። እርሶ ተበድለው እንደገና በቂም ስለምን እርሶ ህመምተኛ ይሆናሉ። ባሰቡት ቁጥር እየተበሳጩ...... እየተብከነከኑ መኖር በእርሶ ላይ አደጋን ያመጣል። ካንሰር ብቻ ሳይሆን ይቅር ማለትኮ የአንጀት አልሰርን የመሳሰሉ ህመሞችን ሊያስከትል ይችላል። ስለዚህ አንድን ሰው ይቅር ስለው ለራሴም ሰላምና ጤንነት ብዬ ነው።

ይቅር ማለት ቀላል ሆኖ ግን አይደለም፤ በጣም ከባድ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ምንም ቢከብድ ግን ሌላ አማራጭ የለም፤ እግዚአብሔር ይቅርታን ይፈልገዋልና። "ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ይቅር ልበለው? ሰባት ጊዜ ነውን?" ብሎ ጠየቀ ጴጥሮስ ኢየሱስን። ጌታም "ሰባት ጊዜ ሰባ ነው እንጂ ሰባት ጊዜ አይደልም" አለው (ማቴ 18፤ 21-22)። አራት መቶ ዘጠና ጊዜ ማለቱ ሳይሆን...... ወሰን የለውም ለማለት ነው!። "ሁል ጊዜ ይቅር በለው" ሲለው ነው። እኛ ራሳችን ከእግዚአብሔር ይቅርታን የምናገኘው የበደለንን ወንድማችንን ይቅር ስንል ብቻ ነው።

በሎስአንጀለስ ካሊፎርንያ አንድ ትልቅ ቢል ቦርድ ላይ "ይቅር በል... ነገሩንም እርሳው" (Forgive and forget) ተብሎ ተፅፏል። ይህንን የሚለማመድ ሰው ትልቅ ሰው ነው። የፈሰሰለትንም የሀጢያት ይቅርታ በሚገባ ተረድቶታል። ይቅር ይበሉ.... ነገሩንም ይርሱ!።

## የጥበብ እንቁ 21

# በቀልን ለእግዚአብሔር መተው !

በጌታ በኢየሱስ ደግ እጆች ላይ ትልቅ ሚስማር የቸነከረውን ወታደር ማርያም አይታዋለች:: በእግሮቹም ላይ ያለ ርህራሄ ሚስማር የመታውን ሰው ልብ ብላዋለች:: በጦር ጎኑን የወጋውም ሰው ከአይታዋ አላመለጠም:: "ክርስቶስ ከሆንክ በል ከመስቀል ውረድና አሳየን" እያሉ የሚያላግጡትን ሰዎች ሰምታቸዋለች:: "ተው ኤልያስ መጥቶ ያድነው!" እያሉም ሲያሾፉበት አድምጣለች (ማር 15:29-35):: ሊቀካህናቱ ቆመው የልጇን መሰቀል በደስታ ሲከታተሉ አይታቸዋለች::

አቤት ከፋታቸው!.... "ኤሎሄ ኤሎሄ ላማሰበቅታኒ!" እያለ እርሱ ሲጮኸ እነርሱ ይሳለቁ ነበር:: ይህንን ሁሉ ማርያም ተመለከተች!፤ የተፃፈው ሁሉ ተፈፀመና አበቃ!፤ ጌታም ተፈፀመ ብሎ ነፍሱን ሰጠ!...... ሁሉም አለፈ!...... ጌታ ከሙታን ተነሳ! ........ ለብዙዎችም ራሱን ገለጠ...... ወደ ሰማይም አረገ!::

ከዚያ በኋላ ግንኮ እነዚያ ሰዎች ሁሉ በየስፍራ ነበሩ:: የገረፉት...... በሚስማር የወጉት...... ልብሱን የገፈፉት....... ያሾሚጠጡበት....... የቀለዱበት...... ሁሉም ነበሩ!:: ታዲያ ማርያም ዘመዶችዋን አሰባስባ ቢያንስ የተወሰኑትን መበቀል አልነበረባትም?፤ ከዘመዶቹስ "ደም መላሽ!" ማስነሳት አልነበረባትም? አላደረገችውም!:: ይልቁን በቀል የእግዚአብሔር እንደሆነ ታምን ነበርና ለእርሱ ተወችለት::

"በቀል የእኔ ነው" ብሏል ጌታ እግዚአብሔር:: "ለእኔ ተውልኝ" አለን (መዝ 94፡1):: ሰው ግን በቀልን ይወዳል.... በቀል ያረካዋል!፤ ካልተበቀለ እረፍት የለውም:: ይህ ግን ፈፅሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ አይደለም!፤ ሰዎችን ይቅር ካልን በኋላ የበቀል ስሜትን ማስተናገድ የለብንም:: ለጌታ ከተውንለት እርሱ በደለኛውን እንዴት እንደሚቀጣ ያውቅበታል:: ማርያም ሔሮድስን ልትበቀለው ባትሞክርም በእግዚአብሔር በቀል ግን ሰውዬው በትል ተበልቶ ሞቷል...... በመልአክ ተመቶ!::

እውነት ነው!፤ እኛ በምንፈልገው ፍጥነት እግዚአብሔር አይበቀልንን ይሆናል፡፡ ንጉሱ ዳዊት በልጁ በአቤሴሎም ምክንያት ተሰዶ ከከተማው ሲወጣ የጌራ ሰው ሳሚ የሚባል ሰው ትብያን እየበተነ በህዝቡ ሁሉ ፊት እጅግ አዋርዶታል፡፡ "አንተ የደም ሰው!" እያለም ብዙ ስድብ ሰድቦታል፡፡ ይህን የተመለከተ ከዳዊት የጦር ጄነራሎች አንዱ ነበረው አቢሳ "ይሄንን የሞተ ውሻ ....... ራሱን ልቁረጠው!" ሲል ዳዊት አልፈቀደም (2ኛ ሳሙ 16:7-9)፡፡ "ተወው እግዚአብሔር ስደበው ብሎት ይሆናል!" ነበር ያለው!፡፡ "እግዚአብሔር ፈቅዶለታል" ለማለት ነው፡፡

ቆይቶም....... ዳዊት በድል ሲመለስ ተሳዳቢውን የጌራ ሰው ሳሚን አገኘው፡፡ ሳሚ ደንግጧል!.... ሞት ሞት ሸቶታል!፡፡ ዳዊት ግን ሊበቀለው....... ሁለት ቦታ ሊሰነጥቀው አቅም እያለው ምንም ሳያደርገው ተወው!፡፡ ለምን? ንጉስ ዳዊት በቀል የእግዚአብሔር እንደሆነ ከልቡ ስለሚያምን ነው፡፡ እግዚአብሔርም ተሳዳቢውን ሰው በራሱ ጊዜ በራሱ መንገድ ተበቅሎታል..... በሰሎሞን ዘመን፡፡

በቀል እጅግ ከፉ፤ መዘዙ የማያልቅ ነገር ነው፡፡ በተለያዩ የምድራችን አካባቢዎች "ደም መላሽ" መሆን የተለመደ ነው፡፡ የህክምና ትምህርቴን እንደጨረስኩ አንድ የገጠር ከተማ ነበር ለስራ የተመደብኩት፡፡ ታዲያ ወደዚያው ላቀና ጥቂት ቀናት ሲቀረኝ አንድ ዘመዴ "አያትህ እኮ ድሮ ከዚያ አገር ወጥተው ነው ወደ ጂጂጋ የሔዱት፤....... ምናልባት የዛን የወጡ ጊዜ አወጣጣቸው መልካም ካልነበረ ሰዎች ዘርህን ቆጥረው እንዳይገድሉህ!" አለኝ፡፡ እኔም እጅግ ተገርሜ "እኔን? እንዴ! ምን አድርጌ?" አልኩት፡፡ "እንደዚያ ነው አሰራሩ!" አለኝ፡፡ ፍርሀት ፍርሀት አለኝ....... እዛ ከተማ ሔጄ አንድ ቀን አድሬ ተመለስኩ፡፡ ፈርቼ ግን አይደለም!!.... ለጥንቃቄ ነው!፡፡

በቀል ፈፅሞ ከመሀላችን መወገድ ያለበት ነገር ነው፡፡ ቁርሾ መያዝ...... ጥርስን ማንገጫገጭ..... ለመበቀል አጋጣሚን መጠበቅ ከእኛ ይራቅ!፡፡ በቀል የእግዚአብሔር ነው!፡፡ "እንደው አምላኬ! የእርሱን ነገር ታሳየኛለህ!" ብሎ የዚያን ሰው ውድቀት መጠባበቅም ተገቢ አይደለም፡፡ ይቅር ማለት...... ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት....... መርሳት..... ያ ሰውም በጊዜው ሲቀጣ "እሰይ!" አለማለት!.......... ይህ ነው ትክክለኛ አሰራሩ፡፡

# የጥበብ እንቁ 22

## ሰላምና እረፍትን መለማመድ !

ቅድስት ማርያም የመራችው ኑሮ ከባድና አስጨናቂ ኑሮ ነበር፡፡ ያለ ወንድ ፈቃድ መፀነስዋ የሚያመጣው ጭንቀት አለ፡፡ ከዚያም የሔሮድስ ዛቻ......... ስደቱ........ መከራው የተደራረበ ነበር፡፡ በልጇ አገልግሎት ምክንያት የሚነሱ ማዕበሎች....... ስድቡ....... መገፋቱ...... ቀላል አልነበረም፡፡ "ሰይፍ በነፍስሽ ያልፋል" እንደተባለች እንዲሁ ትልቅ ሰይፍ ነው በህይወቷ ያለፈው (ሉቃ 2፡34-35)፡፡ በዚህ ሁሉ ግን የማርያም ሰላም የተጠበቀ ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን አላማ ጠንቅቃ ስለተረዳች በጭንቀት ውስጥ አልከረመችም፡፡ በጭንቀት ታማ ስትተኛ....... ጌታም መጥቶ ሲፈውሳት በመፅሀፍ ቅዱስ አላየንም፡፡

'ሰላም'......... በሚያናውጥ አለም ውስጥ እየኖሩ ባለመናወጥ መኖር ነው፡፡ 'እረፍት' ም......... በሚያስጨንቅ አለም ውስጥ እየኖሩ ያለ ጭንቀት መኖር ነው፡፡ የጠቅላላ ሀኪም ሆኜ በሰራሁባቸው አመታት ሳስተውል ለህክምና ወደ ክሊኒክ ከሚመጡ ታካሚዎች ከፊሎቹ ምንም አይነት የውስጥ ደዌ ህመም የሌለባቸው ነበሩ፡፡ "ራሴን ያቃጥለኛል........ ልቤ ይመታል...... ቀኜን ይወጋኛል....." እያሉ የሚሰማቸውን ሲያስረዱ በሚገባ አዳምጣቸዋለሁ፡፡ የሚገባውንም ምርመራ ሁሉ አደርጋለሁ፡፡ ምንም አይነት የውስጥ ደዌ ችግር እንደሌለባቸው ካረጋገጥኩ በኋላ ግን በጨዋታ ስለ ኑሮአቸው፣ ስለ ትዳራቸው፣ ስለ ቤተሰባቸው፣ ስለ ስራቸው እጠይቃቸዋለሁ፡፡ የህመማቸውንም ምንጭ እዛ ውስጥ አገኘዋለሁ፡፡

በምድር ላይ የምናየው የኑሮ ጫናና (Stress) ጭንቀት የተለያየ በሽታን መስሎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ፍርሀት ፍርሀት ማለት፣ የልብ መምታት፣ ማላብ፣ ራስን ማቃጠል፣ እንቅልፍ ማጣት...... እነዚህ 'አንዛይቲ ነውሮሲስ' (Anxiety Neurosis) የተባለውን የጭንቀት አይነት ያመለክታሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ የሆነ በሽታ አለብኝ ብለው ድርቅ ይላሉ፡፡ ለምሳሌ "እኔ ጉበቴን

ያመኛል! የጉበት በሽታ እንዳለብኝ እርግጠኛ ነኝ!" ይላሉ:: ምርመራ ሁሉ ተደርጎ የጉበት በሽታ እንደሌለባቸው ሲነገራቸው ይበሳጫሉ!፤ "እኔ እንዳለብኝ እርግጠኛ ነኝ!" ይላሉ:: ከአንዱ ክሊኒክ ወደ ሌላው ክሊኒክም ይዞራሉ:: ይህ ደግሞ 'ሀይፖኮንድርያሲስ' (Hypochondriasis) ይባላል:: ብዙ ጊዜ ይህ የሚሆነው ሌላ ሰው በጉበት በሽታ ታሞ ካዩ ወይም "እከሌ በጉበት በሽታ ታሞ ሞተ" ተብሎ ሲነገራቸው ነው:: ሌሎች ደግሞ ምንም የውስጥ ደዌ ሳይኖርባቸው በድንገት "እጄ እምቢ አለኝ፣ እግሬ እምቢ አለኝ" የሚሉ ናቸው:: በዊልቼር ሁሉ ሊመጡ ይችላሉ!፤ ይህ ደግሞ 'ሂስቴሪካል ኮንቨርሽን' (Hysterical Conversion) ይባላል ። እነዚህ ሁሉ እንግዲህ በኑሮ ውስጥ ባለ ጫናና ጭንቀት የሚመጡ ችግሮች ናቸው::

ሰው በተቻለ መጠን ጭንቀት የሌለበት የእረፍት ኑሮን መኖር አለበት:: የሚያስጨንቅ ነገር አይኖርም ማለት አይደለም!፤ ይኖራል!:: ነገር ግን እንደ ቅድስት ማርያም በጭንቀት ውስጥ አለመጨነቅ ይቻላል:: እንዲህ ማድረግ የሚቻለው ግን በእግዚአብሔር ላይ በማረፍ ብቻ ነው:: "እረፉ! እኔም አምላክ እንደሆንኩ እወቁ!" ብሎናል እርሱ(መዝ(46):10):: የሚያስጨንቀንን ሁሉ ለእርሱ በፀሎት በመንገርና በእርሱ ላይ በመጣል እረፍት ይመጣል!:: "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት" ተብለናል (1ኛ ጴጥ 5:7):: አንድ ጊዜ በጣም ተጨንቄ በእግሬ ስሔድ አንድ በመንገድ ሁሌ የማየው እብድ ወደ እኔ ቀርቦ "አንተ ከእግዚአብሔር ትበልጣለህ?" አለኝ:: እኔም ደንግጬ "ኧረ አልበልጥም!" አልኩት:: "ታዲያ ምን ወሬ ታበዛለህ!" አለኝና ጥሎኝ ሔደ:: ለእኔ መልክተኛዬ አድርጌ ወሰድኩት..... "እግዚአብሔር ከአንተ ይበልጣልና ለእርሱ ተውለት...... አጉል ስለ ራስህ አውቃለሁ አትበል!"..... ብዬ ተረጎምኩት.... ንግግሩን::

በጤንነት ተባርከው ረጅምና ደስ የሚያሰኝ ኑሮን ለመኖር ከወደዱ በእግዚአብሔር ላይ ማረፍን ይለማመዱ:: ይሆኑብኛል ብለው የሚፈሯቸው..... የሚሰጉባቸው..... እንቅልፍ የሚያጡባቸው ነገሮች አይሆኑቦትም...... ከእግዚአብሔር ጋ ከኖሩ!:: "የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል፣ ከመከራም ስጋት ያርፋል" ብሎታል እግዚአብሔር (ምሳሌ 1:33)::

# የጥበብ እንቁ 23

## የደስታን ምንጭ ንፁህ ማድረግ !

"ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች! መንፈሴም በአምላኬ በመድሀኒቴ ሐሴት ታደርጋለች" አለች ቅድስት ማርያም (ሉቃ 1፡47)፡፡ ሐሴት የደስታ ከፍተኛ ደረጃው ነው፡፡ ምንም ሰይፍ በህይወቷ ቢያልፍም....... ብዙ መከራን ብትቀበልም...... ሁሉም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ስለምታውቅ ማርያም ደስተኛ ነበረች፡፡ በአምላኳ..... በመድህኒቷ ሀሴት ታደርጋለች!፡፡

ደስታ (Joy) የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው፡፡ በምድር ላይ ስንኖር ደስተኞች ልንሆን ይገባል፡፡ ይህንን አጭር የምድር ኑሮ በሀዘን ተቆራፍደን ካሳለፍነው ኪሳራ ነው፡፡ በተሰጠን ዘመን ልንደስትበት (Enjoy ልናደርገው) ይገባል፡፡ ድብርት ከፉ ነገር ነው!፤ አእምሮን ያላሽቃል!፤ እየከፋም ከሔደ ክሊኒካል ዲፕሬሽን (Clinical Depression) ይሆናል፡፡ ያ ደግሞ ያሰቃያል....... እንቅልፍ ይነሳል...... "ከመኖር አለመኖር ይሻለኛል" ወደ ማለት ያመጣል፡፡ ከዚህ በኃላ ነው ሰዎች እራሳቸውን የማጥፋት (Suicide) ሙከራን የሚያደርጉት፡፡

ስለዚህም ደስ ሊለን እንደሚገባ ጥያቄ የለውም!፤ ችግሩ ግን "በምን ደስ ይበለን?" የሚለውን መመለስ ነው፡፡ ከላይ እንዳየነው ማርያም ሐሴት ያደረገችው በአምላኳ በእግዚአብሔር ነው፡፡ የእኔና የእርሶስ የደስታ ምንጭ ምን ይሆን?፡፡

ብዙ ሰዎች አልኮል መጠጣትን የደስታ ምንጭ አድርገው ይወስዱታል፡፡ የአልኮል መጠጥ ሲጠጡት ደስታን እንደሚሰጥ ጥያቄ የለውም፡፡ እኔም እጠጣ ነበርና አውቀዋለሁ፤ ሞቅ ሲል ደስ ይላል...... ጨዋታው ይደራል ...... ሳቁ ይደምቃል...... ሰውነት ዘና ይላል!፤ ግን ይቆይና ስካር ይመጣል፡፡ አእምሮ በአልኮሉ ቁጥጥር ስር ሲውል

የጠጣው ሰው የሚያደርገውን አያውቅም:: በማግስቱ የሚሸማቀቅበትን ነገር ይናገራል....... ጠዋት የሚፀፀትበትን ነገር ሌሊት ያደርጋል..... ስሟን እንኳን ከማያውቃት ሴት ጋ ያድራል፡፡ ደግሞም በህግ የሚያስጠይቀውን ወንጀል ሊሰራ ይችላል፡፡ የተፈጠረውን ነገር የሚያውቀው ጠዋት ሲነሳ ነው...... ራሱን ማረምያ ቤት ያገኘዋል!፤ በመኪና ሰው ገጭቶ ይሆናል...... ወይም ሰው ፈንክቷል!::

አልኮል የገንዘብም ጠር ነው!፤ ያለ ፕሮግራም ያለንን ያራግፋል፡፡ ደግሞ ጠዋት ያለው ሀንግ ኦቨርስ? አቤት ሀንግ ኦቨር!፤ እንዴት ያሰቃየኝ ነበር እኔን!፤ መከራዬን ነበር የማየው........ መድሀኒትነቱ ባይገባኝም የሽሮ ፍትፍት እበላበት ነበር፡፡ ጓደኞቼ ደግሞ "ትንሽ ጠጣበት!...... ይለቅሀል!" ይሉኝ ነበር፡፡ ይሄው አሁን የአልኮል መጠጥ ከጠጣሁ አስራ ስምንት አመት ሆኖኛል፤ አልፎ አልፎ ብቻ ኬክ ውስጥ ተቀላቅላ ትመጣለች.... አልኮል!::

ግን ማርያም በውስኪ ነው እንዴ ሐሴት ያደረገችው?፤ "ኧረ ምን በወጣት!" ይሉ ይሆናል :: ታዲያ እርሶስ ምን በወጣዎ? ደስታ እኮ ያለ መጠጥ ይገኛል!:: ሻይ እየጠጡ ከቦተሰብዎ..... ወይም ከጓደኞችዎ ጋ መሳቅ መጫወት ይችላሉ፤ ንፁህ በሆነው በእግዚአብሔር መንፈስ ሐሴት ያደርጋሉ!፤ እኔ ይሄው በየቀኑ ደስተኛ ነኝ...... ያለ መጠጥና ዳንኪራ!::

ሌሎች ያገሬ ልጆች ደግሞ የደስታቸውን ምንጭ ጫት ያደርጋሉ፡፡ በየመቃሚያው ቤት..... በየ ሱቁ..... ዛፍ ጥላ ስር በቆሙ መኪናዎች ውስጥ ይቅማሉ!:: እውነት ለመናገር ዛሬ ዛሬ በጣም ያሳስበኛል፡፡ የመንግስት ሰራተኛ ለምሳ ወጥቶ ጫት ቅሞ ይገባል!፤ ሹፌሩ መርቅና ይነዳል..... ሐኪሙም መርቅና የቀዶ ጥገና ይሰራል......!፤ ትንሹ........ ትልቁ....... ወንዱ....... ሴቱ......... ይቅማል!፤ ደግሞ ያጨሳል!..... ሲጋራውንም...... ጋያውንም..... ማሪዋናውንም ያጨሳል፡፡ አንዳንዴ "ትውልዱ ሁሉ መርቅኗል ማለት ነው?" እያልኩ አገረማለሁ፡፡

እኔም ድሮ እቅም ነበር፡፡ ለጥናትም ለመዝናናትም ብዬ!:: በተለይ ደግሞ ተማሪዎች ሆነን ተጫውቶብናል......ጫት!:: አንድ ጊዜ

የህክምና ፋኩልቲ ዲን የነበሩት ፕሮፌሰር በአደማርያም የተማሪዎችን የመኖርያ ዶርሚተሪ ለመጎብኘት በድንገት መጡ:: ፕሮፌሰሩ አይናቸውን ማመን አልቻሉም!፤...... ሁሉም ዶርም ይቃማል!..... ቆሻሻ ማጠራቀሚያዎቹ ሁሉ ገራባ ተሞልተዋል!:: በማግስቱ ስብሰባ ጠርተውን "እንዴት ጫት ትበላላችሁ?" አሉን:: በመገረም ሆነው መልስ ሲጠባበቁ "አቦ! ጫት ይቃማል እንጂ አይበላም!"....... አሉአቸው ጀዝባዎቹ!::

የጫት ደስታው ጊዜያዊ ነው:: ጫት ውስጥ ያለው አነቃቂ ቅመም 'ካቲኖን' (Cathinone) ይባላል:: ለጊዜው ያነቃቃል!፤ ስቲሙላንት (Stimulant) ነው:: ኬሚካል ፎርሙላው 'አምፊታሚን' (Amphitamin) ከሚባለው አነቃቂ ቅመም ጋ በጣም ይመሳሰላል:: ለጥቂት ሰአታት አእምሮን በጣም ያነቃል!፤ ቃሚው ይመረቅናል!፤ በዚህ ሰአት ቃሚው በሚርቃና ፎቅ ይሰራል......! ቤንዚን ከአከስቱ ቤት ጓሮ ያወጣል.......! ከቢል ጌትስ ጋ ሻይ ይጠጣል......! ከባራክ አባማ ጋ ስብሰባ ይቀመጣል.....! ከአላሙዲህ ጋ ቢዝነስ ይወያያል.....! በህሳቡ!:: በኋላ ግን የ ካቲኖኑ የማነቃቃት ስራ ሲያበቃ አንጎል መጀመርያውኑ ከነበረበት ንቃት በታች በጣም ይወርዳል:: ከዚህ በተጨማሪ ሰፋ ሰፋ ባሉት ቅጠሎች ውስጥ የሚገኘው ቅመም ልብን ያስጨንቃል..... ያልባል..... አይንን ያስፈጥጣል (Pupilary Dilation) !::

ጫት ወንድ ልጅን ይጎዳል:: የግብረ ስጋ ግኑኝነት የማድረግ ፍላጎትን (Libido) በጣም ይጨምርና የግብረ ስጋ ግኑኝነት የማድረግ አቅምን ግን ይገድላል:: ኢምፖተንት (Impotent) ያደርጋል:: ይህ የተጠና ነገር ነው...... ተንኮሉም አስገራሚ ነው:: ግን ደፈርከኝ አይበሉኝና ጫቱ ቢቀርስ?፤ ያለ እርሱ መደሰት እኮ ይቻላል!....... ሚርቃና የሌለበት ደስታ!:: ይሄው እኔ አስራ ስምንት አመት ሊሆነኝ ነው ጫት ካቆምኩኝ፤ አምላኬ ገላገላኝ!:: ይሄን መፀሀፍ የሚያነቡት እየቃሙ ከሆነ "አቦ! ይሄ ሰውዬ ለምን አይተወንም!" ብለው ይሆናል፤ አልቀየሞትም!::

የሌላው ወገኔ ደግሞ ይብሳል:: ይቅም ይጠጣና ወደ ሴተኛ አዳሪ ይሔዳል:: ገንዘቡን ከፍሎ ይተኛል!:: ያቺ ሴተኛ አዳሪ ግን

እመንገድ የቆመችው እርሷት ሊሆን ይችላል፡፡ “እመጣለሁ ተኙ” ብላ አባብላ ያስተኛቻቸው ሁለት ሶስት ልጆች ይኖርዋታል፡፡ ቸግሯት እንጂ ወንድ ፈልጋ አልወጣችም፡፡ ታዲያ በተቸገረች ሐበሻ ወገን ላይ የሚገኝ ደስታ ምን ደስታ ይባላል?፤ ይልቁን ሰውነቷን ሳይገዙ..... እርሷን ረድቶ..... ከተቻለም አቋቁሞ የመንፈስ እርካታን ማግኘት ይቻላል፤ ያም ንፁህ ደስታን ያመጣል!፡፡

በህዝባችን መሀል ያሉ የብዙ ወገኖቼ የሞራል ጉዳይ እያሳሰበኝ መጥቷል፡፡ የአዲስ አበባ የህፃናትና የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ከወራት በፊት ያወጣውን መግለጫ አምብቤ ደነገጥኩ፡፡ በመግለጫው መሰረት አዲስ አበባ ውስጥ ወደ 3600 የሚጠጉ ህገወጥ የወሲብ ንግድ የሚካሔድባቸው ቤቶች አሉ፤ ራቁት የሚደነስባቸው ቤቶች በዝተዋል!፤ ብዙ የማሳጅ ቤቶች ዝሙት ይሰራባቸዋል!፤ ሺሻ ማጨሻ ቤቶች ተበራክተዋል!፤ ግብረ ሰዶም በከተማው እየተስፋፋ ነው!፡፡

ታዲያ ማርያምን እወዳለሁ የሚል ህዝብ መሀል ይህ ሁሉ ክፉ ነገር እንዴት በዛ?፤ መንፈሳዊ አስተማሪዎችስ ለምን ዝም ይላሉ?፤ የሀይማኖት መሪዎች በያሉበት ህዝባቸውን ማስተማር ያለባቸው ይመስለኛል፡፡ መንግስት መቼም “አታመንዝሩ!” እያለ እንዲያስተምር አንጠብቅበትም፡፡ የሀገሬ ልጅ ሐበሻ ሆይ! የደስታችን ምንጭ ንፁህ ይሁን፡፡ ነፍሳችን...... በአምላካችን....... በመድሀኒታችን ሀሴት ታድርግ!.... ልክ እንደ ቅድስት ማርያም፡፡

# የጥበብ እንቁ 24

## ድንግልናን መጠበቅ !

የሴት ልጆች ወግ መዳር..... ማግባት...... ድንግልናን ለባል መስጠት ነው:: የቅድስት ማርያም ግን እንደዚያ አልነበረም:: ኢየሱስን ለመፀነስ ድንግልናዋን ማጣት አልነበረባትም:: ከመንፈስ ቅዱስ..... ያለ ወንድ ፈቃድ ፀንሳለችና ድንግልናዋ የተጠበቀ ነበር::

ድንግልና ከእግዚአብሔር የሚሰጥ የንፅህና ማህተም ነው:: ሴቶች እህቶቻችን ድንግል ሆነው ነው የሚወለዱት:: በእህቶቻችን ላይ ያለው የድንግልና ማህተም በደም ስሮች የተሞላ ነው፤ ሀይመን (Hymen) ይባላል!:: ቢቻል መቼም እስከ ጋብቻ ድረስ ድንግልናን መጠበቅ መልካም ነው:: "እህቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ፣ የታተመ ፈሳሽ ናት" እንደሚል ቃሉ እግዚአብሔር ላዘጋጅልሽ ሰው የታተመ ምንጭ...... የተቆለፈ ገነት ሆኖ መቆየት ድንቅ ነው (መሀልዩ 4፡12)::

ከጋብቻ በፊት የግብረ ስጋ ግኑኝነት ማድረግ እግዚአብሔር የደነገገው አይደለም:: ሁሉ መሆን ያለበት በጋብቻ ውስጥ ነው:: ወጣቶች በድንግልናቸው መኩራት እንጂ ማፈር የለባቸውም:: 'ስልጣኔ' እየተባለ የ 23 ና የ24 አመት ወጣቶች በድንግልናቸው እንዲያፍሩ ማድረግ የሰይጣን ተንኮል ነው::

ምናልባት ግን በጠላት የተያዘ አለም ውስጥ ነውና የምንኖረው....... ልክ መስሎሽ...... ከጋብቻ ውጪ ድንግልናሽን አጥተሽ ቢሆን አትጨነቂ፤ ያጣሽው ያቺን ማህተሟን ነው:: በቀሪው ዘመንሽ...... እስከታገቢ ድረስ........ ራስሽን ጠብቀሽ ለመኖር ከወደድሽ እርሱም ድንግልና ነው:: ሰውነትሽን የእኔ ብለሽ ላላገባሽው ሰው ላለመስጠት መወሰን ነው!::

ለአንተም ወንድሜ ሆይ እንዲሁ ነው፡፡ አንዳንድ ወንዶች ከዚችም ከዚያችም ጋ መተኛት ጀብድ ይመስላቸዋል፡፡ እውነተኛው ጀብድ ግን የአንተ የሆነችዋ ሴት እስከትመጣና እስከታገባት ድረስ ራስህን መጠበቅ ነው፡፡ አንድ ከብዙ ሴቶች ጋ የተኛ የውጭ ሀገር ስፖርተኛ ሲናገር "መላ አካላቴ በየከተማው ተበጣጥሶ የቀረ ይመስለኛል" ብሎ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት በዚህ ጉዳይ ብዙ አጥፍተህ ቢሆን ንስህ በመግባት ቀሪውን ጊዜህን ማስተካከል ትችላለህ፡፡ትዳር ክቡር ነው!፤ መኝታውም ንፁህ ነው!፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ሳያገቡ እንዲኖሩ የሚጠሩ ይኖራሉ፡፡ ይህንንም መቀበል ይኖርብናል፡፡ "ኧረ ማግባት አለብሽ!" እያልን ነፍሳቸውን ማስጨነቅ የለብንም፡፡ እግዚአብሔር ትዳር ከሰጣቸው መልካም ነው!፤ ካልተሰጣቸው ደግሞ የግድ እንዲያገቡ መወትወት የለብንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሴቶች የዘመዶቻቸውን ንትርክ በመጥላት ብቻ ያገኙትን ወንድ የሚያገቡ አሉ፡፡ አንቺ ግን እንደርሱ አታድርጊ፤ ሳታገቢ 50 አመት 60ም አመት ሞልቶሻል? እህቴ ሆይ ምንም አልቀረብሽም!፤ ያ አንቺ የኖርሽው ህይወትም ራሱ ልዩ በረከት አለው፡፡ያላገባሽው ግን የማትፈለጊ ስለሆንሽ አይደለም!፤ ለጊዜውም ሆነ ለዘለቄታው እግዚአብሔር አምላክሽ እንዲህ እንዲሆን ስለወደደ ነው፡፡

ድንግልና የስጋ ድንግልናም ብቻ አይደለም፡፡የልብ ድንግልናም አለ!፡፡ የልብ ድንግልና ራስን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው!፤ ክፉ ሀሳብ ወደ ልባችን ሊገባ ሲሞክር እምቢ ማለት ነው!፤ ተንኮል ወደ ልባችን ሲመጣ "ልቤ ድንግል ነው! ላስገባህ አልችልም!" ብሎ መመለስ ነው፡፡ እንግዳ የሆኑ አስተሳሰቦችን አለማስተናገድም ነው፡፡ የከበረውን ከተዋረደው ለይቶ ማወቅ........!፡፡

## የጥበብ እንቁ 25

# ለውስጥ ውበት ዋጋ መስጠት !

ስለ ቅድስት ማርያም ውበትና ቁንጅና የተፃፈ ነገር አላየሁም፡፡ ነገር ግን እንዲሁ ውብ እንደነበረች አስባለሁ፡፡ በብዙዎች ዘንድ ያለውም ግምት ይህ ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ነው ሰዎች በጣም ጨዋና የተዋበች ሴት ሲያዩ "እምዬ ማርያምን ትመስላለች!" የሚሉት፡፡ ስለ ውበቷ ያልተፃፈልን ምክንያት ምናልባት በውጭ የሚታይ ውበት በእግዚአብሔር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ስላልሆነ ይሆናል፡፡ ማርያምም ያተኮረችው ውስጣዊ ውበትዋ ላይ ነበር!፡፡

መቼም በአለም ዙሪያ ስለ ቁንጅናና ውበት የሚሰጠው ከመጠን ያለፈ ቦታ የሚያስገርም ነው፡፡ እንደ አንዳንድ ጥናቶች በአሜሪካን ሀገር ለመዋቢያ ኮስሜቲኮች (cosmetics) የሚወጣው ገንዘብ በአመት 10 ቢሊዮን ዶላር ነው፡፡ እነ ሊፕስቲክና የጥፍር ቀለም ናቸው ያን ያህል ሀብት የሚፈስባቸው፡፡ ይህ ለኮስሜቲክስ ብቻ አሜሪካኖቹ የሚያወጡት ዶላር ከአንዳንድ የአፍሪካ አገሮች አመታዊ በጀት ይበልጣል፡፡

ከዚህም ሲብስ ሰዎች ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ውበት ስለማይተማመኑ በቀዶ ጥገና የተለያዩ የሰውነት ክፍላቸውን ቅርፅ ያስለውጣሉ፡፡ አፍንጫቸው ካላማራቸው እነርሱ በፈለጉት ስታይል ያስለውጡታል!፤ 'ሪኖፕላስቲ' (Rhinoplasty) ይባላል፡፡ ፊታቸው ላይ የእድሜ ምልክት የሆኑ መስመሮች (Wrinkles) ወጥተው ካሳሰቧቸው በጣም ውድ ዋጋ ከፍለው ፊታቸውን ያስወጥሩታል!፤ ይሄ ደግሞ 'ፌስሊፍት' (Facelift) ይባላል:: ሴቶቹ ጡቶቻቸው የወንድን እይታ የሚስቡ፣ ቀሚሳቸውን የሚጋፉ እንዲሆኑላቸው ሲፈልጉ በቀዶ ጥገና ጡቶቻቸው ውስጥ 'ኢምፕላንት' (Implant) ያስገባሉ፤ ይህ ደግሞ 'ማስቶፕላስቲ' (Mastoplasty) ይባላል፡፡ ለእንደነዚህ አይነቶቹ በውበት ላይ ላተኮሩ ቀዶ ጥገናዎች ደግሞ አሜሪካኖች ሌላ 10 ቢሊዮን ዶላር ያወጣሉ፡፡

ወንዶቹም ሴቶቹም በሰውነታቸው የተለያየ ክፍል ደስ የማያሰኛቸው ውፍረት.... የተጠራቀመ ስብ ካለ እርሱንም ያስወጡታል....... ያስመጥጡታል!፣ ይህም 'ላይፖሳክሽን' (Liposuction) ይባላል፡፡ በእግርና በፊት ላይ ያለ ፀጉርን በ 'ሌዘር ሰርጀሪ' (Laser Surgery) ማስነሳትም አለ፡፡ ለእንደነዚህ አይነት የቀዶ ጥገና ህክምናዎች ደግሞ አሜሪካኖች ባጠቃላይ በአመት እስከ 4 ቢሊዮን ዶላር ያወጣሉ፤ ይህ ደግሞ በጣም ብዙ ህፃናትን ማስተማር የሚችል ገንዘብ ነው፡፡

ለውበት ተብለው የሚገዙ ልብሶችም በጣም ውድ ናቸው፡፡ በውጪው አለም ሴቶች ሌት ተቀን ለፍተው ያገኙትን ገንዘብ የሚወስድባቸው የልብስ ግብይት (Shopping) ነው፡፡ ይገዛሉ..... ከገዙት በኋላ ይጠሉታል........ ደግሞ ሌላ ይገዛሉ...... ይቀጥላል!፡፡

ይህ ሁሉ የሚደረገው እንግዲህ የበለጠ ውብ ሆኖ ለመታየት ነው፡፡ ታላቁ የስነ-መለኮት ምሁር ጆናታን ኤድዋርስ (Jonathan Edwards) ወበትን ሲገልጠው..... "ውበት ህብር (Harmony) ነው!" ብሎ ነበር፡፡ በሳይኮሎጂስቶቹ አገላለፅ ደግሞ ውበት "ደስ የሚያሰኝ ስሜትን የሚፈጥር፣ ትርጉም ያለው፣ እርካታን የሚሰጥ እይታ (Perception) ነው" ይላሉ፡፡

በትክክለኛው መንገድ ሰዎች ራሳቸውን ለማስዋብ መሞከራቸው መልካም ነው እላለሁ፡፡ በጣም ሲበዛ ግን ችግር አለው፡፡ ቀኑን ሙሉም ስለ ጥፍር ቀለምና ስለ ሊፕስቲክ ብቻ እያሰቡ መዋል ተገቢ አይደለም፡፡በጥሩ ሁኔታ ራስን በንፅህና መጠበቅ ተገቢ ነው፡፡ ከዚያ በተረፈ ግን መተኮር ያለበት የውስጥ ውበት ላይ ነው፡፡

የውስጥ ውበት በመንፈስ ቅዱስ ጌጦች መከሸን ነው፡፡ ትህትናን መላበስ፣ የዋህነትና ገርነትን መደረብ፣ እውነትን መታጠቅ፣ የፍቅር ሽቶን መቀባት፣ በትዕግስት ደርባባ ሆኖ መመላለስ ነው፡፡ በጥበብ መዋብ ደስ ይላል!፤ በማስተዋል መቆንጀት መልካም ነው!፤ ጭምትነትም ውበት ነው፡፡ አቤት ሴቶች ራሳቸውን የሚገዙ ቁጥቦች ሲሆኑ ሲያምርባቸው!፡፡ እንግዲህ ይህ ከሆነ እውነቱ ውስጣችንን እናስውበው!፤ ያም ውበት በራሱ ወደ ውጪም ደምቆ ይታያል..... ያስከብረናል!፡፡

# የጥበብ እንቁ 26

## በማመንና በመተማመን መኋደድ !

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ቅድስት ማርያም ከመላኩ በፊት ወደ ካህኑ ዘካርያስ ተልኮ ነበር..... መጥምቁ ዮሀንስ እንደሚፀነስ ለማብሰር!፡፡ ካህኑ ዘካርያስ ግን ዕድሜው ስለገፋ ባለቤቱም ኤልሳቤጥ ስላረጀች የመጣለትን መልዕክት መቀበል አልቻለም....... አላመነም!፡፡ እግዚአብሔር ይህን ማድረግ እንደሚችል ግን ከአብርሀምና ከሳራ ታሪክ መማር ይችል ነበር፡፡ ይሆናል ተብሎ የተነገረው ነገር ከእርሱ በፊት የሆን ነውና፡፡ ዘካርያስ ግን ባለማመኑ ጠንቅ ዮሐንስ እስኪወለድ ድረስ ዲዳ ሆነ (ሉቃ 1፡22)፡፡ አለማመን እግዚአብሔርን ያስቆጣዋልና!፡፡

በአንፃሩ ግን መልአኩ ገብርኤል ወደ ማርያም መጥቶ ያለ ወንድ ፈቃድ........ ከመንፈስ ቅዱስ እንደምትፀንስ ሲነግራት አመነች!፡፡ ከእርሷ በፊት ግን በታሪክ ከመንፈስ ቅዱስ የፀነሰች ማንም ሴት አልነበረችም፡፡ ይህ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ እምነት ነው....... እግዚአብሔር ደስ የተሰኘበት እምነት!፡፡ ማርያም በማመን ብቻ አላቆመችም....... ለሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ተማመነችበት እንጂ!፡፡

ጌታ ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ ሁለት ጊዜ ተደንቋል፡፡ በአንዱ ጊዜ አንድ የመቶ አለቃ ብላቴናው ታሞበት እንዲፈውስለት ጠይቆት..... አስጠይቆትም ነበር፡፡ ኢየሱስም ተስማምቶ ብላቴናውን ለመፈወስ መንገድ ሲጀምር የመቶ አለቃው መልዕክተኛ ልኮ "ጌታ ሆይ! በቤቴ ጣርያ ስር ልትገባ አይገባኝምና አትድከም፤ስለዚህም ወደ አንተ ልመጣ እንዲገባኝ ሰውነቴን አልቆጠርሁትም፤ነገር ግን ቃል ተናገር፤ ብላቴናዬም ፈወሳል" አለው(ሉቃ 6፡4-10)፡፡ በዚህም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ተገረመ.......ተደነቀ !፡፡ በሌላው ጊዜ ደግሞ

ባደገበት ስፍራ..... በገዛ አገሩ የነበረውን አስገራሚ አለማመን አይቶ ተደንቋል!(ማር 6፡6)፡፡

እግዚአብሔር እንድናምን የሚጠብቅብን በቃሉም በመንፈሱም 'አደርገዋለሁ' ብሎ የነገረንን ነገር ነው፡፡ እኔ ሁለት ህፃናት ልጆች አሉኝ....... "አሜን" ና "ግሬስ" የሚባሉ፡፡ ለልጆቼ "ቅዳሜ መጫወቻ ስፍራ እወስዳችኋለሁ" ብዬ እነግራቸዋለሁ፡፡ ቅዳሜ ሲመጣ ታዲያ ምን ቢደክመኝ.......ምን ጉዳይ ቢኖረኝ......ለልጆቼ የገባሁላቸውን ቃል እፈፅማለሁ........መጫወቻ ስፍራ እወስዳቸዋለሁ!፡፡ እኔ ሰው የሆንኩት ለልጆቼ የገባሁትን ቃል የምጠብቅ ከሆነ...... ታላቁ አምላክ..... የሰማዩ አባትማ ይልቁን እንዴት ቃሉን አይጠብቅ!፡፡

"የተናገረውን ያደርግ ይሆን ?" ብሎ እርሱን መጠራጠር እርሱን እንደ መናቅ ይቆጠራል፡፡ እርሱም "ይህ ህዝብ እስከመቼ ይንቀኛል!...... በተናገርኩትም እስከ መቼ አያምንብኝም!" ብሎ ያውቃል..... ህዝቡ እስራኤል ባለማመን አስቸግረውት(ዘሁ 14፡11)፡፡ ያለ እምነትም እግዚአብሔርን ደስ ማሰደሰት አይቻልም!፡፡

አገልግሎት ከመጀመሬ በፊት ገና በመንፈሳዊ ህይወቴ በደንብ ሳላድግ አንድ ህልም አየሁ፡፡ አንድ ትልቅ ቤተ-ክርስትያን መድረክ ላይ ቆሜ እጄን እያወናጨፍኩ እሰብካለሁ:: ከእንቅልፌ ስነሳ በራሴ ሳቅሁኝ!፤ እኔ ሰባኪ የመሆን ሀሳቡም አልነበረኝም፡፡ ታዲያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሳላውቀው አገልግሎት ውስጥ ገባሁኝ፡፡ ያንን ህልም ባየሁኝ በሁለት አመቱ በህልሜ ያየሁት ቤተ-ክርስትያን ተጋብዤ መድረኩ ላይ ቆምኩኝ፡፡ እዛው መድረክ ላይ ሆኜ ነበር ህልሙን ያስታወስኩት፡፡ በጣም የገረመኝ ነገር ታዲያ በህልሜ ስሰብክ ለብሼው የነበረው ሱፍና የዚያን ቀን ሳገለግል የለበስኩት ሱፍ አንድ መሆኑ ነው...... እስከ ክራቫቱ፡፡

እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ልክ እንደተናገረው ነው የሚያደርገው....... "እንደ ተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምነዋለሁ!" እንዳለ ጳውሎስ (ሐዋ ስራ 27፡25)፡፡ ለእርሶም የነገሮትን ሁሉ እስኪያደርግሎት ድረስ እግዚአብሔር አይተዎትም!፡፡

በከተማችን ውስጥ በብዛት በስራ ላይ ከዋሉ አባባሎች አንዱ "አስተማማኝ ነው!" የሚለው ነው:: ነገር ግን አስተማማኝ የተባለው ሁሉ አስተማማኝ አይደለም:: አስተማማኝ የተባለው መኪና በሶስት ወሩ ይገለበጣል..... በቴክኒክ ችግር:: እውነተኛ አስተማማኝ..... የማያሳፍር...... ሁሌ በቦታው የሚገኝ እርሱ እግዚአብሔር ነው::

ይህ ድንቅ አምላክ እንድናምነው ብቻ ሳይሆን ደግሞ እንድንተማመንበትም ይፈልጋል:: "አምላኬ የት ሔዶ! አባቴ እያለ ምን ችግር አለ!" እያልን ስንኳደድበት ደስ ይለዋል:: "በቅዱስ ስሙ ተኳደዱ...... እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው" ይላል ቃሉ!፤ እናምነዋለን..... እንተማመንበታለን..... በስሙም እንኳደዳለን! (መዝ(105):3)::

# የጥበብ እንቁ 27

## ቃሉን አውቆ ማድረግ !

የቅድስት ማርያም የመንፃቷ ወራት ከተፈፀመ በኋላ ልጇን ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም........ ወደ ቤተ-መቅደሱ ወስዳዋለች፡፡ እዚያም "የእናቱን ማህፀን የሚከፍት ወንድ ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይባላል" በሚለው በሙሴ ህግ መሰረት በእግዚአብሔር ፊት አቅርባዋለች፡፡ የሚቀርበውንም መስዋት ሁሉ........ ሁለት የእርግብ ጫጩት........ በማቅረብ የሚገባውን ስርአት ሁሉም ፈፅማለች (ሉቃ 2፡22-23)፡፡ ይህንን ያደረገችበት ምክንያትም በጊዜው የምትከተለው የአይሁድ ሀይማኖት ቃል ስለምታከብር ነበር፡፡ የእምነቷ መሰረት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ታውቀውም ትጠብቀውም ነበር፡፡

ብዙዎቻችን በቤታችን መፀሀፍ ቅዱስ አለን፡፡ በጣም እናከብረዋለን!፤ እንጠነቀቅለታለን፡፡ በአንዳንዶች ቤት መፀሀፍ ቅዱስ ትራስ ስር የሚቀመጥ ቅዣት መከላከያ ነው፡፡ በሌሎች ዘንድ ደግሞ አልፎ አልፎ እየተነሳ የሚሳም ግን የማይከፈት ቅዱስ እቃ ነው፡፡ ትንሽ በተማሩት በአንዳንዶቹ ዘንድም ከሌሎች መፃህፍት ጋ በመደርደርያው ላይ የሚቀመጥ 'ከመፃህፍቶች አንዱ' ነው፡፡ በብዙ ሰዎች አስተሳሰብ መፀሀፍ ቅዱስ የቄሶች....... የፓስተሮች...... የሰባኪዎች መፀሀፍ ነው፡፡ ቄሶቹ ወይም ፓስተሮቹ ሲያነቡላቸው ብቻ ቢገባቸውም ባይገባቸውም....... አንገታቸውን ደፍተው አሜን!........ አሜን! ማለት ብቻ!፡፡

ዛሬ በትንሽ ብር ልንገዛው የምንችለው መፀሀፍ ቅዱስ እኛ ጋ የደረሰው ብዙ ዋጋ ተከፍሎበት ነው፡፡ ብሉይ ኪዳን የተፃፈበት ቋንቋ እብራይስጥ (Hebrew) ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ (Greek) ነው፡፡ ከነዚህ ቋንቋዎች ውጪ መፀሀፍ ቅዱስ የሚገኝበት ብቸኛ ቋንቋ ላቲን ነበር፡፡ መፀሀፍ ቅዱስን ወደ ሌላ ቋንቋ ለመተርጎም መሞከር እንኳን በሞት ያስቀጣ ነበር፡፡ ቆይቶ ታዲያ በ1380ዎቹ በጆን ዋይክሊፍ የተጀመረው ወደ

እንግሊዘኛ የመተርጎም ስራ እነ ጆን ሀስን የመሳሰሉ የኦክስፎርድ ምሁራንን ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎ በ1560 የመጀመርያው የእንግሊዘኛ ትርጉም "The Geneva Bible" በመባል ለህትመት በቅቷል፡፡ በ1611 ደግሞ በንጉሱ ኪንግ ጀምስ ትዕዛዝ በ 50 ምሁራን የተዘጋጀው የእንግሊዘኛ መፀሀፍ ቅዱስ "The King James Bible" ተብሎ ለህዝብ ጥቅም ቀርቧል፡፡

ዛሬ በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በትግርኛ..... በሌሎችም የእኛው ቋንቋዎች ተተርጉሞ በእጃችን አለ፡፡ የእግዚአብሔር ታላቅ ስጦታ ነው፡፡ ብዙ በአለማችን ኖረው ያለፉ ታላላቅ ሰዎች መፀሀፍ ቅዱስን በሚገባ የሚያነቡ ነበሩ፡፡ ታላቁ ፀሀፊ ዊልያም ሼክስፒር በተለያዩ ፅሁፎቹ ላይ ከመፀሀፍ ቅዱስ በሺ የሚቆጠር ጊዜ ጠቅሷል፡፡ እንደውም መፀሀፍ ቅዱስን ያላነበበ የተዋጣለት ደራሲ ይገኛል ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ እውነተኛ የስነ-ፅሁፍ ጥሪ ያላቸው ሰዎች መፀሀፍ ቅዱስን ቢያንስ ስለ ታለቅ ሊትሬቸርነቱ ያነቡታል፡፡

ለመጀመርያ ጊዜ መፀሀፍ ቅዱስን ሳነብ በጣም አስቸግሮኝ ነበር፡፡ ደጋግሜ ሳነበው ግን እየገባኝ መጣና ወደድኩት፡፡ ዛሬ በየቀኑ ከሰባት ያላነሱ ምዕራፎችን የማንበብ ልምድ አለኝ፡፡ ሁሌ ያስተምረኛል! ቃሉ ያፅናናኛል! ድፍረትን ይሰጠኛል፡፡ "እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው" እንዳለ ጌታ ኢየሱስ መንፈስ የሆነው ቃል የሚገባው ወደ አእምሮአችን ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ወደ መንፈሳችንም ነው (ዮሐ 6:63)፡፡ ውስጠኛውን ሰው ያጠነክረዋል!፡፡

መፀሀፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሰዎች ብዙ ጥበብና ማስተዋል ነው የሚያገኙት፡፡ "ምስክርህ ትዝታዬ ነውና ካስተማሩኝ ይልቅ አስተዋልኩ" እንዳለ መዝሙረኛው ቃሉ አስተዋይ ያደርጋል (መዝ (119):99)፡፡ "እምነት ከመስማት ነው ፤መስማትም በእግዚአብሔር ቃል" እንደሚልም የአምላካችንን ቃል መስማት እምነትን ይጨምራል(ሮሜ 10:17) ፡፡ እንዴት መኖር እንዳለብን ያስተምረናል..... መለኪያ (Standard) ያስቀምጥልናል፡፡

የመፀሀፍ ቅዱስ ቃልን ታዲያ ማንበብ ብቻ ሳይሆን ማሰላሰልም (Meditate ማድረግ) ያስፈልጋል፡፡ በዚያ ጊዜ ቃሉ ከእኛ ጋ በእምነት

ይዋህዳል፡፡ ትንሽ ህመም ሊሰማኝ ከወደደ "በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን" የሚለው ቃል በውስጤ አለልኝ! (ኢሳ 53፡5)፤ የሰይጣን ፉከራ ቢመጣ "እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ሀይል ሁሉ ላይ ስልጣን ስጥቻችኋለሁ" የሚለውን ቃል እመዝበታለሁ (ሉቃ 10፡19)፡፡ ጭንቀት ቢቀርበኝ "እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉ" የሚለው ቃል አለልኝ (1ኛ ጴጥ 5፡7)፡፡

የሚያስፈልገኝ ነገር ከጎደለብኝ "አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል" የሚለውን ቃል እሰላስላለሁ (ፊሊ. 4፡19)፡፡ ማጉረምረም ህይወቴን ሲወረው "ምስጋናን የሚሰዋ ያከብረኛል" የሚለው ቃል መለስ ያደርገኛል (መዝ(50)፡23)፡፡ ለእያንዳንዱ የህይወት ጥያቄና ፈተና ቃሉ መልስ አለው፡፡ ለእርሱም ቃሉን በማንበብ የሚወስዱት ጊዜ ኪሳራ አይሆንቦትም!፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል ታዲያ በግል ማንበብና ማሰላሰ ብቻም ሳይሆን ቃሉን በጥሩ ሁኔታ የሚያስተምሩ መምህራንና ሰባኪዎች ወዳሉበት ቤተ-ክርስትያን በመሔድ የሚሰጠውን ትምህርት...... የሚመጣውን የጌታ ቃል በጥሞና ማዳመጥ ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ ልዩ የማስተማርና የመስበክ ስጦታን ስለሚሰጥ በዚያ ፀጋ መጠቀም ብልህነት ነው፡፡

# የጥበብ እንቁ 28

## የሀገርን ህግ ማክበር !

የዘጠኝ ወር እርጉዝ ሆኖ ረጅም መንገድ መጓዝ ለማርያም ከባድ ነበር:: ለዚህ ጉዞ ምክንያት የሆነው በወቅቱ የሮማን ኢምፓየር ይገዛ የነበረው የቄሳር ትዕዛዝ ነው (ሉቃ 2፡1):: ሁሉም ሰው እንዲቆጠር ብሎ አዟል..... ጊዜው የህዝብ ቆጠራ (Census) ጊዜ ነበርና:: ይህንን ትዕዛዝ ለመጠበቅ ነው ቅድስት ማርያም በዚያ አስቸጋሪ የእርግዝና ወራት ከዮሴፍ ጋ ጉዞን ያደረገችው:: የሀገሯን ህግ..... የወጣውንም ትዕዛዝ አከበረች ::

ይህ ሚያሳየን የምንኖርበትን ሀገር ህግ፣ ደንብና ስርአት መጠበቅ እንዳለብን ነው:: ጌታ ኢየሱስ ከሚቃወመን ህግ ነፃ እንዳወጣን እናውቃለን:: የሚቃወመንን የእዳ ፅህፈት በመስቀል ላይ ጠርቆ አስወግዶታል!፤ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን!:: ነገር ግን ይህ በመስቀል ላይ ተጠርቆ የተወገደው ህግ የብሉይ ኪዳን ህግ ነው እንጂ የሀገር ህግ አይደለም:: የሀገር ህግ መከበር እንዳለበት ጌታ እራሱ በአስታቴር ግብርን በመክፈል አሳይቷል (ማቴ 17፡27)::

ምንም እንኳን እኛ ሰማያዊ ዜጋ ብንሆንም...... በምድርም ደግሞ እንግዶችና መፃተኞች ነን ብለን ብናምንም....... በዚህ በምድር እስካለን ድረስ የሀገር ዜጎችም ነንና እንደ ማንኛውም ዜጋ ህግን ማክበር ይጠበቅብናል:: እንደውም መንፈሳዊ ሰዎች ነን ካልን ከሌሎችም ሰዎች በበለጠ ህግን ማክበር አለብን:: "በፊትህ የተከፈተ በርን ሰጥቼሀለሁ"...... "የሚቋቋምህ ማንም የለም" ቢባልልንም ቀይ የትራፊክ መብራት ሲበራ ግን መኪናችንን ማቆም ግዴታችን ነው:: ይህንን ባናደርግ የሚያገኘን ትራፊክ በጥቅስ የሚመለስ አይደለም::

ህገ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ የመጣ ዱብ እዳ አይደለም:: ህገ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚነገርለት የበለጠ አሜሪካ ውስጥ

ይዘመርለታል:: አሜሪካውያን የፌደራል መንግስት ሆነው በአንድነት የመቆም ተስፋቸው ህገ መንግስታቸው ነው:: ስለዚህም እንደ አባታቸው ርስት ነው የሚጠብቁት:: የሰው ልጅ እኩል እንደሆነ የሚያስማማቸው እርሱ ነው:: አንድ ሰው የአሜሪካን ዜግነትን ለመውሰድ ሲያመለክት ፈተና ይፈተናል:: ከፈተናው ጥያቄዎች ብዙዎቹ ህገ መንግስታቸውን የሚመለከቱ ናቸው::

በአንድ ሀገር ስንኖር ህገ መንግስትንም ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ የተደነገጉ ደንቦችንና ስርአቶችን ሁሉ መጠበቅ ያስፈልጋል:: ታክስን መክፈልም በኢትዮጵያውያን ላይ የመጣ መከራ አይደለም:: ሁሉም መንግስታት የሚንቀሳቀሱት ከህዝብ በሚሰበሰብ ታክስ ነው:: አሜሪካ ውስጥ IRS የሚባል ይህንን የሚቆጣጠር ድርጅት አለ:: በታክስ ጉዳይ ላይ ቀልድ አያውቅም፤ ተከታትሎ....... አሳዶ ነው የሚይዘው!::

ወደ ሌሎች ሀገራትም ለስራም ሆነ ለእረፍት በምንወጣበት ጊዜ የምንሔድበትን ሀገር ህግ መጠበቅ ይጠበቅብናል:: በሀገሩ ያለውን ደንብና ስርአት መከተል አለብን:: ብዙ ጊዜ ከእኛ አገር ወደ ሎንዶን ኢንግላንድ የሚሔዱ ሰዎች ለመኪና አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ:: ምክንያቱም በለንደን ያለው የመኪና ፍሰት አቅጣጫ ከኢትዮጵያ ተቃራኒ ስለሆነ ለመሻገር ሲፈልጉ ስለሚደናገሩ ነው:: እዚህ ቀኛችንን ይዘን እዚያ ደግሞ ግራቸውን ይዘው ይነዳሉ...... መሪውም የእኛ በግራ የእነርሱ ደግሞ በቀኝ ነው::

እንኳን ሀገርና የትኛውም ቤት ወይም ድርጅት ስንገባ የቦታውን ስርአት ወይም ፕሮቶኮል መጠበቅ አለብን:: ለምሳሌ ካናዳና ስዊድን ቤት ሲገባ ጫማ ማውለቅ በጣም የተለመደ ነው:: አሜሪካ ደግሞ ብዙም አይጨነቁም:: እኔ ምንጣፍ አነጥፎ "አትርገጡ" የሚባል ነገር ባልወድም እነዚህ አገሮች ስሔድ ግን ጫማዬን ማውለቅ አልረሳም:: የሀገሩ..... የቤቱ ስርአት ነው:: ህግና ስርአትን መጠበቅ እግዚአብሔር ያብዛልን:: ሰው ሁሉ በትክክል ህግን ቢጠብቅ አለማችን ምን አይነት አለም ትሆን ነበር ?::

## የጥበብ እንቁ 29

# ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት !

ቅድስት ማርያም የወለደችው ልጇ ክርስቶስ እንደሆነ ታውቃለች፡፡ በመጀመርያ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ እርሱ እንደሆነ ትረዳለች፡፡ "እግዚአብሔር ሁሉን በእርሱ ፈጠረ...... ሁሉን ለእርሱ ፈጠረ..... በመጨረሻም ሁሉን በእርሱ ይጠቀልለዋል" ብላ ታምናለች፡፡ እርሱ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር እንዳልሆነ እርሷንም ሳይቀር እርሱ እንደፈጠራት ጠንቅቃ ታውቃለች፡፡ በዚህ ዩኒቨርስ ያሉ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ከዋክብት በእርሱ ዲዛይን ተደርገው የተሰሩ እንደሆኑና እያንዳንዳቸውንም በስማቸው እንደሚጠራቸው ታስተውላለች፡፡

አብሯት ሲኖር ፍፁም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍፁም አምላክም እንደሆነ ከእርሷ ተሰውሮ አያውቅም፡፡ ሰማይ....... ከሰማይም በላይ ያለው ሰማይ ይይዙት ዘንድ የማይችሉት አምላክ ከእርሷ ከድንግሷ መወለዱ ሁሌ ሳይገርማት አይቀርም፡፡ "እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ክርስቶስ ሰው ሆኖ እንዲወለድ ያደረገበት ጥበቡ ይበልጣል" ይባላል፡፡ እውነትም ነው!፡፡ ቃል ስጋ የሆነበት ሚስጥር (The Incarnation) ከአእምሮ በላይ ነው!፤ ኢየሱስ የጌቶች ጌታ የነገስታት ንጉስ ነው!፤ ያለ...... የነበረ...... ለዘላለም የሚኖር!፡፡

ቅድስት ማርያም ታዲያ ለዚህ ታላቅ ጌታ የሚገባውን ክብር ሁሉ ትሰጠው ነበር፡፡ ከእኔ ተወልዷል ብላ ዝቅ አላደረገችውም፡፡ በልዩ ጥንቃቄ፣ በልዩ አክብሮት ነበር የያዘችው፡፡ ድንግል ፈጣሪዋን ብትወልደውም "ከእኔ ተወልደሀልና ላከብርህ አልችልም" አላለችውም፡፡ የእርሱ ደቀመዛሙርት የሆኑት ሁሉ ክብርን ለእርሱ ሲሰጡት....... ሲንበረከኩለት...... ሲሰግዱለት ደስታዋ ወደር አልነበረውም፡፡ አምላክ መሆኑ ስለገባት፣ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንም ጠንቅቃ ስለተረዳች የሚገባውን ክብር ሁሉ

ትሰጠው ነበር፡፡ እርሷ እንደሁ ትሁት ነች!፤ እንኳን ከክርስቶስ ከፈጣሪዋ ጋ ቀርቶ ከሌሎችም ጋ ራስዋን አላስተካከለችም!፤ ከብር ለሚገባው ለእርሱ ከብርን ሰጠች!፡፡

የቅድስት ማርያም ወዳጆች የሆኑ ሁሉ ይህንን ያደርጋሉ፡፡ የነገስታቱን ንጉስ ኢየሱስ ክርስቶስን ያመልኩታል፡፡ በጉልበታቸው ይንበረከኩለታል!........ በአንደበታቸውም "ጌታችን ነህ!" ይሉታል....... ይዘምሩለታል......... ይሰግዱለታል....... በፊቱ በግንባራቸው እየወደቁ "ይገባሀል!" ይሉታል፡፡ ከዚህ የበለጠ ማርያምን ደስ የሚያሰኛት ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡

ታዲያ አንዳንዴ በህዝባችን በሀበሾቹ መሀል በአንዳንድ ሰዎች ላይ የማየው የእውቀት ማነስ ውጤት የሆነ ነገር ያስገርመኛል፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በድንገት "በኢየሱስ ስም" ብሎ ያንን ክቡር ስም ቢጠራ "ይሄ ጴንጤ!" ይለዋል፡፡ ወይም ምፅዋት የሚለምን ሰው "ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ" ብሎ ቢለምን "ይሄ ጴንጤ ነው!" ብሎ ሊዘልፈው ይሞክራል፡፡ በቤተ-ክርስትያን ውስጥ አንድ መምህር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ደጋግሞ ከተናገረ ...... "ይሄ ሰው ወዴት እየሔደ ነው?" የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡

ግን ኢየሱስ የጴንጤ ነው? የካቶሊክና የኦርቶዶክስ ክርስትና መሰረቱ ኢየሱስ አይደለምን?፤ እነ ዘርፌ........ እነ ምርትነሽ...... እነ ዲያቆን እዝራ የሚዘምሩለት "የማልደራደርበት" ያሉት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?፤ እነ መምህር ምህረተ አብ........ እነ መምህር ታሪኩ ......... እነ መምህር በጋሻው የሚሰብኩት.......... ስለማንነቱ የሚሟገቱለት እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን?፤ ታዲያ የትኛው የኦርቶዶክስ መምህር ነው "ፕሮቴስታንቶች የሚያመልኩት ኢየሱስ ሌላ ኢየሱስ ነው" ብሎ ያስተማረ?፤ እንግዲያውስ በክርስቶስ አካል ሁሉ የሚሰበከው አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!፡፡

አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሰራላቸውን ስራ ተረድተው....... ደንቋቸው....... በእርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ተማርከው "አንተ ጌታ ነህ!" ሲሉት......... በገባቸውም መንገድ ሲያመልኩት...... አጥብቀው ይጣሏቸዋል፡፡ "መቃብሬ ላይ እንዳትቆም!

መቃብርህ ላይ አልቆምም" ይላሉ!፤ "ልጄ አይደለህም!" ብለው ይከዳሉ!... ይቆጣሉ!..... ይረግሙአቸዋል!፤ አንዳንዶቹ ልጆቻቸውን "ሐይማኖት ቀይረሀል" በሚል ሰበብ አሳደዋቸው ፊታቸውን ካዩአቸው አስር አመት ይሆናቸዋል፡፡ ግን እንደው በውኑ የማርያም ወዳጅ ልጆቹን ያሳድዳል? መቃብሬ ላይ እንዳትቆም ይላል?፤ "ፊትሽን ማየት አልፈልግም"..... "እህል ካንቺ ጋ አልቀምስም" ይላል?፤ የማርያም ወዳጅ ይህንን ያደርጋል?፡፡

በታላላቅ የክርስትና እምነት ተቋማት መካከል አንዳንድ የአስተምህሮና የስርአት (Tradition) ልዩነቶች ይኖራሉ፡፡ በፕሮቴስታንቶች መሀከል ብቻ እንኳን ብዙ መከፋፈልና ልዩነት አለ..... በኦርቶዶክሶችም መሀል እንዲሁ!፡፡ ሁላችንም የምናመልከው እግዚአብሔር ግን አንድ ነው፡፡ መቼም አንዳንዴ ታናሽ ታላቅን ይመክራልና ዛሬ ልምከርዎት....... "አይንሽን ላፈር" ያሉዋትን ልጅዎን ጠርተው ይመርቋት!፡፡ "ፊቴን እንዳታይ!........ ቤቴ እንዳትመጣ!" ያሉትን ልጅን ጠርተው ይባርኩት፡፡ ምናልባት ይህንን አለም ጥለን ስንሔድና በእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ እንዳናፍር እንጠንቀቅ!፤ እርቅና ሰላም ይሁን!፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች በመስቀል ላይ በቃላት ለመግለፅ የሚያስቸግር ዋጋ ከፍሏል፡፡ "መፅሀፉን ትወስድ ዘንድ ማህተሙን ትፈታ ዘንድ ይገባሀል!....... ታርደሀልና!" ተብሎለታል (ራዕይ 5፡9-10)፡፡ ስለዚህም እርሱ ሊልቅ...... ሊከብር ይገባዋል!፤ ቅድስት ማርያምም....... የእርሷም ወዳጆች ይህንን አይቃወሙም!፤ በዚህ እጅግ ደስ ይላቸዋል እንጂ! ፡፡

## የጥበብ እንቁ 30

## ልብን በማዳመጥ መመራት !

ስለ ቅድስት ማርያም ከተፃፈልን ጥቂት ነገር እንደምንረዳው ከሆነ ማርያም ያደረገችውን ሁሉ ያደረገችው ከእግዚአብሔር በምታገኘው ምሪት ነበር። ትፀንሻለሽ ተባለች...... ፀነሰች፤ ወደ ግብፅ ሒጂ ስትባል ወደ ግብፅ ሔደች፤ ተመለሺ ስትባል ደግሞ ተመለሰች። እግዚአብሔር እንዲህ አይነት ምሪቶችን የሰጣት አንዳንዴ መልአኩን በመላክ ሌላ ጊዜ ደግሞ ለዮሴፍ ህልም በማሳየት ነበር። ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ስትሔድ ግን መልአክም አልተገለጠላት....... ህልምም አላየችም። ልቧን አዳምጣ ሔደች!።

በህይወታችን በአንዳንዱ ቀን "ዛሬ ከቤት መውጣት ምንም አልተሰማኝም!" እንላለን። "ይገርምሻል! እዚያ ቦታ ሄጄ ቅፍፍ አለኝና ቶሎ ወጣሁ!" ትላለች ለጓደኛዋ። "ከዚያ ሰው ጋ ተቀምጬ ውስጤ ከብድ አለኝ! ምን እንደሆነ አላውቅም!" ይላል ሌላው። አንዳንዶች ይህንን አይነቱን ምሪት "ኢንስቲንክት" (Instinct) ወይም (Intuition) ይሉታል። መንፈሳዊ ልምምድ ያላቸው ደግሞ "የመንፈስ ቅዱስ ምሪት" ይሉታል።

ማታ ህፃን ልጇን ያስተኛች እናት ምንም ድምፅ ሳትሰማ የሆነ ነገር "ተነሺ" ብሏት ወደ ልጇ መኝታ ቤት ትሔዳለች....... ልጇንም ታፍኖ ታገኘዋለች...... ከአደጋም ታተርፈዋለች። ምን እንደ መራት........ ምን እንደቀሰቀሳት የምታውቀው ነገር የለም። ቤታችንን ቆላልፈን ልንወጣ ስንል ተመልሰን የማብሰያ ከፍሉን እንድናይ በውስጣችን ይሰማናል። እዚያም ስንሔድ ያልጠፋ እሳት እናገኛለን!..... ቤታችን ከእሳት አደጋ ተረፈ ማለት ነው። በኒውዮርክ የምትኖር አንዲት ዘመዴ በአውሮፕላን ጉዞ ልታደርግ ትኬት ቆርጣ ቀኑ ሲደርስ ጨነቃት...... ውስጥዋ በጣም ተረበሸ። ስለዚህም ጉዞዋን ተወችው!...... ልትሳፈርበት የነበረው አውሮፕላን ግን ወድቆ ተከሰከሰ።

መንፈሳዊውን አለም በደንብ ስንረዳ ደግሞ ነገሩ ከኢንስቲንክት አልፎ እናገኝዋለን:: መንፈሳዊ ሰው በመሆኔ ደስ ከሚሉኝ ምክንያቶች አንዱ መንፈስ ቅዱስን ማግኘቴ ነው:: አንድ ሰው ስለ ሀጢያቱ በሞተለትና ከሙታንም በተነሳው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ሙት የነበረ መንፈሱ ህይወትን ያገኛል:: ከዚያም በኋላ የማይነገረውን ታላቅ ስጦታ ይቀበላል:: ያም ስጦታ መንፈስ ቅዱስ ይባላል!:: መንፈስ ቅዱስ እንደሚያውቁት የስላሴ ሶስተኛው አካል ነው:: ማርያምም የፀነሰችው ከእርሱ ነው!፤ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል....... የልዑልም ሀይል ይፀልልሻል" እንደተባለ ሁለንተናዋን የወረሳት እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነበር (ሉቃ 1:35) ::

በግል ሲያውቁት መንፈስ ቅዱስ መልካም ወዳጅ ይሆናል:: መልካም አስተማሪ........ መልካም መሪ....... ሆኖ አብሮ ይኖራል:: ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ተጠምቆ ሲወጣ በተቀደደው ሰማይ እንደ እርግብ የወረደበት እርሱ መንፈስ ቅዱስ ነው:: ጌታ በዲያብሎስ እንዲፈተን ወደ ምድረበዳ የተወሰደውም በመንፈስ ቅዱስ ነበር:: ከምድረበዳም የተመለሰው በእርሱ በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ነው:: ጌታ ኢየሱስ ለሶስት አመት ተኩል ሲያገለግል የመንፈስ ቅዱስ ሀይል አብሮት ሰራ:: መንፈስ ቅዱስን ከመውደዱና ከማክበሩ የተነሳ እርሱን መንፈስ ቅዱስን የሰደበ እንደማይሰረይለት ተናግሯል (ማቴ 12:32):: ከጌታም በኋላ እነ ቅዱስ ጴጥሮስ...... እነ ቅዱስ ጳውሎስ....... ወንጌልን የሰበኩትና ተአምራትን ያደረጉት በእርሱ ነው::

ሁላችንን እግዚአብሔር ስለፈጠረን ለሁላችንም ይጠነቀቃል::ከከፉ ሊታደገን ስለሚፈልግ በልባችን ውስጥ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጠናል:: የሚያርጉትን ሁሉ ሲያደርጉ ልቦን እያዳመጡ ያድረጉ!:: አንድ ጊዜ ዘመዶቼ ከድግስ ቤት ምግብ ይዘውልኝ መጡ፤ የመጣውን ምግብ ልበላ ስል ውስጤ በፍፁም እምቢ አለኝ:: ተውኩትና ቁራሽ ዳቦ በልቼ ተኛሁ:: በማግስቱ ስሰማ ለካ እዛ ድግስ ቤት የነበረ ሰው ሁሉ ሆዱን ታሞ ነው ያደረው!፤ እኔ ግን ልቤን አደመጥኩኝ...... አመለጥኩኝ! ::

እንዲህ ልብን እያዳመጡ መመላለስ በተለይም ደግሞ መንፈስ ቅዱስን አውቆ መኖር ሌላም ልዩ ጥቅም አለው:: ሰዎች ታላላቅ መነሻ ሀሳቦችን (ideas) የሚያገኙት በመንፈስ ሲሆኑ ነው:: ድሮ ድሮ የቀዶ ጥገና

ህክምና የሚሰጠው ያለ ሙሉ ማደንዘዣ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ታካሚዎቹ ብዙ ስቃይ ይቀበሉ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ጊዜ ዶ/ር ጄምስ ሲምፕሰን የተባሉ ሀኪም መፀሀፍ ቅዱስ ሲያነቡ እግዚአብሔር ሔዋንን ለመፍጠር በአዳም ላይ ልዩ የቀዶ ጥገና ስራ እንደሰራ ያያሉ፡፡ አምላክ ይህንን ሲያደርግ ታላቅ እንቅልፍ በአዳም ላይ እንደጣለበት ያስተውላሉ!፤ በዚህ ሰአት ዶክተሩ አንድ ሀሳብ መጣላቸው፡፡ "ቀዶ ጥገና በምንሰራበት ጊዜ ታካሚዎቹ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሳያውቁ መተኛት አለባቸው!" የሚል ሀሳብ!፡፡ እንደዚያ የሚያደርግም መድሀኒት ሲፈልጉ ክሎሮፎርም (Chlorophorm) የተባለውን መድሀኒት ለዩ፡፡ በራሳቸውም ላይ ሙከራ ካደረጉ በኋላ ለጥቅም አዋሉት፡፡ ይሄው እስከዛሬ ድረስ ክሎሮፎርም እየተሰራበት ይገኛል፡፡

ልክ እንደዚሁ በጥቅም ላይ የነበረውና አሁን በኮምፒውተሮች የተተካው ታይፕ ራይተር የተፈለሰፈው በመንፈስ በነበሩ....... ልባቸውን ባዳመጡ ወጣቶች ነበር፡፡ ጓደኛሞች ናቸው፤ ቤተ-ክርስትያን ይሔዳሉ፤ ሁል ጊዜ ሲያስተውሉ ታዲያ ፓስተራቸው በጣም ስራ ስለሚበዛበት ማስታወሻው በትክክል ያልተስተካከለና የተዘበራረቀ ነበር፡፡ ጓደኛሞቹም "ለምን የሚፅፍ መሳርያ አንሰራም" አሉ....... ሀሳብ (idea) መጣላቸው፡፡ ፊደሎቹንም አንድ ባንድ እየቀረፁ አዘጋጇአቸው፡፡ ከጥቂት ጊዜም በኋላ ዘናጭ ታይፕ ራይተር ሰሩ፡፡ ይህንን የተመለከቱ የክርስትያን ወጣት ሴቶች ማህበር መሪዎች ደግሞ ቶሎ ብለው ሴቶች ታይፕ መምታት እንዲማሩ ስላደረጉ ብዙ ሴቶች ታይፒስቶች ሆኑ፡፡

እንግዲህ ታላላቅ አይዲያዎችን ከፈለጉ....... ወደ መንፈስ ቅዱስ ይጠጉ፤ በፀሎና ይሁኑ፤ ልብዎን ያዳምጡ!፤ እኔ እንዳየሁት በአገራችን ...... በአርቱ..... በሳይንሱ....... በቢዝነሱ አለም ያለው ትልቁ ችግር የአይዲያ ችግር ነው፡፡ እግዚአብሔር ኦሪጅናል አይዲያ ከሰጦት....... አምልጠዋል!፡፡

## የጥበብ እንቁ 31

# መስጠትና መቀበልን ማወቅ !

በመስቀል ላይ በጣር ሆኖ ጌታ ኢየሱስ በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ከተናገራቸው ነገሮች መሀል ወደ ማርያም ተመልክቶ "እነሆ ልጅሽ" ያለውና ወደ ዮሐንስም ተመልክቶ "እነኋት እናትህ!" ያለው ይገኝበታል (ዮሐ 19:26-27):: ይህንንም የጌታ አደራ ማርያምም ዮሐንስም ተቀብለውታል:: ቅድስት ማርያም የዮሐንስን ልጅነት ተቀበለች!..... ለዮሐንስም እናትነቷን ሰጠች!:: መስጠትና መቀበልን ታውቅ ነበርና!::

እኛ ሀብትን ስለምን እንፈልጋለን? ምንስ ያደርግልናል? ብንበላ አንድ እንጀራ ነው!፤ ብንተኛ አንድ አልጋ ላይ!፤ ብንነዳም አንድ መኪና ነው:: ከማየት ዉጪ ለባለ ሀብቱ ሀብት ምን ፋይዳ አለው?:: እንደኔ ከሆነ የብልፅግና ትልቁ በረከቱ ያለ ችግር ለሌሎች መስጠት ማስቻሉ ነው:: በመስጠት ውስጥ ያለ ደስታ እውነተኛ ደስታ ነው:: የእግዚአብሔርን ስም ብዙ የማያነሱ ባለጠጋ የሆኑ ሰጪዎች ወይም 'ፊላንትሮፒስቶች' (Philanthropists) እንኳን በመስጠት ታላቅ ደስታን ያያሉ...... እርካታን ያገኛሉ:: እንደውም እነርሱ የመስጠት ሱስ እንዳለባቸው ነው የሚታሰበው!...... ጥሩ ሱስ ነው ይሄኛው!::

መስጠት ለጤንነትም ጥሩ ነው:: የሆድ ድርቀት (Constipation) ብዙ ሰዎችን እንደሚያሰቃይ ይታወቃል:: ታዲያ የሆድ ድርቀት ብዙ መንስኤዎች ሲኖሩት ከነዚህ አንዱና ብዙ ጊዜ የማይታሰበው መንስኤ ከመጠን ያለፈ ንፉግነት ነው:: አንዳንድ ሰዎች ሸቶ ይገዙና ሸቶው ካለቀ በኋላ እንኳን ቢልቃጡን አይጥሉትም:: ልብሳቸው ምን ቢበዛ....... ቁም ሳጥን ቢጠብ አውጥተው ለሰው አይሰጡም:: አዲስ ሶፋ ገዝተው አሮጌውን ለሰው በመስጠት ፋንታ ቤቱን አጣበው ጥግ አሲዘው ያስቀምጡታል:: ታዲያ ለነዚህ ሰዎች ትልቁ የሆድ ድርቀት ህክምና በቤታቸው ያለውን አሮጌ እቃ

ሁሉ አውጥተው እንዲሰጡ ወይም እንዲጥሉ ማድረግ ነው፡፡ ያንን አውጥተው ሲጥሉ በሆዳቸውም ያለ መውጣት ያለበት ነገር ሁሉ ይወጣል፡፡

በመስጠት ብዙ በረከት አለ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል የምንከተል ከሆነን በመጀመርያ ለእግዚአብሔር ቤት አስራታችንን መስጠት አለብን፡፡ ከገቢያችን አስሩ ፐርሰንት የእኛ አይደለም!...... የእግዚአብሔር ነው (ሚል 3፡8-10)፡፡ የሰማይ መስኮቶችን የሚያስከፍተው ይህ ነው፡፡ ለቤተ-ክርስትያን መስጠት ፈፅሞ ኪሳራ አይደለም፡፡ ይህን ካደረግንም በኋላ ያለንን ለሌሎች ለተቸገሩ ማካፈል መልካም ነው፡፡ የምንሰጠው ነገር ሁሉ በብዙ ተባዝቶ በሰፈርንበት በዚያው መስፈርያ ተሰፍሮ....... ተሞልቶ........ ተነቅንቆ...... ተጨቁኖ......ተትረፍርፎ ይመጣልናል (ሉቃ 6፡38)፡፡ መስጠት እጅግ አስፈላጊ የህይወታች ልምምድ ነው፡፡

መስጠት ግን ገንዘብና ንብረትን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ፍቅርን መስጠት አለ!፤ ይህም ሰው እንደማይወዳቸው የሚያስቡ ሰዎችን "በክርስቶስ ፍቅር አወድሀለሁ" ማለት....... በስራም ያን ፍቅርን ማሳየት........ በችግራቸው ስለ ፍቅር ብሎ መገኘት ነው፡፡ ደግሞም ጊዜን መስጠት አለ፤ ነገራቸውን ሊያማክሩንና ከእኛ ሊማሩ ለሚወዱ ሰዎች ጊዜን መስጠት!፡፡

በመስጠት ብልፅግና ወደ እኛ ይመጣል፡፡ ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር ናት፡፡ እኛ የምንሰጥና ያለንን የምናካፍል ከሆነ እርሱ አትረፍርፎ ይሰጠናል፡፡ ሁሉም የእርሱ ነው!፡፡ የአለማችን ቁጥር አንድ ባለፀጋ ሰው የሜክሲኮው ካርሎስ ስሊም ናቸው፡፡ ከእርሳቸውም ቀጥሎ ደግሞ የአሜሪካው ቢልጌትስ ይከተላሉ፡፡ በሶስተኛ ደረጃም ከዚያው ከአሜሪካ ዋረን ባፌት ተሰልፈዋል፡፡ እነዚህን ቢሊየነሮች እናደንቃቸዋለን!፤ አላቸው እንላለን!፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ "ብሩ የእኔ ነው፤ ወርቁም የእኔ ነው!" ይላል (ሐጌ 2፡8)፡፡ በምድር ላይ ያለው ሀብት በሙሉ የእርሱ ነው፡፡ ለፈለገው ሰው በአደራ ይሰጠዋል፡፡ ታዲያ እኛ ሰጪዎች ከሆንን የጌታ ብልፅግና በአደራ ከሚሰጣቸው መሀል እንሆናለን፡፡ ታማኝ አድርጎ ይቆጥረናልና፡፡

መስጠት ብቻ ግን አይደለም። መቀበልም መቻል አለብን። አንዳንድ ሰዎች አጋጥመውኛል። በጣም ሰጪዎች ናቸው!፤ መቀበል ግን አይችሉም!፤ የሚያገኙዋችሁ እነርሱ ጋባዥ ከሆኑ ብቻ ነው። መጋበዝ ይከብዳቸዋል። መቀበል ትህትናን ይጠይቃል። ለመስጠትም ለመቀበልም ፈቃደኞች መሆን አለብን።

# የርህራሄ ስራን መስራት !

በቃና ዘገሊላ ሰርግ ተዘጋጀ፡፡ ኢየሱስና ማርያምም ተጋብዘው ከታደሙት ውስጥ ነበሩ፡፡ ሰርጉም በጥሩ ሁኔታ እየተካሔደ ሳለ ግብዣው ሳያበቃ ለሰርጉ የተዘጋጀው ወይን ጠጅ አለቀ፡፡ ይህ ሰርግን ለደገሰ ሰው እጅግ አስደንጋጭ ነው!፤ ያዋርዳልም!፡፡ አጋጣሚ ሆኖ የወይን ጠጁን ማለቅ ማርያም ሰምታለች....... ወይም ሆን ብለው ነግረዋት ይሆናል፡፡ ማርያም ተጋባዥ እንግዳ ስለ ሆነች ማድረግ የነበረባት እንዳልሰማች ሆና የቀረበላትን በልታ ወደ ቤቷ መሔድ ነበር..... ሰርጉን ከደገሱት መሀል አልነበረችምና፡፡ እርሷ ግን አላስቻላትም!፤ ወደ ኢየሱስ ተጠግታ "የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም!" አለችው (ዮሐ 2፡1-5)፡፡ ይህ የሚያሳየው ለሌሎች እንዴት ታስብ እንደነበረና ስትችልም ቸርነትን ታደርግ እንደነበረ ነው፡፡ ማርያም ሩህሩህ ነበረች!፡፡

በአሜሪካ የሚገኝ አንድ ጎል አፕ (Gallup) የሚባል ድርጅት አለ። ይህ ድርጅት በየአመቱ ከህዝብ አስተያየት በመሰብሰብ የአመቱን ድንቅ ሰዎች ዝርዝር ያወጣል፡፡ በ 1999 ዓ/ም ግን ድርጅቱ ያወጣው በ 20ኛው ክፍለ ዘመን...... በ 100 አመታት ውስጥ........ ከኖሩ ሰዎች በጣም ድንቅ (Most admired) የተባሉት ሰዎችን ስም ዝርዝር ነበር፡፡ በዚህም መሰረት የ 18 ሰዎችን ስም በደረጃ አወጣ፡፡ ለምሳሌ 16ኛው ደረጃ ለኔልሰን ማንዴላ ተሰጥቷል፡፡ ከአስረኛው ደረጃ ጀምረን እስከ አንደኛው ብናይ...... አስረኛ ደረጃ የተሰጣቸው የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ዊንስተን ቸርቺል ነበሩ፡፡ በዘጠነኛ ደረጃ የአሜሪካ 32ኛ ፈርስት ሌዲ የነበሩት ኤልየኖር ሮዝቬልት ተቀመጡ፡፡ የስምንተኛው ደረጃ የሮማ ካቶሊክ ቤተ-ክርስትያን ፖፕ ለነበሩት ለጆን ፖል ሁለተኛ ተሰጣቸው፡፡ ሰባተኛውን ደረጃ ደግሞ ታላቁ ወንጌላዊ ቢሊ ግራሃም ወሰዱ፡፡

ሲቀጥል የስድስተኛ ደረጃን የአሜሪካ 32ኛ ፕሬዚደንት የነበሩት ፍራንክሊን ሮዘቬል ሲወስዱ የአምስተኛው ደራጃ ማየትና መስማት የተሳናት ግን አስደናቂ አስተማሪና ፀሀፊ ለነበረችው ለሔለን ኬለር ተሰጣት፡ እንዲሁም አራተኛው ደረጃ ላይ ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን ተቀመጠ፡፡ ከዚህ ሲቀጥል የሶስተኛ ደረጃን 35ኛው የአሜሪካ ፕሬዘደንት የነበሩት ጆን ኤፍ ኬኔዲ ሲያገኙ የሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ለታላቁ የጥቁር አሜሪካ የነፃነት ታጋይ ለማርቲን ሉተር ኪንግ ተሰጠ፡፡ መቼም ታዲያ "አንደኛ ማን ሊወጣ ነው?" ብለው ቢጓጉ አይገርመኝም፡፡ እጅግ የሚያስደንቀው አንደኛ ደረጃን ያገኙት ታላቅ የርህራሄ ሰው የነበሩት ማዘር ቴሬዛ ነበሩ፡፡ በሀያኛው ክፍለ ዘመን...... በ100 አመታት ውስጥ ከኖሩ ሰዎች ሁሉ እጅግ በጣም የተከበሩ ድንቅ ሰው ማዘር ቴሬዛ ናቸው፡፡

እኚህ አልቤንያ በምትባል የምስራቅ አውሮፓ አገር የተወለዱ ሴት ገና በልጅነታቸው ነበር ሚሽነሪ ለመሆን የተመኙት፡፡ ጊዜው ሲደርስ በ 18 አመታቸው መንኩሰው ወደ ህንድ ካልካታ አቀኑ፡፡ ለሀያ አመታት በገዳም እየኖሩ እንግሊዘኛን ያስተምሩ ነበር፡፡ የህንድ ቋንቋንም አቀላጥፈው ተናገሩ፡፡ ከዚህ በኃላ ግን የህዝቡን ድህነት እያዩ በሚመች ገዳም ውስጥ መቀመጥ ስላላስቻላቸው ጥለው ወጡ...... ኑሮአቸውን ከድሆች ጋ አድርገው የበጎ አድራጎት ስራቸውን ጀመሩ፡፡

ማዘር ቴሬዛ በዋናነት የሰሩት ሆስፒስ (Hospice) የሚባል ቦታ ነው፡፡ ሆስፒስ ማለት እንደ ሆስፒታል ሆኖ በሕይወት ለመኖር ተስፋ የሌላቸው ሰዎች ቀሪ ጊዜያቸውን በስቃይ እንዳያሳልፉ እንክብካቤ የሚሰጥበት ማዕከል ነው፡፡ ብዙ ስቃይና የሞት ጣር የሚታይበት ቦታ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ማዘር ቴሬዛ የስጋ ደዌ የነበረባቸውን ሰዎች ያገለግሉ ነበር፡፡ አባትና እናት የሌላቸውንም ልጆች ለማሳደግ ሰበሰቡ፡፡

እኚህ ሴት በዘመናቸው ሁሉ ለሌሎች እየኖሩ ታላቅ የርህራሔን ስራ ሰርተዋል፡፡ አገልግሎታቸው አለም አቀፍ እውቅናን አግኝቶ ስለነበር የ 1979 ዓ/ም የኖቤል የሰላም ሽልማት ተሸላሚ ሆኑ፡፡ ሚሽነሪስ ኦፍ ቻሪቲ (Missionaries of Charity) የተባለውም ድርጅታቸው በጣም አድጎ በ 123 አገሮች 610 ሚሽነሪዎችን ለመላክ ችለዋል፡፡ ማዘር ቴሬዛ ደጋግመው

የሚናገሩት አንድ ንግግር ነበራቸው..... "እኔ በትውልዴ አልባንያዊት ነኝ..... በዜግነቴ ደግሞ ህንዳዊት ነኝ...... ልቤ ግን ሙሉ በሙሉ የኢየሱስ ነው!" ይሉ ነበር:: እግዚአብሔር በአንዲት ህይወታቸውን በሰጡት ሴት ትልቅ ስራን ሰራ:: ይህንን ሁሉ ስናነብ ግን "የማዘር ቴሬዛ ሚስጥራቸው ምንድን ነበር ?" ብለን ልንጠይቅ እንችላላን:: ሚስጥራቸው....... ርህራሄ (Compassion) ነበር!::

እኛስ ?፤ ስንቶቻችን ለተጎዱና ለተጠቁ (Underprivilaged ለሆኑ) ሰዎች እንቆማለን?:: ሁላችንም የበጎ አድራጎት ድርጅት እናቋቁማለን ማለት አይደለም:: ግን ቢያንስ ለአንድ ሰው መቆም አይቸግረንም:: በአንድ ህዝብ መሐል የርህራሄ አገልግሎት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ሰው ለራሱ ገንዘብ አጠራቅሞ፣ ቤቱን በረዥምና በአደገኛ አጥር አጥሮ "የራሳችንን ኑሮ ብቻ እንኑር" ማለቱ ጌታንም ህሊናችንንም የሚያስደስት አይደለም::

አርሱ እግዚአብሔር የታመሙትን በማስታመም፣ የታሰሩትን በመጠየቅ፣ የታረዙትን በማልበስ፣ የተራቡትን በማጠጣት ደስ ይለዋል:: እንደዚህ የሚያደርጉ ሰዎችንም ያከብራል፣ ይባርከማል:: "ተርቤ አብልታችሁኛልና፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና" የሚለውን የታላቁን ጌታ የኢየሱስን ቃል ባነበብኩት ቁጥር በጣም ይነካኛል (ማቴ 25፡35-36)::

በበኩሌ ሁላችንም ቢያንስ አንድ የርህራሔ ስራ መስራት አለብን ብዬ አምናለሁ:: አንድ አባትና እናት የሌለው ህፃን ወስደን ማሳደግ...... ወይም አንድ ጧሪ የሌላቸውን አዛውንት መንከባከብ....... ወይ ደግሞ እርዳታ የሚያስፈልገውን አንድ አካል ጉዳተኛን ማገዝ...... ውስጣችን እንደመራን ማድረግ ነው:: በምድራችን የተለያዩ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አሉ:: ከእነዚህም እውነተኛና ንፁህ ስራ እንደሚሰሩ የተመሰከረላቸው ድርጅቶች እንዳሉ ይታወቃል:: ከእነርሱ ጋ በመቆም የተለያየ ችግር ያለባቸውን ሰዎች ብንረዳ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋችን ትልቅ ነው:: ሩህሩህ የሆነው አምላክ ልባችንን በርህራሄ ይሙላው!::

# የጥበብ እንቁ 33

## በመታዘዝ መባረክ !

"ከሴቶች መሀከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ!":: ይህ በመልአኩ ገብርኤል የመጣላት መልዕክት ነው....... ለማርያም (ሉቃ 1፡28):: መልአኩ "የተባረክሽ ነሽ!" ካላት ታዲያ እንዴት ነው የተባረከችው?:: ያ ዘመን ጌታ ከመወለዱ በፊት ስለ ነበር የብሉይ ኪዳን ዘመን ነበር:: ገና በኢየሱስ ደም የሆነው አዲስ ኪዳን አልመጣም:: በብሉይ ኪዳን ደግሞ ፀጋ ወይም ነፃ ስጦታ አልነበረም:: ሁሉም እንደ ስራው መጠን ነው ዋጋውን ይቀበል የነበረው:: እግዚአብሔርም የሚባርከው የሚታዘዙትን....... ቃሉን የሚጠብቁትን ነበር:: ታዲያ ማርያምም "የተባረክሽ ነሽ" የተባለችው እንዲሁ አልነበረም:: በመታዘዝ ኖራ....... የአምላኳን ቃል ጠብቃ........ በስርአቱም ሔዳ ነው እንጂ::

እግዚአብሔር በረከቱን ሁሉ ያዘጋጀው ለሚታዘዙት ነው:: "እግዚአብሔር ራስ ያደርግሀል እንጂ ጅራት አያደርግህም፤ ሁል ጊዜም በላይ እንጂ በታች አትሆንም" ያለላቸው ቃሉን በመጠበቅ ደስ የሚያሰኙትን ነው (ዘዳ 28፤13-14):: ደግሞም በመውጣትህ ብሩክ ትሆናለህ........ በመግባትህም ብሩክ ትሆናለህ፤....... የከብትህ ርቢ፣..... ቡሀቃህ፣..... ሌማትህ ብሩክ ይሆናል እያለም ተናግሮላቸዋል:: ጨምሮም "ጠላቶችህን በፊትህ የተመቱ ያደርጋቸዋል" ብሎ ቃል ገብቶላቸዋል:: የዚህ ተቃራኒው ያለመታዘዝ ውጤት ደግሞ መርገም ነው::

አንድ በጣም ልቤን የሚነካው ፀሎት አለ....... መፀሐፍ ቅዱስ ውስጥ....... "እባክህ፤ መባረክን ባርከኝ፤ አገሬንም አስፋው፤ እጅህም ከእኔ ጋር ትሁን....... እንዳያሳዝነኝም ከክፋት ጠብቀኝ" የሚል ፀሎት ነው (1ኛ ዜና 4፡9-10):: ይህንን ፀሎት የፀለየው ያቤፅ የሚባል ሰው ነው:: የያቤፅ የስሙ ትርጉም 'ህምም' ወይም 'Pain' ማለት ነው:: ስለዚህ ያቤፅ በዘመኑ የኖረው "ህመም ! አስቲ አንዴ ና" እየተባለ ነው:: ታዲያ በህይወቱ አንድ ምዕራፍ ላይ ሲደርስ ከልቡ ሆኖ ይህንን ፀሎት ፀለየ...... "አቤቱ መባረክን ባርከኝ!.....

አገሬንም አስፋው!...." እግዚአብሔርም ሰማው፡፡ የለመነውንም ሁሉ ሰጠው፡፡

'የእግዚአብሔር በረከት' ማለት ሀብታም መሆን ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ፀፀትና ሀዘን የማይገኝበት ማጣት የሌለበት ኑሮ ነው፡፡ ብዙ ሚሊየነሮች ኑሮ እያስጠላቸው ራሳቸውን አጥፍተዋል፡፡ ሀብቱ ነበራቸው...... በረከቱ ግን አልነበራቸውም፡፡ ብልፅግናና ሀብት ብቻውን ደስታን አያመጣም፡፡ በሰው ህይወት የእግዚአብሔር በረከት ሲኖርበት ግን ሰላሙ እንደ ወንዝ የሚፈስ ደስታው የሚፍለቀለቅ ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የእግዚአብሔር በረከት ብልፅግናን ማምጣቱ አይቀርም፡፡

አንዳንድ ቤት ገብቻለሁ፡፡ በተሸራረፈ ብርጭቆ ሻይ ይቀርብልኛል፡፡ በላስቲክ ሰሀን ደግሞ ዳቦ ተቆራርሶ ይሰጠኛል፡፡ አቤት ሻይው ሲጣፍጥ!.... አቤት ዳቦው ሲጥም!፡፡ ግን የተለየ ሻይ ነው? አይደለም! ፡፡ ዳቦውስ የተለየ ነው? አይደለም!፡፡ ነገር ግን እዛ ቤት ውስጥ የእግዚአብሔር በረከት ሰላለ ነው!...... ውጡ ውጡ አይልም፡፡ ሌላ አይነት ቤት ደግሞ ገብቻለሁ፡፡ ገበታው ተትረፍርፎ የተዘጋጀበት!....... ምንጣፉ ለመርገጥ የሚያሳሳበት..... ሶፋው ምቹ ሆኖ የሚያንሳፍፍበት !......... እዛ ቤት ውስጥ ግን መቆየት አይቻልም!........ ሞት ሞት ይሸታል!....... አምልጥ አምልጥ ይላል!፤ ያ ቤት ደግሞ የእግዚአብሔር በረከት የሌለበት ቤት ነው፡፡

በረከት ከብልፅግና ጋ ግኑኝነት የለውም ማለት ግን አይደለም፡፡ እንደውም የእግዚአብሔር በረከት ባለፀጋ ማድረጉ የማይቀር ነው፡፡ ከብልፅግናው ጋ ግን ሀዘንን ይዞ አይመጣም፡፡ በችኮላ አይከማችም...... በፍጥነትም አይበተንም፡፡ ተድላ አለበት!........ ሰላምና ደስታ አለበት!፡፡

የእግዚአብሔር በረከት ታዲያ በቀላሉ አይገኝም፡፡ የሚገኘው በመታዘዝ ነው!፡፡ ለእግዚአብሔር 'እሺ' በማለት!፡፡ የእርሱን በረከት ከፈለግን አመፃን ሁሉ ከቤታችን...... ከስራችንም ማራቅ አለብን፡፡ ህሊናችን "እባከህ ተው" የሚለንን ነገር መተው አለብን፡፡ ወደንና ፈቅደን የአምላካችንን ፈቃድ ካደረግን፤ ከታዘዝን..... የእግዚአብሔር በረከት በክርስቶስ ኢየሱስ የእኛ ናት፡፡

## የጥበብ እንቁ 34

## አነጋጋሪ መሆንን አለመፍራት !

በምድር ኖረው ካለፉ ሰዎች መሀል እጅግ አከራካሪ ከሆኑት ውስጥ ቅድስት ማርያም አንዷ ናት፡፡ ስምዋ በአንድ ስፍራ ከተነሳ ትንሽ ቆይቶ ክርክር መነሳቱ አይቀርም፡፡ "ታማልዳለች!"...... "አይ! አታማልድም!" ...... "ከሀጢያት ነፃ ሆና ነው የተወለደችው!"........ "የለም! እንደ ማንኛውም ሰው የአዳምን ሀጢያትን ተካፍላለች"....... "በአክብሮት ሊሰገድላት ይገባል!"...... "አይ! ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው!" ክርክሩ ይቀጥላል፡፡ ማብቅያም የለውም!፡፡ በታላላቅ የክርስትና እምነት ተቋማት መሀል ካሉ ዋነኛ ልዩቶች መሀል ስለ ቅድስት ማርያም ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ ቅድስት ማርያም እጅግ አነጋጋሪ...... አከራካሪም ናት!፡፡

አከራካሪ (Controversial) መሆን የታላላቅ ሰዎች መለያ ነው፡፡ ማንነታቸው፣ ስራቸው፣ ሌጋሲያቸው ሁሉ ያከራክራል፡፡ ሰው አነጋጋሪ መሆንን ካልፈለገ በህብረተሰቡ ዘንድ ልቆ ከመውጣት መቆጠብ አለበት፡፡ ልቆ ከወጣና በህዝብ እይታ ውስጥ ከገባ ግን አነጋጋሪ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡ ሰዎች ስለ እርሱ ሲነጋገሩ....... ሲከራከሩ ታዲያ የተለያየ አቋም ይዘው ነው፡፡ በአንድነት ሁሉም ሰው የሚያጨበጭብለት ሰው አይገኝም፡፡ ቢጨበጨብለት እንኳን ትንሽ ቆይቶ ማከራከሩ አይቀርም፡፡ አንዳንዴ እንደውም ክርክሩ ከበዛ አንዱ ቡድን ሰውዬውን ሚካኤል ሲያደርገው ሌላው ደግሞ ሳጥናኤል ያደርገዋል፡፡

ሰዎች ስለ ታዋቂ ሰዎች ማውራትን ይወዳሉ፡፡ በየ ካፌው፣ በየ ቤቱ፣ በየ ምግብ ቤቱ....... ሰዎች የሚጫወቱትን ካዳመጥን አብዛኛው ስለ ሌሎች ሰዎች እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ልቀው ከወጡ በየቦታው...... የመነጋገርያ ርዕስ የዝምታ መስበርያ...... መሆንዎ አይቀርም፡፡ ወሬ ከጠፋ..... ምን ይደረግ .........ሰዎች ስለ እርሶ መነጋገር ይጀምራሉ፡፡ ታዲያ ሁሉም ሰው እያደነቁት እንዲናገር አይጠብቁ!፣ እንደዛ ያለ ነገር የለም!፣ ጌታ ኢየሱስ ራሱ ሰዎች ሁሉ መልካምን ሊናገሩልን እንደማይችሉ ነግሮናል፡፡

በእኛ እድሜ አሜሪካንን ከመሩ ፕሬዚደንቶች መካከል ጆርጅ ቡሽ ይገኙበታል፡፡ እርሳቸው 43ኛው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ናቸው፡፡ እኚህ ሰው የአፍሪካ በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ ባለ ትልቅ ውለታ ናቸው፡፡ እንዴት ማለት ጥሩ ነው? ፤ የ ኤች አይ ቪ ኤድስ (HIV/AIDS) ችግር አህጉራችንን ሲያናውጥ በነበረበት ዘመን ድንገት የህይወት ማራዘምያ መድሀኒት የመገኘቱ ወሬ ተሰማ፡፡ እነዚህ መድሀኒቶች ይመረቱ እንጂ ዋጋቸው ግን ለአፍሪካ የማይሞከር ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ለአፍሪካ........ ኢትዮጵያን ጨምሮ..... መድሀኒት በነፃ እንዲቀርብ ገንዘብ (Fund) ያዘጋጁልን ጆርጅ ቡሽ ነበሩ፡፡ PEPFAR ይባላል...... ፈንዱ፡፡ በዚህም ፈንድ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካውያን ከሞት ተርፈዋል፡፡ ጆርጅ ቡሽ በእውነት ባለ ውለታችን ናቸው!፡፡

እኚህ ባለ ውለታችን ታዲያ ስማቸው ሲነሳ ወዲያው ተከትሎ ከፍተኛ ክርክር ይነሳል፡፡ ይህም የኢራቅን ጦርነት በመምራታቸው...... ጦርነቱን ለማካሔድ የወጣው ወጪ...... እንዲሁም የተከተለው የኢኮኖሚ ውድቀት.... ሀላፊነቱ በሙሉ በእርሳቸው ላይ ተጥሎ መነጋገርያ ያደርጋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ "አሜሪካንን ገጥሟት የነበረውን የሽብርተኝነት አደጋ በሚገባ ቀልብሰዋል! መቆጣጠር ችለዋል!" ብለው የሚያደንቋቸው ሰዎች አሉ፡፡ ጆርጅ ቡሽ ያከራክራሉ!፡፡

እርሶ በህብረተሰብ መሀል እየላቁ ከመጡና አነጋጋሪ ሰው ከሆኑ "ለምን ስሜ በከፉ ተነሳ!" ብሎ መበሳጨትን ይተው፡፡ ይህ ዝና ይዞት የሚመጣ....... ሲሆን ግድ የሆነ ነገር ነው፡፡ በታማኝነት በጎ መስራቶን ይቀጥሉ!፤ ጥሩ ማድረጎን ሲቀጥሉ የክርክሩ ሚዛን ወደ በጎው ያደላሎታል፤ መልካም ስምንም እግዚአብሔር ይሰጦታል፡፡

በቅርቡ አንድ ጋዜጣ ላይ ያነበብኩት ታሪክ ትዝ አለኝ፡፡ አንድ ንጉስ "እኔ ብሸጥ ስንት አወጣለሁ" ብለው ጠቢባንን ጠየቁ፡፡ የሚመልስ ጠፋ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ የቆሎ ተማሪ እኔ መልሱን አውቃለሁ አለ፡፡ በንጉሱም ፊት ሲያቀርቡት ለንጉሱ "እርሶ 25 ብር ነው የሚያወጡት!" አላቸው፡፡ "እንዴት አንተ!?" ብለው ቢጠይቁት "ጌታ ኢየሱስ በ 30 ብር ነው የተሸጠው! እርሶ ደግሞ ከኢየሱስ አይበልጡም!" አላቸው ይላል፡፡ እርሶም ከኢየሱስ አይበልጡምና "ለምን ስሜ ተነሳ" ብለው አይበሳጩ!፡፡

## የጥበብ እንቁ 35

## ለተቃዋሚዎች መልስ አለመስጠት !

"ይሄ ሰው በአጋንንት አለቃ በብኤልዜቡል አጋንንትን ያስወጣል!"............ "ከህጢያተኞች ፣ከቀራጮችና ከጋለሞታዎች ጋ ይውላል!"..........."ክርስቶስ ሳይሆን ራሱን ክርስቶስ ነኝ ይላል!"...... "አብዷል!"........ "ጋኔል አለበት!" ....... "እንዴት ደሜን ጠጡ ስጋዬን ብሉ ይላል!"...... "ራሱን ከፍ እያደረገ ከአብርሀም በፊት ነበርኩ ይላል......" ፡፡ እነዚህ ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስ ተቃዋሚዎች በጌታ ላይ የሚያነሱት ተቃውሞ ነበር፡፡ ይሄው ተቃውሞ ወደ ቅድስት ማርያም ፊት መምጣቱ አይቀርም..... በስጋ ወልዳዋለችና፡፡ ደስ የሚለው ግን ኢየሱስም ሆነ ማርያም ለተቃዎሚዎቹ........ ለተሳዳቢዎቹ....... መልስ አይሰጡም ነበር፡፡

የተለያዩ ሚዲያዎች የህዝብ አገልጋዮች ናቸው፡፡ እንደ መረጃ ምንጭነታቸው ለህዝብ የሚያቀርቡትን መረጃ ይፈልጋሉ፡፡ መረጃ ማግኘትም አለባቸው!፡፡ በሚዲያዎች ላይ ለመቅረብ እድል ማግኘት መልካም ነው፡፡ እድሉ የተሰጠው ሰው ራሱን ግልፅ ለማድረግ፣ ያለበትን ሁኔታ ለማስረዳት፣ የወደ ፊት ራዕይውን ለማስተዋወቅ፣ አጥፍቶ ከሆነም ህዝብን ይቅርታ ለመጠየቅ፣ የተወራበትን ሀሰተኛ ወሬ ለማስተባበል መድረኩን ይጠቀምበታል፡፡ በምዕራቡ አለም እንደውም ታዋቂ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚያስረዱት ነገር ሲኖራቸው ራሳቸው ጋዜጠኞችን ጠርተው ፕሬስ ኮንፈረንስ (Press Conference) ይሰጣሉ፡፡ አጋጣሚውንም በደንብ ይጠቀሙበታል፡፡ ታዋቂ ሰዎች እውነትን ፍለጋ የሚቀርቡአቸውን ጋዜጠኞች ከሽሹ አላስፈላጊ ዋጋ ነው የሚከፍሉት፡፡ ማስረዳት ያለባቸውን ነገር ማስረዳት አለባቸው፡፡ ጋዜጠኞችንም እንደ ባለሙያ ማክበር ይገባል፡፡

ከዚህ በተለየ ግን አንዳንድ ሰዎች በድፍን ጥላቻ የሚነሱበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ፍላጎታቸው ያ የጠሉት ሰው ከምድረ ገፅ እንዲጠፋላቸው ነው እንጂ ማብራርያ ሰጥቶ ራሱን ግልፅ እንዲያደርግ አይደለም፡፡ ስለዚህ

ጠምደው የያዙትን ሰው አጥብቀው ይቃወሙታል...... ይሰድቡታል:: መግለጫ ቢሰጥ፣ ይቅርታ ቢጠይቅ፣ ቢያብራራ አይቀበሉትም:: ምክንያቱም መነሻቸው ቅንአትና ጥላቻ ስለሆነ ነው:: ለእንደነዚህ አይነት ሰዎች መልስ መስጠት ፈፅሞ አያስፈልግም:: መልስ በመስጠት የሚመጣ ሰላምም የለም::

በአሜሪካ ካሉ ታላላቅ የቴሌቪዥን ኔትወርኮች መሀል CNN እና Fox News ይገኙበታል:: CNN የአሁኑን የአሜሪካንን ፕሬዚደንት ባራክ ኦባማን ይደግፋቸዋል:: በተለይ በቅርቡ ጡረታ የወጡት ላሪ ኪንግ (Lary King) የተባሉት ጋዜጠኛ የባራክ ኦባማ አድናቂ ነበሩ ማለት ይቻላል:: በተቃራኒው የፎክስ ኒውስ በአብዛኛው ኦባማን ይቃወም ነበር:: በተለይም አንዱ ጋዜጠኛ የግል ጠብ ያለው ነበር የሚመስለው:: ኦባማ ለዚህ ሰው መልስ መስጠት አይፈልጉም ነበር:: መልስ መስጠት ከጀመሩ ግን ነገሩ የጠላ ቤት ሴቶች የሚጣሉትን ጠብ አይነት ይሆናል........ መጨረሻ የሌለው መሰዳደብ!::

በየትኛውም ሀላፊነት ላይ ስንቀመጥ መረጃ ለመስጠት፣ ጥያቄን ለመቀበል፣ ማስረዳት ያለብንን ለማስረዳት ቢሮአችንን ክፍት ማድረግ አለብን::ጋዜጠኞች ባለሙያዎች፣ የህዝብ አገልጋዮች ናቸው:: ከዚያ ውጪ ግን ማስተዋል ያለብን ነገር ቢኖር በምድር ስንኖር ያለ ምክንያት የሚጠሉን ሰዎች መኖራቸው የማይቀር መሆኑን ነው:: እነዚህ ሰዎች ምንም መልካም ብናደርግ...... አግኝተን ብናናግራቸው....... ብናባብላቸው....... ብንለምናቸው..... ፈፅሞ ሀሳባቸውን አይቀይሩም:: መፍትሔው ታዲያ ይሄ ነው...... መልስ አለመስጠት!፤ ፈፅሞ ፈቃደኛ አለመሆን!:: ብለው ብለው ማቆማቸው አይቀርምና እነርሱን ትቶ ስራን መስራት ነው የሚሻለው::

## የጥበብ እንቁ 36

## መልካም ስብዕናን መጠበቅ !

የቅድስት ማርያም ስብዕና (Personality) ሲጠና አንዳችም የተቃወሰ ነገር አይገኝባትም። አጅግ መልካም የሆነ ስብዕና፣ ምሳሌ የሚሆን ማንነት ነበራት። እስካሁን በነበሩት ክፍሎች ሁሉ ያየነው ይህንን ነው። እንደ ምሳሌ እርሷን የመውሰዳችንም ምክንያት ይሄው ነው።

ስብዕና ወይም ፐርሰናሊቲ የብዙ ነገሮች ድምር ነው። እውቀታችን፣ ስሜታችን፣ አስተሳሰባችን፣ ባህሪያችን ተደምረው ፐርሰናሊቲያችንን ይሰራሉ። ያም ፐርሰናሊቲ መለያችን ይሆናል።በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ስናልፍ የመጡብንን ነገሮች የምንይዝበት መንገድ የፐርሰናሊቲያችን ማሳያ ነው። ካራክተር (Character) የሚባለው ደግሞ የፐርሰናሊቲያችን አንኳሩ ነው።

በሰዎች ዘንድ የሚታዩ የተለያዩ የተቃወሱ የስብዕና አይነቶች (Personality Disorders) አሉ። ከነዚህ አንዱ 'አንቲ ሶሻል ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር' (Antisocial Personality Disorder) ይባላል። ይህ ችግር ያለባቸው ሰዎች የህብረተሰብ ጠር ናቸው። ማፍረስ ደስ ይላቸዋል!፤ በወጣትነታቸው እቃ ከቤት እያወጡ ይሸጣሉ!፤ የጎረቤት እቃን ይሰርቃሉ!፤ ስፖኪዮ ይፈነቅላሉ!፤ የሚያስደስታቸው ነገር ማጥፋት ነው!። ሰዎችን መሳደብ.... መደባደብ... መፈንከት ይወዳሉ!፤ ጠብ መሀል በተደጋጋሚ ይገኛሉ!። ትልቅ ሰውም ከሆኑ በኋላ የማበላሸት..... የማፍረስ ስራቸውን አይተውም። አንድ ማህበር ውስጥ ከገቡ ይበጠብጡታል!..... ከቻሉም ይበትኑታል!።

ሁለተኛው የተቃወሰ ስብዕና አይነት 'ናርሲስቲክ ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር (Narcisstic Personality Disorder) ይባላል:: እነዚህ የሚታወቁት ከመጠን ያለፈ ራሳቸውን በመውዳደቸው ነው:: በእነርሱ አይን እንደነርሱ ቆንጆ የለም!፤ መስታወት ፊት ቆመው ብዙ ጊዜ ያሳልፋሉ:: ሀሳባቸው ሁሉ በራሳቸው ላይ ነው:: ናርሲስቲክ የሚለው ቃል ራሱ የመጣው መስታዎት ባልነበረበት ቦታ በውሀ ውስጥ ፊቱን ማየት ይወድ በነበረና በውሀው ውስጥ ሰጥሞ በሞተ በግሪክ አፈ ታሪክ ውስጥ በሚገኝ አንድ ሰው ስም ነው::

ሶስተኛው የተቃወሰ የስብዕና አይነት 'ሒስትሪዮኒክ ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር' (Histrionic Personality Disorder) ይባላል:: እነዚህ ደግሞ በጣም ይሽቀረቀራሉ:: በሰው መሀል ከተገኙ እነርሱ ብቻ ማውራት አለባቸው:: ለሌላ ሰው ተራ አይሰጡም:: በአንድ ስፍራ ሲቀመጡ የሰዎች ሁሉ ቀልብ (Attention) በእነርሱ ላይ እንዲሆን ይፈልጋሉ:: መታየት ደስ ይላቸዋል!፤ ሰዎች ሁሉ በተለየ መንገድ እንዲፈልጓቸው የሚያደርግ አኳኋንና የአነጋጋር ዘይቤ አላቸው::

አራተኛዎቹ ደግሞ 'ኦብሰሲቭ ኮምፐልሲቭ ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር' (Obsessive Compulsive Personality Disorder) ያላቸው ናቸው:: እነዚህ ደግሞ አንድ አይነት ያለማቋረጥ አእምሮአቸውን የሚይዝባቸው ሀሳብ ይኖራቸዋል..... ለምሳሌ 'አለመቆሸሻ' ይሆናል:: ይህ ኦብሴሽን (Obsession) የሚባለው ነው:: ይህ አይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች ቆሻሻ ከመፍራታቸው የተነሳ ሰው ለመጨበጥ እንኳን ይፈራሉ:: እጃቸውን ደጋግመው ይታጠባሉ:: የታጠበ ብርጭቆ ሲቀርብላቸው ተነስተው ደግመው ያጥቡታል:: ይህ ድርጊታቸው ደግሞ ኮምፐልሽን (Compulsion) ይባላል:: ምግብ ቤት ሲገቡ ሁሉ ምግቡ ስለተሰራበት ንፅህና ይጠራጠራሉ:: ራሳቸው ይሰቃያሉ........ ሳያውቁት ሌሎችንም ያሰቃያሉ::

አምስተኛዎቹ ደግሞ ስኪዞይድ ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር (Schizoid Personality Disorder) ያላቸው ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ብዙ ጊዜ ብቻቸውን ማሳለፍ ይወዳሉ:: ከሰው ጋ መቀላቀል ያስፈራቸዋል!......

ይጨንቃቸዋል! ስለዚህም ብዙውን ጊዜ ጓደኛ አይኖራቸውም:: ቢያሞግሷቸውም ቢያጣጥሏቸውም ምንም ስሜት አይሰማቸውም::

ስድስተኛው የፐርሰናሊቲ ቀውስ ደግሞ ዲፔንደንት ፐርሰናሊቲ ዲስኦርደር (Dependent Personality Disorder) ይባላል:: ይህ ችግር ያለባቸው ሰዎች ያለ ሰው መኖር አይችሉም:: በራሳቸው ውሳኔን ማሳለፍ ይቸግራቸዋል:: ለእያንዳንዱ ነገር ሰውን ማማከር አለባቸው:: በሌሎች ሰዎች ላይ ሲበዛ ጥገኛ ናቸው::

ያነሳኋቸው የስብዕና መቃወስ አይነቶች የተወሰኑትን ነው:: ሌሎችም አሉ:: እነዚህ ቀውሶች የሚታዩበት ሰው ሳይኮሎጂስቶችን ወይም ሳይካትሪስቶችን ማማከር ይኖርበታል:: በእኛ አገር የምክር አገልግሎትን (Counseling) ማግኘት ብዙ አልተለመደም:: የአዕምሮ ሐኪሞችንም በስህተት "የእብድ ሐኪሞች" አድርገን እንወስዳቸዋለን:: በሰለጠነው አለም ግን ካውንስሊንግ ለጤነኞቹም ሰዎች ሁሉ አስፈላጊ እንደሆነ ይታመናል:: ምንም ሳይሆኑ ራሳቸውን ለማየት አማካሪዎቻቸው ጋ ይሔዳሉ::

እርሶ ግን ስብዕናዎን ትክክለኛ በሆነ..... ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ ማስተካከልና መጠበቅ ይኖርቦታል:: ፐርሰናሊቲ.... የሚስተካከል.... የሚያድግ ... የበለጠ ተወዳጅ እየሆነ መምጣት የሚችል ነገር ነው:: ትልቅ ቦታ ላይ ለመድረስና እዛው ለመቆየት ደግሞ ፐርሰናሊቲ....... ካራክተር ወሳኝ ነው::

# የጥበብ እንቁ 37

## ወደ ብስለት (Maturity) መድረስ !

ቅድስት ማርያም ጌታን የፀነሰችበት እድሜ የወጣትነት ጊዜዋ ነበር:: በእርሷ እድሜ ያሉ ሴቶች ገና ተጫውተው ያልጠገቡ ናቸው:: ማርያም ግን ያሳየችው ብስለት (Maturity) ፈፅሞ ከእድሜዋ በላይ ነበር:: እንዴት አንዲት ወጣት ያንን ታላቅ አደራ ተቀበለችው? እንዴትስ ተወጣችው? ለእርሷ ብስለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆኖላት ነበር!::

ብስለትን እግዚአብሔር ይፈልገዋል:: የሚያበስልም እርሱ ነው:: እስራኤላውያን ከግብፅ የወጡበትን ቀን ሲያከብሩ በየ ቤቱ ጠቦት ይታረድ ነበር:: ስጋውንም በእሳት ይጠብሱታል (ዘፀ 12:8-10):: እግዚአብሔር እንዲጠብሱት ነው ያዘዛቸው!:: ጥሬውን እንዳትበሉ!...... የተቀቀለውንም እንዳትበሉ!..... በእሳት የተጠበሰውን ብሉት!....... ብሎ አዟቸው ነበር:: የተጠበሰውንም ስጋ ከመራራ ቅጠል ጋ እንዲበሉት አዟቸዋል:: ጥሬው ያው ጥሬ ነውና አልበሰለም:: ቅቅሉ ደግሞ ተመችቶት ነው የወጣው...... በሞቀ ውሀ ውስጥ ነው ሲንከባለል የሰነበተው:: በእሳት የተጠበሰው ግን በደንብ በስሏል:: የእሳቱ ሀይል በሚገባ አግኝቶታል::

ሰዎችን የሚያበስላቸው የሚያልፉበት እሳት እንጂ በዩኒቨርሲቲ የተማሩት ትምህርት አይደለም:: የሚታለፍበት የህይወት እሳት አለ!.... እርሱ ደህና አድርጎ ያበስላል:: ባለሙያ ሴት የከተፈችውን ስጋ የጋለ መጥበሻ ላይ ታስቀምጠዋለች:: ከዚያም ስጋው በትክክል እንዲበስል ገልበጥ...... ገልበጥ እያደረገች እሳቱ ሁለንተናውን እንዲያገኘው ታደርገዋለች:: እኛንም ወደ ብስለት የሚያመጣን የህይወት ምድጃ..... መጥበሻ ነው:: በትክክልም እንድንበስል በህይወታችን የተለያዩ አቅጣጫዎች እሳቱ ያልፍብናል:: በመስሪያ ቤት....... ገልበጥ ሲል ደግሞ በቤት...... ደግሞ ገልበጥ ሲል

በጎረቤት...... በጤንነት ጉድለት......... በማጣት..... በተለያየ መንገድ እሳቱ ይመጣል፤ ያበስለንማል!::

ታዲያ መብሰል አለመብሰላችን የሚታወቀው ሰዎች ሲነኩን........ ሲተናኮሉን ነው:: ጥብሱን እያዘጋጀች ያለች ሴት ስጋው በደንብ መብሰሉን የምታረጋግጥበት መንገድ አለ:: በያዘችው ሹካ ወጋ ወጋ ታደርገዋለች!፤ ካልበሰለ እሳቱን ጨመር ማድረግ አለባት:: እኛም መብሰል አለመብሰላችን የሚታወቀው ሹካ ይዘው በሚዞሩ ሰዎች ነው:: ወጋ!....... ወጋ! ያደርጉናል....... ይተናኮሉናል:: ሲወጉን ከተናደድንና ከጮህን ገና ይቀረናል ማለት ነው:: እሳቱም ይቀጥላል!:: ሲወጉን ግን ዝም ማለት ስንጀምር ያን ጊዜ ወደ ብስለት ደርሰናል...... እግዚአብሔር የሚፈልገን ቦታ!::

ማንም ባለሙያ ሴት ስጋው ከበሰለ በኋላ ስጋውን አታሳርረውም፤ ታወጣዋለች እንጂ!:: አውጥታ ውብ ሸክላ ሰሀን ላይ ታስቀምጠዋለች ........ከአትክልት ጋ አሳምራ ታቀርበዋለች:: እግዚአብሔር አምላካችንም ያበስለናል እንጂ አያሳርረንም:: ለዚህ ነው ቃሉ "ትታገሱም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል" የሚለው (1ኛ ቆሮ 10:13):: መውጫ (Exit) አለው ማለት ነው!:: ከወጣንም በኋላ የምንቀመጥበት ቦታ ውብ ነው:: ታዲያ እንደዚያ አምሮ ስጋው ሲቀርብ ኩሽና ያየውን መከራ ማንም እንደማያስበው ሁሉ እኛም በመከራ በስለን ስንወጣ ከመዋባችን የተነሳ ስለ መከራ ሰምተን እንኳን የምናውቅ አንመስልም:: ያበሰለን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን::

ብስለት በንግግራችን...... በአኗኗራችን..... በህይወታችን የሚታይ ውብት ነው:: በጣም የተማሩ ግን ከእህት ወንድሞቻቸው ጋ ለአምስት ደቂቃ በሰላም ማውራት የማይችሉ ሰዎችን አይተው ያውቃሉ?፤ ወይስ በጣም የተማሩ ግን በየደቂቃው ግንፍል ግንፍል የሚሉ ሰዎችስ?፤ የተማሩ ሆነው እንዴት እንዲህ ይሆናሉ ብለው ተገርመዋል?፤ አዎ! ሰዎቹ ተምረዋል..... ነገር ግን አልበሰሉም!..... የህይወት እሳት አልነካቸውም::

የሰው አዋቂነት ሶስት ዋና ዋና አይቶች አሉት ነው:: አንዱ 'ኮንቬንሽናል ኢንተሊጀንሲ' (Conventional Intelligency) ይባላል::

የዚህ አይነቱ ኢንተሊጀንሲ ከትምህርት ቤት ከምናገኘው ትምህርት ጋ ይገናኛል:: በማንበብም ይጨምራል:: ደራጃው የአንዳችን ከሌላችን ይለያያል:: በምዕራፍ 13 ላይ የዘረዘርናቸው ኢንተሊጀንሲዎች በሙሉ በዚህኛው ስር ይጠቃለላሉ::

ሁለተኛው ደግሞ ሶሻል ኢንተሊጀንሲ (Social Intelligency) ይባላል:: ይህ ደግሞ በህብረተሰብ ውስጥ በመግባባት የመኖር ችሎታችንን ያመለከታል:: አንድ ሰው በቀለም አውቀቱ ትልቅ ሆኖ ከህብረተሰብ ጋ የመኖር ችሎታው ግን የወረደ ከሆነ 'ዝቅተኛ ሶሻል ኢንተሊጀንሲ' አለው ማለት ነው::

ሶስተኛው አዋቂነት ኢሞሽናል ኢንተሊጀንሲ (Emotional Intelligency) ይባላል:: ይህ ደግሞ የአንድ ሰው ስሜቱን የመቆጣጠር ችሎታው ነው:: ሲያዝን ፣ ሲቆጣ ፣ ሲደሰት የሚያደርጋቸውን ሁኔታዎች ያመለከታል:: በትምህርት ቤት እውቀቱ ትልቅ ሆኖ ሲናደድ ግን ሚስቱ ላይ ብርጭቆ የሚወረውር ሰው ይኖራል!:: በመስሪያ ቤት ፀሀፊውም ላይ በቀን ሶስት አራቴ ይባርቃል!:: በጓደኞቹ ላይ ይነጫነጫል:: ታዲያ ይህ ሰው ምንም እንኳን የተማረ ሰው ቢሆንም 'ኢሞሽናል ኢንተሊጀንሲው' ግን በጣም ዝቅተኛ ነው::

በእውነት አዋቂዎች ከሆንን በሶስቱም መላቅ አለብን:: የበሰሉ ሰዎች በትውልድ መሀል የተከበሩ ይሆናሉ!፤ የብዙዎች መካሪ ለመሆን ይበቃሉ!፤ የተማሩ ሆነው ሲገነፍሉ የሚውሉ ከሆነ ግን አስቸጋሪ ይሆናል:: እግዚአብሔር ሁለንተናዊ እውቀትና ብስለትን ይስጠን::

# የጥበብ እንቁ ፴፰

## ለዘላለም ህይወት ማሰብ !

ቅድስት ማርያም በዚህ በምድር የምንኖረው ኑሮ በጣም አጭር እንደሆነ ተረድታለች፡፡ የምታስበው ስለ ዘላለማዊው ህይወት ነበር፡፡ በምድር የኖረችው ለአስርተ አመታት ነው፡፡ ወደ መንግስተ ሰማይ ሄዳ ኑሮዋን በዚያ ካደረገች ግን ይሄው ሁለት ሺ አመት ሊሞላት 50 አመት ቢቀረው ነው፤ ወደ ዘላለም እረፍቷ ገብታለች፤ ገናም ለዘለአለም ትኖራለች!....... የእግዚአብሔርን መንግስት ወርሳለችና!፡፡

አንድ በቅርቡ ወደ ዘላለም ቤቱ የሔደ ወዳጅ ነበረኝ፡፡ ቸርነት መኮንን የሚባል የቅርብ ወዳጄ ነው፡፡ በጣም ነበር የምወደው!፤ አንባቢም ስለሆነ ወሬው ደስ ይለኛል፡፡ የሚኖረው አንድ ክፍል ውስጥ ነበር፤...... አንድ አልጋ..... አንድ ጠረጴዛ...... ሁለት ወንበሮች....... እንዲሁም አንዲት ትንሽ ቴሌቪዥን ነበረችው፡፡ ያለው ሀብት መፃህፍቶቹ ብቻ ነበሩ፡፡ ብሔራዊ ቲያትር አካባቢ አይጠፋም........ የቅዳሜ ጋዜጦችን ገዝቶ ማንበብ ይወዳል፡፡ ለእኔም ገዝቶ ያመጣልኛል፡፡ ካፌ ሲገባ “ሻይ አምጪልኝ.... በሎሚ...... ያለቀለት” ይል ነበር፡፡ በጣም ጥሩ ሰው ነበር ቸሬ!፡፡ ታዲያ ወዳጄ ቸርነት አስም ያስቸግረው ነበር፡፡ ሲያመው ይደውልልኛል....... መርፌ ይወጋል...... ይሻለዋል፡፡ አንድ ቀን ግን አስሙ በረታበት፤ እኔ ደግሞ በፕሮግራም ምክንያት አልነበርኩም፤ ስለዚህም የቤተ-ክርስትያን ወዳጆቹ ጥቁር አንበሳ ወሰዱት፡፡ በህኪሞች ብዙ ጥረት ቢደረግም ቸሬ የልብም ችግር ስለነበረው አልሆነም፤ የቸሬ የምድር ጉዞ የዛን ቀን አበቃ!፡፡

“ቸሬ ሞተ!” ብለው ሲነግሩኝ ማመን ስላልቻልኩ ጥቁር አንበሳ ሔጄ አስከሬን ወደሚቀመጥበት ክፍል አስፈቅጄ ገባሁ፡፡ አየሁት ቸሬን!..... በጀርባው ተኝቷል!..... ፀጥ ብሎ ተኝቷል!፤ ለብዙ ደቂቃዎች ቆሜ ተመለከትኩት...... አሰብኩኝ!..... “በቃ ማለት ነው?” አልኩኝ፤ ትንሽ ቆይቼ

ግን ሳስበው እዛ ጋ የተኛው ቸሬ እንዳልሆነ ገባኝ፡፡ እርሱ ከምድር አካሉ ወጥቶ ወደ አምላኩ መንግስት ሔዷል፡፡ እዛ ጋ የተጋደመው ቸሬ ይኖርበት የነበረው ከአፈር የተሰራው ወደ አፈር የሚመለሰው የምድር አካሉ ነው፤ ተገላግሎት ሔዷል!፡፡

ቸሬን አሰብኩት!፤ ቸሬ ወደ ሌላ አለም ሐዷል!፤ ጌታ ኢየሱስ በዙፋኑ ላይ ወደ ተቀመጠበት...... እነ አብርሀም...... ይስሀቅ..... ያዕቆብ...... ሙሴ...... ኤልያስ....... ዳዊት ሌሎችም ነብያት ወደ ተሰበሰቡበት ደግሞም እነ ጳውሎስ....... ጴጥሮስ........ ዮህንስ........ ማቲዎስ ሌሎቹም ሐዋርያት ወደ ተከማቹበት....... ደግሞም ቅድስት ማርያም........ መግደላዊት ማርያም...... ዮሃና...... ሶስና....... ሌሎቹም የእምነት እናቶች ወዳሉበት የሰላም ሀገር ተቀላቅሏል፡፡ "ቸሬ ታድሎ!" አልኩኝ በሀሳቤ፡፡ ቸሬን አሰብኩት!፤ በጣም ተጨዋች ስለነበረ "አቤት አሁን እነ ሙሴን በወሬ ልባቸውን ውልቅ ያደርጋቸው ይሆን?" ብዬ አሰብኩ........ ከአስከሬን ክፍሉም ወጣሁ!፡፡

መልመድ የሚያስቸግረን ነገር ቢኖር ሞት ነው፡፡ የቅርብ ሰዋችንን ስናጣ እንደነግጣለን፡፡ ይህ 'የድንጋጤ የምዕራፍ' (shock stage) ይባላል፡፡ ከዚያም "አይ በፍፁም አልሞትም! አይሆንም!" እንላለን፡፡ ይህ ደግሞ 'የሆነውን የመካድ ወይም ለመቀበል እምቢ የማለት ምዕራፍ' (Denial stage) ይባላል፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍ 'እንግዲህ እግዚአብሔር ከፈቀደ ምን ይደረጋል' ማለት እንጀምራለን፡፡ ይሄኛው ደግሞ 'የመደራደር ምዕራፍ' (Bargain stage) ይባላል፡፡ ከዚያም ጥልቅ ሀዘን ውስጥ እንገባለን፡፡ እርሱ ደግሞ 'የሀዘን ምዕራፍ' (Depression stage) ተብሎ ይጠራል፡፡ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ስንደርስ የሆነውን ነገር ተስማምተን እንቀበለዋለን፡፡ ይህ የመጨረሻ የሆነው 'የመስማማት ምዕራፍ' ነው (Acceptance stage)፡፡ እነዚህ አምስቱ ሀዘን የገጠመው ሰው የሚያልፍባቸው ምዕራፎች (Mourning stages) ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ እንግዲህ ቀስ በቀስ ይረሳል፡፡

የምድር ኑሮ እንዴት አጭር ነው!፤ ኮሪደር ነው የሚመስለኝ!፡፡ ሁላችንም በተራችን እንሞታለን፤ እኔም እሞታለሁ!፤ ከሞት በኋላ ያለው ነገር ነው የሚያሳስበው፡፡ ህንድ አካባቢ የሞተው ሰው ነፍስ ተመልሶ በምድር

ይኖራል ብለው ያምናሉ፡፡ 'ሪኢንካርኔሽን' (Reincarnation) ይሉታል!፡፡ የሞተው ሰው ጥሩ ሰው ከነበረ ሌላ ጥሩ ሰው ሆኖ ይመጣል!...... ክፉ ሰው ከነበረ ደግሞ አይጥ ወይም ሌላ እንስሳ ሆኖ ሊመጣ ይችላል ብለው ያምናሉ፡፡ በአንዳንዱ ስፍራ አይጥ ለመግደል ይፈራሉ........ "ያቺ ነገረኛ አክስቴ ብትሆንስ!" ብለው ይሰጋሉና ነው፡፡ ህንድ ቦምቤ ሔጄ ሳይ በተለይ ላሞች በጣም ነው የሚከበሩት፡፡ ላሞቹ በመኪና አስፋልት ላይ ሲንጎራደዱ ወንድ ነኝ የሚል "እሽ" የሚላቸው የለም፡፡ እኔ በበኩሌ በዚህ አላምንም፡፡ እነርሱም ማመናቸው ይገርመኛል፡፡

ግን አብዛኞቻችን እንደምንስማማው ከሞት በኋላ ሌላ ህይወት አለ፡፡ በዚህ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ታዲያ "ስሞት ወዴት ነው የምሔደው? ወደ መንግስተ ሰማያት እገባለሁ ወይ?" ብሎ መጠየቅ መልካም ነው፡፡ ይሄ ብዙ ጊዜ የሚቀለድበት ሲኦል በእውነት ቢኖርስ?፤ እኔ እንደሆነ እዛ መግባት አልፈልግም፤ ወደ ሰላም ቦታ ነው መሔድ የምፈልገው፤ ስለዚህ ስለዘላለም ህይወት አስባለሁ፤ ወደ መንግስተ ሰማያት መግቢያዬን እፈልጋለሁ፡፡

እንኳን ወደ መንግስተ ሰማያት ካናዳ እንኳን ለመግባት ቪዛ ይጠየቃል፡፡ መስፈርት አለው፡፡ የእኔ መልካምነት ለመንግስተ ሰማይ የሚጠየቀውን መስፈርት ያሟላል ብዬ አላምንም፡፡ "ፃድቅ የለም..... አንድ እንኳን" ስለሚል ቃሉ (ሮሜ 3፡11)፡፡ ስለዚህም "በሩ እኔ ነኝ!....... መንገድ እኔ ነኝ!........ የዘላለም ህይወት እኔ ነኝ!........ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ህያው ይሆናል!" ያለውን ኢየሱስን አጥብቄ ይዣለሁ፡፡ እርሱ የተሰቃየው ለእኔ እንደሆነ በማመን....... ከዚያም ደግሞ እርሱ እንዳስታማረው በመኖር...... እከተለዋለሁ!፤ በእርግጥ እገባለሁ!፡፡ እርሶስ? ስለ ዘላለም ህይወት አስበው ያውቃሉ?

# የጥበብ እንቁ 39

## ታሪክ ሰሪ መሆን !

የክርስትና ታሪክ ሲነሳ ቅድስት ማርያምን ማንሳት የግድ ነው:: ምክንያቱም ክርስቶስ የሆነው ታላቅ ጌታ የመጣው በእርሷ በኩል ስለሆነ ነው:: እርሱ ከሀጢያታችን አዳነን!...... የመንግስቱ ወራሾች አደረገን!፤..... ከሲኦል አስመለጠን!........ በክቡር ደሙ አጠበን!...... ታደገን!....... የሞትን መውጊያ ሰበረልን!....... ዲያብሎስን ከእግራችን በታች ፈጥኖ ቀጠቀጠለን!........ ለዘላለም ስሙ የተባረከ ይሁን!:: ታዲያ በዚህ ድንቅ የማዳን ስራ ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ ቃል ስጋ እንዲሆን የፈቀደው በማርያም ማህፀን ውስጥ ነበር:: ይህም ሊረሳ የማይችል ታሪክ ሰሪ አደረጋት::

በየዘመናቱ ድንቅ የታሪክ ፀሀፊዎች ይነሳሉ:: ታሪክን ፅፈው ያስቀሩልናል:: ከመፀሀፍ ቅዱስ ጋ ተዛማጅ የሆነውን ታሪክ የፃፈልን ጆሴፈስ (Josephus) የሚባል ፀሀፊ ነው:: መፀሀፍ ቅዱስን ስናጠና ታሪካዊ ዳራውን ለማየት የጆሴፈስ ስራዎችን መንብኘት የማይቀር ነው:: በዚህም ምክንያት ይህ ታሪክ ፀሀፊ በጣም ጠቅሞናል:: የታሪክ ፀሀፊዎች የሚፅፉትን ታሪክ ደግሞ የየዘመናቱ የታሪክ ተመራማሪዎች ይመረምሩታል.... ያጠኑታል:: ህዝብም ታሪክን ያነባል!..... ያደምጣልም!:: ከነዚህ ሁሉ በላይ ግን ታሪክ ሰሪዎች (History Makers) ይበልጣሉ:: ታሪክ ሰሪዎች ባይኖሩ ኖሮ የሚፃፍም....... የሚመረመርም....... የሚነበብም ታሪክ ባልኖረ ነበር::

ጣልያን አገር ሔጄ ቫቲካንን ጎብኝቼ ነበር:: ታዲያ የሚያስጎበኘን ሰው አንዲት ትንሽ ክፍል ስንደርስ አቁሞን " የቅዱስ ጳውሎስ አንገት የተቀላው እዚህ ነበር" አለን:: በጣም ውስጤ ተነካ:: ያ ታሪክ ሰሪ ሐዋርያ ወንጌልን ሰብኮ....... የአዲስ ኪዳንን ሁለት ሶስተኛ ፅፎልን ይህንን አለም የተሰናበተው አንገቱ ተቀልቶ ነበር:: በዚያው አካባቢም ሌላው ታሪክ ሰሪ የሆነው ሐዋርያው ጴጥሮስ "እንደ ኢየሱስማ መሰቀል አልፈልግም!......

ከጌታዬ እኩል መሆን አልሻም፤ ስትሰቅሉኝ ዘቅዝቃችሁ ስቀሉኝ ብሎ ተሰውቷል:: የክርስትና ታሪክ በነዚህና በሌሎቹ ሐዋርያት ከእነርሱም በኋላ በተሰውት ሰማዕታት መስዋዕትነት ያሸበረቀ ነው::

ከመንፈሳዊውም አለም ወጣ ስንል ደግሞ ብዙ ታሪክ ሰሪዎችን እናስታውሳለን:: እንደ አብርሀም ሊንከን ያሉ ህግን አሻሽለው ለትውልድ የሚያልፍ ስራ ሰርተው የተሰው ሰዎች......... እንደ አልበርት አንስታይን ያሉ የተፈጥሮን እንቆቅልሽ ለመፍታት አእምሮአቸውን ያሰሩ ሰዎች........ እንደ ቻርልስ ዲከንስ ያሉ በስነ-ፅሁፍ ግፍን የታገሉ ፀሀፊዎች....... እንደ ሞዛርት ያሉ የሙዚቃ ሰዎች......... ዳቪንቼን የመሳሰሉ ድንቅ የሰነ-ስዕል ጂኒየሶች............. እንደ ስፐርጀን ያሉ የወንጌል ሰባኪዎች........ ታሪክን ሰርተውታል::

በእኛው በሀበሻው ህዝብ መሀል ታሪክ ሰርተው ያለፉ ድንቅ ሰዎችም ሞልተዋል:: እንደ ሚኒሊክ ያሉ የለውጥ አራማጆች....... እንደ አቡነ ጳውሎስ አይነት ሰማዕት የሆኑ የሀይማኖት መሪዎች....... እንደ አክሊሉ ለማ አይነት ሳይንቲስቶች........ እንደ ፀጋዬ ገ/መድህን አይነት ድንቅ ፀሀፊዎች....... እንደ አፈወርቅ ተክሌ አይነት ብርቅ ሰአሊዎች...... እንደ ወጋየሁ ንጋቱ ያሉ ያልተደገሙ ተዋናዮች......... እንደ ታደሰ ሙሉነህ ያሉ ታላላቅ ጋዜጠኞች........ ሌሎችም ብዙ ብዙዎች የሚያፍ ታሪክን ሰርተው አልፈዋል::

አሁን ሊያሳስበን የሚገባው "እኛ በተገኘንበት ትውልድ መሀል ታሪክን እየሰራ ያለው ማነው?" የሚለው ጥያቄ ነው:: ባሁኑ ዘመን አብዛኛው ሰው ኑሮን በማሻሻል ላይ ስላተኮረ...... ውድድሩ የንብረት ስለሆነ...... ለየት ያለ እሴት ያላቸው ሰዎች ብዙ አይመስሉኝም:: ጥያቄው ሁል ጊዜ "ገንዘብ ይገኝበታል ወይ?" ከሆነ ጂኒየሶች ከወዴት ይገኛሉ?፤ ሁላችን የምንሮጠው ለእንጀራ ከሆነ ታሪክ ሰሪዎች ከየት ይመጣሉ?:: ታሪክ የሚሰሩ ሰዎች..... ራሳቸውን የካዱ...... የኑሮ ሲምፕሊሲቲን (Simplicity) የተለማመዱ....... ከቁሳቁስ ፍቅር የራቁ...... ከንቱ ውዳሴ የማያስደስታቸው ሰዎች ናቸው:: እግዚአብሔር ሆይ! እባክህን በዘመናችን ታሪክ ሰሪ ሰዎችን ስጠን!::

# የጥበብ እንቁ 40

## ራዕይ፣ ሌጋሲ ፣ታላቅነት!

"እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" አለች ቅድስት ማርያም (ሉቃ 1:48) :: ትውልድ ሁሉ (All the Generations) ስትል አሁን ያለሁበት ትውልድ...... የሚቀጥለው ትውልድ........ ከዚያም በኋላ የሚመጣው ትውልድ....... ይህ አለም እስኪጠቀለል ድረስ ያለው ትውልድ ማለቷ ነው:: ይህ እጅግ በጣም አስገራሚ ራዕይ ነው::

'ትልቅ ሰው' ና 'ታላቅ ሰው' ለየቅል ናቸው:: በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተማረ ሰው ትልቅ ሰው ነው:: ባለ ሀብት ትልቅ ሰው ነው:: ባለስልጣን ትልቅ ሰው ነው:: ታዋቂ ሰው ትልቅ ሰው ነው:: 'ታላቅ ሰው' ግን ይለያል:: አንድ ሰው ታላቅ ሰው (Great Person) ነው የሚባለው በተገኘበት ትውልድ መሀከል ለውጥን አምጥቶ ለሚቀጥሉት ትውልዶች የሚተርፍ ሌጋሲ የተወ እንደሆነ ብቻ ነው:: ታላቅነት (Greatness) እንዲሁ በቀላሉ አይገኝም::

ወደ አሜሪካን ሀገር ስሔድና በዚያ ቆይታ ሳደርግ ፍፁም ነፃነት ተሰምቶኝ ነው:: እኔ ሐበሻ እንደመሆኔ ጥቁር ነኝ!:: ጥቁርነቴ ግን ምንም ተፅዕኖ አያመጣብኝም:: ነጮች በብዛት የሚገኙበት ሬስቶራንት ገብቼ የፈለኩትን አዝዤ እበላለሁ:: ነጮች የሞሉበት አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ "አሳልፈኝ" ብዬ በነፃነት ቦታዬ ላይ እቀመጣለሁ:: ነጮች በብዛት የሚያርፉበት ሆቴል ውስጥ ገብቼ አርፋለሁ:: ማንም ጥቁር ነህ ብሎ የሚከለክለኝ የለም!::

ከ 50-60 አመታት በፊት ግን ይህ የማይታሰብ ነበር:: አሜሪካ ውስጥ ጥቁሮች ሁሉ የነጮች በታች እንደሆኑ ነበር የሚታሰበው:: ልዩነቱ በጣም ሰፊ ስለነበር "ይህ የነጮች ት/ቤት ነው....... የጥቁሮች ልጆች እዚህ

# የጥበብ እንቁ 40

## ራዕይ፣ ሌጋሲ ፣ታላቅነት!

"እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" አለች ቅድስት ማርያም (ሉቃ 1:48) :: ትውልድ ሁሉ (All the Generations) ስትል አሁን ያለሁበት ትውልድ...... የሚቀጥለው ትውልድ........ ከዚያም በኋላ የሚመጣው ትውልድ....... ይህ አለም እስኪጠቀለል ድረስ ያለው ትውልድ ማለቷ ነው:: ይህ እጅግ በጣም አስገራሚ ራዕይ ነው::

'ትልቅ ሰው' ና 'ታላቅ ሰው' ለየቅል ናቸው:: በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የተማረ ሰው ትልቅ ሰው ነው:: ባለ ሀብት ትልቅ ሰው ነው:: ባለስልጣን ትልቅ ሰው ነው:: ታዋቂ ሰው ትልቅ ሰው ነው:: 'ታላቅ ሰው' ግን ይለያል:: አንድ ሰው ታላቅ ሰው (Great Person) ነው የሚባለው በተገኘበት ትውልድ መሀከል ለውጥን አምጥቶ ለሚቀጥሉት ትውልዶች የሚተርፍ ሌጋሲ የተወ እንደሆነ ብቻ ነው:: ታላቅነት (Greatness) እንዲሁ በቀላሉ አይገኝም::

ወደ አሜሪካን ሀገር ስሔድና በዚያ ቆይታ ሳደርግ ፍፁም ነፃነት ተሰምቶኝ ነው:: እኔ ሐበሻ እንደመሆኔ ጥቁር ነኝ!:: ጥቁርነቴ ግን ምንም ተፅዕኖ አያመጣብኝም:: ነጮች በብዛት የሚገኙበት ሬስቶራንት ገብቼ የፈለኩትን አዝዤ እበላለሁ:: ነጮች የሞሉበት አውሮፕላን ውስጥ ገብቼ "እሳልፈኝ" ብዬ በነፃነት ቦታዬ ላይ እቀመጣለሁ:: ነጮች በብዛት የሚያርፉበት ሆቴል ውስጥ ገብቼ አርፋለሁ:: ማንም ጥቁር ነህ ብሎ የሚከለክለኝ የለም!::

ከ 50-60 አመታት በፊት ግን ይህ የማይታሰብ ነበር:: አሜሪካ ውስጥ ጥቁሮች ሁሉ የነጮች በታች እንደሆኑ ነበር የሚታሰበው:: ልዩነቱ በጣም ሰፊ ስለነበር "ይህ የነጮች ት/ቤት ነው....... የጥቁሮች ልጆች እዚህ

መማር አይችሉም!" ፤ "ይህ የነጮች ሬስቶራንት ነው....... ጥቁሮች እዚህ መመገብ አይችሉም!" ፤ "ይህ የነጮች ሆስፒታል ነው........ ጥቁሮች እዚህ መታከም አይችሉም!" የሚባልበት ዘመን ነበር፡፡ ታዲያ ለውጡ እንዴት መጣ? ማርቲን ሉተር ኪንግ በተባለ ታላቅ ሰውና በአጋሮቹ፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ 'ታላቅ' (Great) መባል የሚገባው ሰው ነው፡፡ የተማረው ሶሽዮሎጂ (Sociology) ና ቲዎሎጂ (Theology) ነው፡፡ ሰባኪና የእግዚአብሔርን ቃል አስተማሪም ነበር፡፡ ኪንግ የራሱን የተመቻቸ ኑሮ መኖር ሲችል ለጥቁሩ ህዝብ መታገልን መረጠ፡፡ የመረጠውም የትግል ስልት ፍፁም ሰላማዊ ነበር፤ "የእኔ ሞዴል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!" ይል ነበር፤ ከዚያም ቀጥሎ የህንዱን ጋንዲን ያደንቅ....... እንደ አርአያም ይወስዳቸው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት በፍፁም ረብሻና ብጥብጥ እንዲነሳ የማይፈቅድ የነፃነት ታጋይ ነበር....... ኪንግ!፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ ለትውልድ የሚተርፍ ራዕይ ነበረው፡፡ ህልም አለኝ (I have a dream!) በሚለው ንግግሩ "እምናለሁ አንድ ቀን አራቱ ልጆቼ በቆዳቸው ቀለም ሳይሆን በአስተሳሰባቸውና በካራክተራቸው የሚመዘኑበት ዘመን እንደሚመጣ" ብሎ ነበር፡፡ እውነትም ታዲያ ያ ዘመን መጣ፡፡ ጭራሹኑ ጥቁር ፕሬዚደንት ወደ ኋይት ሀውስ ገባ!፡፡ ኦባማ በተመረጡ ጊዜ እንደ ጄሲ ጃክሰንና ኦፕራ ዊንፈሪን የመሳሰሉ ጥቁር አሜሪካኖች እንባቸውን ያፈሱ ነበር፡፡ ምናልባት በዛ ሰአት ማርቲን ሉተር ኪንግን አስበውት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡

ማርቲን ሉተር ግን በጥቁሮች ህይወት የመጣውን ለውጥ ለማየት አልታደለም ፡፡ በናሽቪል ቴነሲ የፅዳት ሰራተኞች እረብሻ አስነስተዋል ተብሎ ሲነገረው እነርሱን ለማረጋጋት ወደ ናሽቪል አመራ፡፡ በዚያም ቀን እነርሱን ሰብስቦ ንግግር ሲያደርግ "ወደ ተራራው ላይ ወጥቻለሁ (I have been to the top of the mountain) የተስፋይቱንም ምድር አይቻለሁ፡፡ እኔ አብሬያችሁ አልገባ ይሆናል፡፡ እናንተ ግን በእርግጠኝነት ትገባላችሁ" ብሎ ተናገረ፡፡ ይህንን ተናግሮ...... ስብሰባው ተበትኖ....... ሁል ግዜ ያርፍባት ወደ ነበረችው ሎሬን ሞቴል ሔደ፡፡ 306 ቁጥርም አረፈ፡፡ ነገር ግን አየር

ለመቀበል ከክፍሉ ወደ በረንዳው ሲወጣ ከየት እንደተተኮሰ በማይታወቅ ጥይት ተገደለ፡፡ ያ ታላቅ ሰው በ 39 አመቱ ይህንን አለም ተሰናበተ፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ በህይወት እያለ ብዙ የክብር ዶክትሬቶችን ተቀብሏል፡፡ የ 1964 ዓ/ም የሰላም ኖቤል ሽልማትም ተሸላሚ ነበር፡፡ የሚያስገርመው ከሞተም በኋላ የተለያዩ ሽልማቶችን ተሸልሟል፡፡ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን ታላቅ ሰው ስለሆነ የሰራው ስራ አብሮት አልሞተም፡፡ ሌጋሲው ይኖራል!፤ በሌጋሲውም እኔ እንኳን ተጠቅምያለሁ!፤ ታላቅነት ማለት ይህ ነው!፡፡

እንግዲህ ቢቻል ለትውልድ የሚሆን ሌጋሲ ትተን ብናልፍ መልካም ነው፡፡ ራዕያችን ለራሳችን ውድ መኪና ከመግዛት....... ፎቅ ቤት ከመስራት....... ማለፍ አለበት፡፡ የሚቀጥለው ትውልድ የሚጠቀምበትን ነገር ትተን ማለፍ አለብን፡፡ የዚያን ጊዜ የሚመጣው ትውልድ "ታላቅ ሰው ነበር!" ብሎ ያነሳናል፡፡ ትውልድ ሁሉ በልፋታችን ውጤት ይጠቀማል፡፡

# ሜርዮሎጂ (Mariology)

ምሁራን ናቸው፡፡ ለብዙ ዘመን ስለ ቅድስት ማርያም ያጠኑ ምሁራን፤ የካቶሊክ ምሁራን...... የኦርቶዶክስ ምሁራን...... የፕሮቴስታንት ምሁራን!......... በሜሪዮሎጂ ተጠበውበታል!፤ ብዙ ፅሁፎችን...... መፃህፍትንም ፅፈዋል፡፡ ሜሪዮሎጂ ማርያምንና ከማርያም ጋ የሚገናኝ ማንኛውንም ዶክትሪንና እምነት የሚያጠና የስነ መለኮት ክፍል ነው፡፡ ክሪስቶሎጂ ስለ ክርስቶስ የሚያጠና ክፍል እንደሆነ ሁሉ ሜሪዮሎጂም ስለ ማርያም ያጠናል፡፡ 'ማርያም በብሉይ ኪዳን'....... 'ማርያም በአዲስ ኪዳን'...... 'ማርያም በቀደሙ አባቶች እይታ'...... የመሳሰሉትን ሀሳቦች ይተነትናል፡፡ ሜርዮሎጂ ከሚያነሳቸው ትኩረትን የሚሰቡ ሀሳቦች አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማርያም የተወለደችበትና ያስተዳደጓ ታሪክ፡፡

  (The Birth and Growth of Mary)

- የዚህ ታሪክ ምንጭ የሆነው ፕሮቶ ኢቫንጄሊየም ኦፍ ጄምስ (Protoevangelium of James) እውነተኛ መሆን አለመሆን፡፡

- ማርያም ራሷ ስትፀነስ ያለ አዳም ሀጢያት እድፍ ነው ወይስ አይደለም ፡፡ ( Immaculate Conception)

- የቅዱስ ገብርኤል ለእርሷ መገለጥና የምስራቹን መንገር ፡፡

  (The Annunciation)

- የማርያም ምሳልያዊ ህይወት፡፡

  (The Exemplary life of Mary)

- ድንግል ሆና የመፅናትዋ ወይም ያለመፅናትዋ ነገር ::

  (Perpetual Virginity)

- በመፀሀፍ ቅዱስ የተነገረላት እውነት::

  (Biblical account)

- የመሞትዋና የአካልዋ ማረግ ወይም አለማረግ::

  (Death and Ascention)

- የሞተችው ኤፌሶን ነው ኢየሩሳሌም::

  (Ephesus Vs Jerusalem)

- የማማለድዋ ወይም ያለማማለዷ ነገር::

  (Intercession)

- ወደ ማርያም መፀለይ ይገባል አይገባም::

  (Prayers to Mary)

- በአክብሮት ሊሰገድላት ይገባል አይገባም::

  (Venerating and bowing to Mary)

- የማርያምን ስዕል የሳለው ሉቃስ ነው አይደለም::

  (The painting of Mary)

- ማርያም ለሰዎች ተገልጣ ታይታ ታውቃለች አታውቅም::

  (The Apparitions of Mary)

የተለያየ አቋም ያላቸው የሜሪዮሎጂ ምሁራን እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳዮችን እያነሱ ያጠናሉ.... ይነጋገራሉ፡፡ በየፊናቸው በጥልቀት ይመራመራሉ....... ያስተምራሉ!፡፡ በትምህርቶቻቸው መካከል ግን ልዩነቶች አሉ፡፡ በካቶሊኮችና በኦርቶዶክሶች መካከል እንኳን አንዳንድ የአስተምህሮ ልዩነቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ በቤተ-ክርስትያን ውስጥ ለወራት ወይም ለአመታት ብቻ የቆዩ ሳይሆን ለመቶ አመታት የዘለቁ ሙግቶች ናቸው፡፡

ልክ እንደ ምሁራኑ ሁሉ የተለያዩ የቤተ-ክርስትያን መሪዎችም ልዩነታቸውን በስብከቶቻቸው ያሳያሉ፡፡ ህዝባቸውን ያስተምራሉ፡፡ የእያንዳንዳቸውም አስተምህሮ ስር የሰደደ፣ የቤተ-ክርስትያን ዶክትሪን ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ታዲያ በዚህች ትንሽ መፀሀፍ ይህንን ሙግት እፈታዋለሁ ብዬ ባምን ምኝነት ይሆንብኛል፡፡ በእነዚህ ታላላቅ አብያተክርስትያናት...... ካቶሊክ..... ኦርቶዶክስና...... ፕሮቴስታንት መካከል ያለውን የሜሪዮሎጂ መሰረታዊ ልዩነቶችን ለማስረዳት እንኳን ሌላ ትልቅ መፀሀፍ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

በመግቢያው ላይ እንዳስረዳሁት የዚህ መፀሀፍ አላማ ከቅድስት ማርያም ህይወት መማር እንጂ ዶክትሪኖችን ማወዳደር.... ማበላለጥ ወይም ማስታረቅ አይደለም፡፡ በጥቅሉ ግን ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸውን ለማንሳት ይፈቀድልኝ፡፡ ቅድስት ማርያም ድንቅ ህይወት (Exemplary life) እንደነበራት ሁሉም ይስማማሉ፡፡ ደግነትዋ፣ ፍቅርዋ፣ መልካምነቷ በየትኛውም ጎራ ጥያቄ ውስጥ አይገባም፡፡ ደግሞም ማርያም ድንግል ሆና ያለ ወንድ ፈቃድ ከመንፈስ ቅዱስ እንደፀነሰች ሁሉም ያምናሉ፡፡ ቅድስት ማርያም የኢየሱስ እናት እንደሆነች...... ፈጣሪዋንም እንደወለደችው የሚከድ ማንም የለም፡፡ እውነት ለመናገር ማርያምን የማይወድ፣ ማርያምን የሚጠላ፤ ካቶሊክ ቢሆን ኦርቶዶክስ ወይም ፕሮቴስታንት........ አለ ብዬ አላምንም፡፡ ኢየሱስን የሚከተል..... መንፈስ ቅዱስን የተሞላ ........ ክርስትያን ተብሎ የሚጠራ ነገር ግን የማርያም ጠላት የሆነ አንድም ሰው ኢጋጥሞኝ አያውቅም፡፡ ቅድስት ማርያም በክርስቶስ አካል ሁሉ ዘንድ የተወደደችና የተከበረች ናት፡፡

ይሄን ያህል ካልኩኝ በኋላ በተለያዩ የክርስትያን ተቋማት...... በቤተ-ክርስትያን ደረጃ....... በተያዙ አስተምህሮዎች ላይ አስተያየት ከመስጠት እቆጠባለሁ......:: ነገር ግን በመፀሀፍ ቅዱስም ሆነ በየትኛውም ቤተ-ክርስትያን አስተምሮ ውስጥ የሌሉ ሁለት ከቀጥተኛው ትምህርት ያፈነገጡ አስተሳሰቦችን እንዳነሳ ይፈቀድልኝ:: ምክንያቱም ይህንን ሳደርግ የትኛውንም እምነት እንደማልነካ ስለማውቅ ነው::

የመጀመርያው አስተሳሰብ "ቅድስት ማርያም ከኢየሱስ በተጨማሪ ሌሎች ልጆች ነበሯት" የሚለው ትምህርት ነው:: የካቶሊክም ሆነ የኦርቶዶክስ አብያተክርስትያናት ቅድስት ማርያም ድንግል ሆና ፀንሳ..... ድንግል ሆና እንደወለደች በህይወቷም ዘመን ሁሉ ድንግል ሆና እንደኖረች ያምናሉ:: ይህም ፐርፐቱዋል ቨርጂኒቲ (Perpetual Virginity) በመባል ይታወቃል::

ታላላቅ የፕሮቴስታንቲዝም (Protestantism) መስራቾች የሆኑ እንደ ማርቲን ሉተር (Martin Luther) ና ጆን ካልቪንን (John Calvin) የመሳሰሉት አስተማሪዎችም በስራዎቻቸው ላይ ተፅፎ እንደምናነበው ሁሉም ማርያም በድንግልናዋ ፀንታ መኖርዋን ያምናሉ:: "ልጆች ነበሯት" ብለው አያውቁም:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ ጆን ዌስሊ (John Wesly) ያሉ ከእነርሱ በኋላ የተነሱ ፕሮቴስታንት አስተማሪዎችም በዚሁ በቅድስት ማርያም ድንግል ሆና የመፅናቷ ነገር ይስማማሉ:: ስለዚህም የፕሮቴስታንቲዝም አባቶች ያስተማሩት ማርያም ኢየሱስን ከወለደች በኋላ እድሜ ዘመንዋን ሁሉ ድንግል እንደነበረች ነው:: ዛሬም በአለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ፕሮቴስታንት መምህራን የማርያምን ድንግል ሆና የመፅናት ነገር አይጠራጠሩም::

ታዲያ "ማርያም ሌሎች ልጆች ነበሯት" የሚለው በአንዳንድ ግለሰቦች የሚነገር ትምህርት ከየት መጣ?:: የዚህ ትምህርት ምንጭ አንቲዲኮሜርያናይትስ (Antidicomarianites) ተብለው የተጠሩ ከ 200 እስከ 400 ዓ/ም በአረብ አገሮች አካባቢ የተንቀሳቀሱ አስተማሪዎች ናቸው:: የነዚህ ሰዎች ዋነኛ ፍላጎታቸው ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው

'ተራ ሰው' እንደሆን ማሳመን ነበር፡፡ ይህንንም ለማድረግ የተጠቀሙበት አንዱ መንገድ ደግሞ ማርያምን እንደማንኛዋም እናት 'ተራ ሴት'..... አግብታ የኖረች...... ልጆች የወለደች...... አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡ በፅሁፍም ደረጃ "ማርያም ልጆች አሏት" ብሎ የፃፈው በአሁንዋ ሰሜን አፍሪካዊት ሀገር በቱኒዚያ 'ካርቴጅ' በተባለ ቦታ በ 155 ዓ/ም ተወልዶ የኖረው ቴርቱሊያን (Tertullian) የተባለ ግለሰብ ነው፡፡ ስለዚህ "ማርያም ሌሎች ልጆች ነበሯት" የሚለው አስተሳሰቡ የ አንቲዲኮሜርያናይትስ አስተሳሰብ እንጂ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክ ወይም የፕሮቴስታንት አስተሳሰብ አይደለም፡፡

በመፀሀፍ ቅዱስ "የጌታ ወንድሞች" ተብለው የተጠቀሱ ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል (ማቴ 12:46)፡፡ ነገር ግን በአይሁድ ባህል የአጎትና የአክስት ልጆችን "ወንድሜ" "እህቴ" ብሎ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ የእኔ የአክስቶቼ ልጆች ከሰው ጋ ሲተዋወቁ "የዶ/ር ወዳጄነህ እህት ነኝ" ብለው ይተዋወቃሉ፡፡ እኔም ሳስተዋውቃቸው "እህቴ ናት....... ተዋወቃት" ነው የምለው፡፡ እነዚህ 'እህቶቼ' ግን የእናቴ ልጆች አይደሉም፡፡ ስለዚህም "የኢየሱስ ወንድሞች" ስለተባለ ብቻ "ማርያም ድንግልናዋን አጥታለች...... ሌሎች ልጆች ወልዳለች" ብሎ ማስተማር መፀሀፍ ቅዱሳዊ መሰረት የለውም፡፡ "የበኩር ልጇን እስከትወልድ ድረስ አላወቃትም" የሚለውም ቃል ይህንን አያመለክትም (ማቴ 1:25)፡፡ ስለዚህ ይህንን ትምህርት የሚያስተምሩ ግለሰቦች በዘመናችን ቢኖሩ ሳያውቁት ኢየሱስን ለማጣጣል ተነስተው ከነበሩ ሰዎች ጋ እየተባበሩ እንደሆነ አውቀው ትምህርታቸውን ያስተካክሉት፡፡ ቅድስት ማርያም ድንግል ሆና ፀንሳ ድንግል ሆና ወልዳለች!፣ ድንግል ሆና ወልዳም ድንግል ሆና ኖራለች!፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መፀሀፍ ቅዱስም ሆነ የትኛውም ቤተ-ክርስትያን ባላስተማረው መልኩ ለማርያም የእግዚአብሔርን ቦታ በመስጠት ለእግዚአብሔር የሚገባውን አምልኮ ለማርያም ካልሰጠን የሚሉ ሰዎች እንዲሁ ትምህርታቸውን ማስተካከል አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የካቶሊክም ሆነ የኦርቶዶክስ ወይም የፕሮቴስታንትም አባቶች "ማርያም አምላክ ነች! እናመልካታለን!" ብለው አላስተማሩምና ነው፡፡ አሁንም አያስተምሩም፡፡ ማርያምም እራሷ ዋጋ የከፈለችው

የክርስቶስ ክብር እንዲታይ...... ደምቆ እንዲያበራ..... ስሙም እንዲገንን ነው ። እርሷ እግዚአብሔርን ለመሸፈን..... የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለመጋረድ ሞከራ አታውቅም...... አትፈልግምም፡፡ ለዚህ ነው "እነሆኝ የጌታ ባርያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" ብላ ራሷን ዝቅ ያደረገችው፡፡ ይህ እርሷን አምላክ የማድረግ ሙከራ ማርያምን ራሷን በጣም እንደሚያስቀይማት..... እንደሚያሳዝናት እረዳለሁ፡፡ ሁሉም የየራሱ ቤተ-ክርስትያን የሚስተምረውን ትክክለኛ ትምህርት ቢያውቅ እግዚአብሔርን ከመበደል ይጠበቅ ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡

እኔ ራሴን 'ክርስትያን' ብዬ መጥራት ብመርጥም...... ፕሮቴስታንት ክርስትያን መሆኔ የታወቀ ነው፡፡ ካሪዝማቲክ.... ፔንቴኮስታል..... ፕሮቴስታንት....... ክርስትያን ነኝ፡፡ ወደ ፊትም እንዲሁ እንደሆንኩ እቀጥላለሁ፡፡ ታዲያ "ፕሮቴስታንቶች ማርያምን አይወዱም" የሚባል ነገር ስሰማ አዝናለሁ፡፡ ምክንያቱም ፕሮቴስታንቶች ማርያምን እንደሚወዷት...... መፀሀፍ ቅዱስ የሚሰጣትን አክብሮትም እንደማይነፍጓት ስለማውቅ ነው፡፡ እንኳን ለቅድስት ማርያም ለእኔዋ ሚስኪን እናቴ የሚገባትን የናትነት አክብሮት ነፍጊያት አላውቅም፡፡

በግሌ ፀሎትን በምፀልይበት ጊዜ የምፀልየው ወደ እግዚአብሔር ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ባስተማረኝ መሰረት ......... እንደተረዳሁት...... እፀልያለሁ፡፡ የምፀልየው በቅዱስ መንፈሱ ምሪት ነው!፤ የምፀልየው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው!፤ የምፀልየው ወደ እግዚአብሔር ነው፡፡ በፀሎቴ እግዚአብሔርን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላደረገልኝ ማዳኑ አመሰግነዋለሁ፡፡ ደግሞም ስለ ቅዱሳን መላዕክቱ፣ በፊቱ ስላሉት ሐዋርያትና ነብያት፣ እንዲሁም ስለ ቅድስት ማርያምና ስለ ሌሎቹ የእምነት እናቶች አመሰግነዋለሁ፡፡ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ስላለ (Omnipresent ስለሆነ) አሜሪካም፣ ቻይናም፣ ኢትዮጵያም የሚፀለየውን ፀሎት በአንድ ጊዜ ይሰማል፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ (Omniscient ስለሆነ) የምፀልየው ፀሎት እንግዳ አይሆንበትም፤ ገና ከመፀለዬ በፊት እርሱ ችግሬን አስቀድሞ ያውቀዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ (Omnipotent) ከመሆኑ የተነሳ የምለምነውን ነገር ሊያደርግልኝ ምንም አያስቸግረውም፡፡

በአብያተ-ክርስትያናት መካከል የተለያዩ ሜሪዮሎጂካል እምነቶችና አመለካከቶች መንፀባረቃቸው የማይቀር ነው፡፡ ለምሳሌ በቅድስት ማርያም አማላጅነት ላይ በአብያተክርስትያናት መካከል ልዩነቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህም ልዩነቶች በአብያተክርስትያናቱ በዶክትሪን ደረጃ የተያዙ ናቸው፡፡ ለሁሉም አብያተክርስትያናት ካለኝ ጥልቅ አክብሮት የተነሳ የራሴን አስተያየት በዚህ መፀሀፍ አላቀረብኩም፡፡ ልዩነቶቹም እንዳሉ መቀጠላቸው የማይቀር ነው፡፡ እግዚአብሔር የክርስቶስን ቤተሰብ ሁሉ ይባርክ!፡፡

# ኤኪውሜኒዝም (Ecumenism)

የኢትዮጵያ መካነ ኢየሱስ ቤተ-ክርስትያንና የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ቤተ-ክርስትያን ሁለቱም ፕሮቴስታንቶች ናቸው፡፡ ልዩነቶች ግን አሉአቸው፡፡ መካነ ኢየሱስ ህፃናትን ስታጠምቅ ሙሉ ወንጌል ደግሞ በህፃናት ጥምቀት አትስማማም፡፡ በዚህ ልዩነታቸው ምክንያት ግን አንዳቸው ሌላውን "መናፍቅ" እያሉ አይጠሩም፡፡ "ወንድሜ!" "እህቴ!" ነው የሚባባሉት፡፡ የአንዱ ሰባኪ ሌላው መድረክ ላይ ተጋብዞ ይሰብካል፡፡ ልዩነታቸውን አቻችለው አንድነታቸውን ጠብቀዋል፡፡

ለታላላቆቹ አብያተክርስትያናት ማለትም ለኦርቶዶክስ ለካቶሊክና ለፕሮቴስታንቶችም የምመኘው ይህንን ነው፡፡ ልዩነታቸውን አቻችለው አንድነታቸውን እንዲጠብቁ!፡፡ ይህ ደግሞ የእኔ ምኞት ብቻ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ የፀለየበትም ጉዳይ ነው፡፡ "እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ" ብሏል በፀሎቱ (ዮሐ 17:22)፡፡ አካሉ ሲከባባር፣ ሲዋደድና ሲቀራረብ እርሱ የፍቅር አምላክ ደስ ይለዋል፡፡ አንዳንድ ቤተ-ክርስትያኖችና ተቋማት ይህን ህብረትና አንድነት ለማምጣት ይጥራሉ፡፡ ይህም ኤኪውሜኒዝም (Ecumenism) ተብሎ ይጠራል፡፡

ኤኪውሜኒዝምን ብዙዎች ሲደግፉት አንዳንዶች ደግሞ ሲነቅፉት ይታያል፡፡ ከሚቃወሙት አንዳንዶቹ ኦርቶዶክስ ከሆኑ "ብቸኛዋ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰረታት ሐዋርያዊት ቤተ-ክርስትያን ኦርቶዶክስ ናት!" ይላሉ፡፡ ካቶሊክ ከሆኑ ደግሞ "ብቸኛዋ ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰረታት የጴጥሮስ ቁልፍ ያላት ሐዋርያዊት ቤተ-ክርስትያን ካቶሊክ ናት!" ይላሉ፡፡ ፕሮቴስታንት ከሆኑም "በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግም የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች ፕሮቴስታንቶች ብቻ ናቸው!" ብለው ያስተምራሉ፡፡

እኔ እንዳየሁት ሰዎች መግባባት የማይችሉት የራሳቸውን እምነት በጥልቀት የማያውቁት ከሆነ ነው፡፡ የካቶሊክ እምነትን በጥልቀት ከሚያውቅ ካቶሊክ ጋ ስንገናኝ በጣም እንግባባለን፡፡ ልዩነታችንንም በእውቀት እንረዳለን፡፡ ተጫውተን በፍቅር እንለያያለን፡፡ እንደዚሁም የኦርቶዶክስን

እምነት በጥልቀት ከሚያውቅ ሰው ጋ ስንገኛኝ በሚገባ እንግባባለን፡፡ ከፕሮቴስታንቱም ጋ እንደዚሁ፡፡ በስም ብቻ አማኝ ከሆኑና እውቀታቸው ላይ ላዩን ከሆነ ግን ፈጥነው ይቆጣሉ፡፡ የሚናገሩትንም አያውቁም፡፡ ስለዚህ ችግሩ ያለው የልዩነቱ መስፋት ላይ ሳይሆን ያሉበትን ቤተ-ክርስትያን አስተምህሮ በጥልቀት አለመረዳት ነው፡፡

ለእኔ ቤተ-ክርስትያን አንድ ናት፡፡ በዘመናት በታሪክ በተለያየ መከፋፈል (Schism) ብትለያይም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር አንድ አካል እንዳለው ነው የማምነው፡፡ ለዚህም ነው በተደጋጋሚ መድረክ ላይ ስወጣ “እኔ ክርስትያን ነኝ!” የምለው፡፡ በአስተሳሰብና በልብ ስፋት አምናለሁ፡፡ ሌላው ክርስትያን ወንድሜ የሚያምነውን ሳላጣጥልበት ማዳመጥና ከእኔ ጋ ያለውን ልዩነት በፍቅር መረዳት ደስ ይለኛል፡፡

ታዲያ በወገኔ በሀበሻው ህዝብ መሀል በሚገኙ አብያተክርስትያናት ማለትም አርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት መካከል መቀራረብ...... መዋደድ.... መከባበር እያደገ ቢመጣ መልካም ይመስለኛል፡፡ በስብከቶቻችንም እነዚያኛዎቹ እነዚህኛዎቹን “መናፍቃን” ከማለት ቢቆጠቡ እነዚህኛዎቹ ደግሞ እነዚያኛዎቹን “አህዛብ” ከማለት ቢቆጠቡ....... ደግሞም እንደ ወንድምና እንደ እህት ቢተያዩ እጅግ መልካም ይሆን ነበር፡፡

በስብከታችንና በትምህርታችን መሀል ቅዱሳን መላዕክቱን ስናነሳ በአክብሮት እናንሳቸው፡፡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰይፍና በስቅላት ሰማዕት የሆኑትን እንደነ ጳውሎስና ጴጥሮስ የመሳሰሉትን የወንጌል አርበኞችንም ስናነሳቸው እግዚአብሔር የሰጣቸውን አክብሮት አንንፈጋቸው፡፡ እንዲሁም ቅድስት ማርያምን ስናነሳት በአክብሮትና በትህትና እናንሳት፡፡

ሁሉም በየምስባኩ ከድንግል ተወልዶ ስለ ሰው ልጆች ደሙን ያፈሰሰውን ኢየሱስ ክርስቶስ መድህኔአለምን ያለመቆጠብ ያግንነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ሁሉ ይገባዋልና ሁሉም ዝቅ እያለ እርሱን ከፍ ያድርገው፡፡ ትውልድ ሁሉ ይዘምርለት! ይቀኝለት!፡፡ የሁሉም ቤተ-ክርስትያን ራስ..... የጌቶቹ ጌታ.....የነገስታቱ ንጉስ.....አልፋና ኦሜጋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና!፡፡

# የሐይማኖት ውይይት! (Interfaith Dialogue!)

ከቤተ-ክርስትያን ወጣ ልበልና በዚህኛው ሀሳቤን ልቋጭ:: እኔ በጣም የምወዳቸው ሙስሊም ጓደኞች አሉኝ:: አብረን ተምረናል:: በጣም ነው የምንዋደደው:: ስንገናኝ አብረን በልተን..... ስቀን..... ተጫውተን..... ነው የምንለያየው:: አንዳንድ ጉዳይ ሲኖራቸው ይደውሉልኛል:: እኔም ስፈልጋቸው እደውልላቸዋለሁ:: የሁል ጊዜ ጓደኞቼ ናቸው::

ደግሞ የጆሆቫ ዊትነስ የሆኑ ዘመዶቼ አሉ:: ቤቴ ይመጣሉ፤ እኔም ቤታቸው እሔዳለሁ፤ በጣም እንተሳሰባለን:: ውጪ ያሉት ሁሉ ትዝ ስላቸው ይደውሉልኛል፤ እኔም ያሉበት አገር ስሔድ እጎበኛቸዋለሁ፤ አብረን ወጥተን አገር እናያለን:: የሁል ጊዜ ዘመዶቼ ናቸው::

በአለም ላይ ያሉ እምነቶችን ሁሉ አንድ ማድረግ አይቻልም:: እንደውም አንድ አለም አቀፍ ሐይማኖትን የሚያመጣው ሀሰተኛው ክርስቶስ ሲመጣ ነው:: ሐይማኖቶች ልዩነታቸውን ጠብቀው በመቻቻል ይኖራሉ:: ሁሉም በራሳቸው መንገድ ይቀጥላሉ::

ታዲያ በእኛ በህበሮቼ መካከል የቆየ የመቻቻልና የመከባባር ባህል አለን:: የተወለድኩባት ሐረር ለዚህ ምሳሌ በመሆኗ ደስ ይለኛል:: ህገራችን የምትመራበት ህገመንግስት ማንኛውም ዜጋ የወደደውን ሐይማኖት የመከተል መብት እንዳለው አበክሮ ያስረዳል:: አንዱ ሌላውን መተናኮል ነው የማይችለው::

እኔ የተገኘሁበትን ህዝብ አደራ የምለው ይህ መከባበርና መቻቻል እንዲቀጥል ነው:: የሐይማኖት ግጭቶችን ለማነሳሳት የሚፈልጉ የውጪ ሀይላት እጃቸውን ጣልቃ ለማስገባት ሲሞክሩ ህዝቡ በፍፁም እምቢ ማለት ነው ያለበት:: በበለጠ መቻቻል.... በጨመረ መከባበር..... በላቀ ፍቅር.... እንድንኖርና ይህም መልካም ነገር በሚመጡት ትውልዶች ሁሉ እንዲቀጥል እግዚአብሔር ይርዳን:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!:: አሜን!::

# ምስጋና

የእግዚአብሔርን ስራ ልንሰራ ስንነሳ ብቻችንን ልንፈፅመው ከቶ እንደማንችል እንረዳለን:: የሚያግዙንን ሰዎች ፍለጋ አይናችን ይማትራል:: እንደኔ አይነቱ በብዙ ሰዎች ያልተከበበ ብቸኛ ሰው ደግሞ የበለጠ ይቸገራል:: "አሁን ማን ነው በዚህ ጉዳይ የሚያግዘኝ" እያለ ያስባል:: የሚያስገርመው ግን እግዚአብሔር ሁል ጊዜ የራሱ ሰዎች አሉት:: በእርሱ የተባረኩ፣ ገንዘባቸውም የእርሱ ገንዘብ የሆነ፣ ለእርሱ ሁለንተናቸውን የሰጡ ልጆች አሉት እግዚአብሔር::

ታዲያ እኔ ይህንን መፀሀፍ ፅፌ ከጨረስኩ በኋላ ለማሳተም ስነሳ እንደዚህ አይነት ሰዎች ናቸው ወደ እኔ የተላኩት:: በማበረታታት፣ በፀሎት፣ በገንዘብ እግዚአብሔር የሰጠኝ ወንድሞቼና እህቶቼ አገዙኝ:: ሁሉም ስማቸው እንዲነሳ የማይፈልጉ፣ በቀኛቸው ያደረጉትን ግራቸው እንዳታውቅ የሚከለከሉ ናቸው:: ባህሪያቸው ሆኖ የሚሰጡት አምላካቸውን ለመታዘዝ ስለሆነ "አደረጉ" ተብሎ እንዲነገርላቸው አይፈልጉም:: እኔም ይህን ድንቅ አስተሳሰባቸውን አከብርላቸዋለሁ::ለዚህም ነው ስማቸውን ያልዘረዘርኩት::


እነዚህን ወንድሞቼንና እህቶቼን በማገለግለው ጌታ ፊት በፀሎት ባርኬያቸዋለሁ:: አሁን ደግሞ በግሌ ላመሰግናቸው እወዳለሁ:: እናንተ የተወደዳችሁ ወገኖቼ..... እግዚአብሔር ይባርካችሁ:: ስላደረጋችሁልኝ መልካም ነገር ሁሉ ከልቤ አመሰግናለሁ:: ውለታችሁንም ፈፅሞ አልረሳም:: መልካሙን ብድራታችሁን እግዚአብሔር ይከፈልልኝ::

# ፀሎት

ከዚህ በታች አንድ ፀሎት አቅርቤያለሁ፡፡ እርሶ ከአምላኮ ከእግዚአብሔር ጋ መልካም ህብረት (Fellowship) ካለዎት ይህን ፀሎት መፀለይ አያስፈልጎትም፡፡ ደግሞም ከዚህ በፊት እንዴት እንደሚፀለይ በመምህራኖችዎ በሚገባ ተምረው ከሆነም ይህ አጭር ፀሎት ብዙም አይጠቅሞትም፡፡ ነገር ግን ከአምላክዎ ጋ እንዴት መነጋገር እንዳለቦት የማያውቁ ከሆነ፣ ከዚህም በፊት ከልብዎ ፀልየው የማያውቁ ከሆነ ይህንን አጭር ፀሎት በእግዚአብሔር ፊት ይፀልዩት፡፡

“እግዚአብሔር ሆይ! በአንተ ተፈጥሬ በአንተው ስለተመረጥኩ አመሰግንሀለሁ፡፡ በህይወት ዘመኔም ሁሉ ስለጠበከኝ፣ ከክፉ ስለታደከኝ፣ እዚህ ስላደረስከኝ በኢየሱስ ስም አመሰግንሀለሁ፡፡ ጌታ ሆይ! በቀራንዮ መስቀል ላይ ሐጥያት የማያውቀው ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኔ ሐጥያት ስርየት እንደ ተሰቀለ፣ ደሙን እንዳፈሰሰ፣ እንደተሰቃየ ፣ነፍሱንም አሳልፎ እንደሰጠ አምናለሁ፡፡ ደግሞም የሞትን መውጊያ ሰብሮ ከሙታን እንደተነሳ፣ ወደ አንተ ወደ አባቱ እንዳረገም አምናለሁ፡፡ አቤቱ በህይወት ዘመኔ የሰራሁትን በደልና ሐጢያት ሁሉ ይቅር በለኝ፣ ክቡር በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም እጠበኝ፣ አንፃኝ፡፡ ቀሪውን ዘመኔን ለብቻዬ ልኖር አልወድምና ክርስቶስ ወደ ህይወቴ ይግባ፡፡ አለምን፣ ሰይጣንንና ከፉ ስራውን እክዳለሁ፤ አንተን እከተልሀለሁ!፤ አመልክሀለሁ!፡፡ በምድር ላይ ልኖር በቀረልኝ ዘመን ሁሉ ያንተ ፈቃድ ይሁንልኝ፡፡ በቅዱሳን መላዕክቶችህ ጠብቀኝ፡፡ የመንግስትህ ወራሽ አድርገኝ፡፡ እኔንም፣ ቤተሰቤንም፣ ያለኝንም ሁሉ ለአንተ አደራ አሳልፌ ሰጠሁ፡፡ ስለተቀበልከኝ፣ ፀሎቴንም ስለሰማህ በምትወደው ልጅህ በኢየሱስ ስም አመሰግንሀለሁ፡፡ አሜን!፡፡

**ተፈፀመ!........ እናም ........ ተጀመረ!**





**ቅድስት ማርያም**

እግዚአብሔርን በመምሰል
በህይወቷ ያሳየቻቸው
40 የጥበብ እንቁዎች

የሀበሻው ህዝብ
ከሚወዳት ድንግል ማርያም
ምን ይማራል?

ደራሲው ዶ/ር ወዳጄነህ መሐረነ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሲሆን በህክምና ሳይንስ የዶክትሬት ዲግሪ በሳይኮሎጂ የማስተርስ ዲግሪ በቲዎሎጂ የማስተርስ ዲግሪ እንዲሁም በትሮፒካል ሜዲሲን የማስተርስ ዲግሪ አግኝቷል። ዶ/ር ወዳጄነህ አዌከኒንግ አለም አቀፍ የመንፈስ ቅደሱ ሚኒስትሪ የተባለን አገልግሎት ይመራል።

ዋጋ 30 ( ሰላሳ ብር ) ብቻ
$ 10
ርሆቦት አታሚዎች